የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሣኛ ዓመት ቁጥር ፳፭
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No.25
ADDIS ABABA, 20th May 2024


**ማውጫ**


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፳፪/፪ሺ፲፮

የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አዋጅ ……………..ገጽ ፲፭ሺ፬፻፺፫


**Content**


Proclamation No 1322/2024

Special Economic Zone Proclamation...Page 15493


## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፳፪/፪ሺ፲፮

## የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አዋጅ

በኢትዮጵያ እስካሁን ተግባራዊ የተደረገውን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ሥርዓት ዲዛይን እና ትግበራ ወደልዩ የኢኮኖሚ ዞን ሥርዓት በማሳደግ የኢኮኖሚውን መስፋፋት እና ተፅእኖ ፈጣሪነት ከፍ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የልዩ ኢኮኖሚ ዞን መርሀ-ግብር ቀልጣፋ እና አመቺ የኢንቨስትመንት እና የንግድ ከባቢ ሁኔታ ማሻሻያዎችን ለመፈተሽ እና አስፈላጊ በሆነ ጊዜም ወደ ሀገራዊው ኢኮኖሚ ለማስፋፋት አይነተኛ መሳሪያ መሆኑን በመገንዘብ፣

የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ማዕቀፍ የሀገሪቱን የዓለም-አቀፍ እሴት ሰንሰለት ተሳትፎ ለማጎልበት፣ እንዲሁም በቀጠናዊ ንግድ ውጤታማ በሆነ መንገድ በቅልጥፍና፣ በጊዜ፣ እና በወጪ የመወዳደር አቅምን ለማጠናከር የሚያስችል በመሆኑ፣

## PROCLAMATION NO. 1322/2024

## SPECIAL ECONOMIC ZONE PROCLAMATION

**WHEREAS** it has been found imperative to step up Ethiopia's experience in the design and implementation of the industrial parks' scheme to a special economic zone regime in order to attain higher economic diversification and impact;

**REALIZING** that a special economic zone program is conceived as an appropriate mechanism for experimenting on efficient and conducive investment and business environment reforms which may be scaled to the wider economy where appropriate;

**WHEREAS** a special economic zone framework serves to enhance the country's participation in global value chains and strengthen its capacity to effectively compete in regional trade on efficiency, lead time and cost;




https://t.me/customsclearingagents

በሀገሪቱ አዋጪ እና ስትራቴጂያዊ በሆኑ አካባቢዎች የሚመሰረቱ ልዩ ኢኮኖሚ ዞኖችን ልማት፣ አስተዳደር እና ቁጥጥር የሚገዛ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀፅ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፳፪/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "ልዩ የኢኮኖሚ ዞን" ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ የተሰየመ፣ ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ በሚፈጥሩ ፖሊሲዎች፣ ንግድን በሚያሳልጡ አቅርቦቶች፣ መሰረተ-ልማቶች እና አገልግሎቶች የተደገፈ፣ እንዲሁም የአንድ ማእከል አገልግሎት፣ የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ነጻ ጥቅሞች እና ሌሎች ልዩ ማበረታቻዎች ያሉት ሆኖ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን፣ ነፃ የንግድና ሎጂስቲክስ ቀጠናዎች፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፓርኮች፣ የአገልግሎት ፓርኮች፣ የግብርና እና እንስሳት ዞኖች እና ተመሳሳይ ኢንቨስትመንቶችን ሁሉ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ከእነዚህ አንዱን ወይም የተወሰኑትን ብቻ ይዞ የተደራጀ የጉምሩክ



**RECOGNIZING** the importance of adopting legislation in respect of the development, operation and regulation of special economic zones to be established in commercially viable and strategic locations;

**NOW, THEREFORE, in** accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short title

This Proclamation may be cited as the **''Special Economic Zone Proclamation No. 1322/2024''.**

### 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ **''Special Economic Zone''** means a geographical area designated by the Ethiopian Investment Board in accordance with this Proclamation which is subjected to customs control, and is attended by business enabling policies, trade facilitation service, infrastructure and utilities, and amenities including a one stop shop, duty and tax free privileges and other special incentives, and as appropriate organizing within it any one or several of the following constituents: industry parks, free trade and logistics zones, science and technology parks, service parks, agriculture and livestock zones, and similar investments;

https://t.me/customsclearingagents

ቁጥጥር የሚደረግበት የተለየ አካባቢ ነው፤

፪/ "የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስያሜ" ማለት በአልሚው የሚቀርብ ማመልከቻ እና አባሪ ሰነዶች አጥጋቢ በሆነ ደረጃ ተሟልተው መቅረባቸው ሲረጋገጥ ቦርዱ ለአንድ ተለይቶ ለሚታወቅ ቦታ ለአንድ ወይም ለባለብዙ ዘርፍ የልዩ የኢኮኖሚ ዞን ደረጃ ለመስጠት የሚያሳልፈው ውሳኔ ነው፡፡

፫/ **"መሠረተ-ልማት"** ማለት ለልዩ ኢኮኖሚ ዞን ልማት አስተዳደር አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችን፣ የኤሌክትሪክ ሀይል፣ ጋዝ፣ የመጠጥ እና ኢንዱስትሪ አገልግሎት ውሀ የሚያቀርቡ መስመሮች፣ ቴሌኮም፣ የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ስርአት፣ የአየር ብክለት መቀነሻ ሥርዓት፣ የፍሳሽ መውረጃ፣ የማዕበል እና መሬት መሸርሸር መቆጣጠሪያ፣ መንገድ፣ ድልድይ፣ ባቡር፣ ወደብ እና የአየር ማረፊያን ጨምሮ የትራንስፖርት አገልግሎት፣ እና ሌሎች ለልዩ ኢኮኖሚ ዞን ልማት እና አስተዳደር አስፈላጊ የሆኑ መሰል ልማቶችን ያካትታል፤

፬/ "የኢንዱስትሪ ፓርክ" ማለት ዕቃዎች የሚራገፉበት፣ የሚከዘኑበት፣ የሚያዙበት፣ የሚበተኑበት፣ እንደገና የሚታሸጉበት፣ የሚገጣጠሙበት፣ የሚሰራጩበት፣ የሚለዩበት፣ ደረጃ የሚወጣበት፣ የሚነፁበት፣ የሚደባለቁበት፣ የሚመረቱበት ወይም በሌላ መልክ የሚቀርቡበት፣ እና ለኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት የሚቀርቡበት ወይም ተመልሰው ወደ ውጪ የሚላኩበትን ሂደት የሚያካትት በአምራች ዘርፍ ላይ ትኩረት ያደረገ ሥራ የሚከናወንበት ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ነው፤

2/ **‘‘Special Economic Zone Designation’’** means a decision passed by the Board to accord a certain geographical area unipurpose or multipurpose a special economic zone status where it is proved that the developer’s application and documentary requirements are completed to a satisfactory extent.

3/ **“Infrastructure”** means equipment, grids for the provision of electricity, gas, potable and industrial water, telecom, solid and liquid waste management, air pollutant emissions management, drainage, tide and erosion control, transportation including roads, bridges, rail, harbors and airstrips, and other like structures necessary for the development and operation of special economic zones;

4/ **“Industrial Park’’** means a special economic zone with a focus on manufacturing activities, and includes areas in which goods may be landed, stored, handled, broken up, repackaged, assembled, distributed, sorted, graded, cleaned, mixed, manufactured or reconfigured, and re-exported or supplied as input for industries;

https://t.me/customsclearingagents

፭/ **"ነፃ የንግድ ቀጠና"** ማለት ዕቃዎችና አቅርቦቶች ያለ ጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ክፍያ ወደ ሀገር የሚገቡበት፣ የሚከዘኑበት፣ የሚቀየሩበት፣ የሚያዙበት፣ የሚመረቱበት፣ እንደገና የሚሰሩበት እና/ወይም ተመልሰው ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩበት በዚህ አዋጅ መሰረት ልዩ ኢኮኖሚ ዞን እንዲሆን የተሰየመ ቦታ ነው፤

፮/ **"የግብርና ዞን"** ማለት የአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ የግብርና ኤክስቴንሽን፣ ንብ እርባታ፣ አሳ ሃብት ልማት፣ የግብአት አቅርቦት አገልግሎት፣ የደረቅ እና ቀዝቃዛ መጋዘኖች ኦፕሬሽን፣ የእንስሳት ማቆየት እና ክትትል፣ እንስሳትን የመመገብ እና ማደለብ፣ የቄራ አገልግሎት፣ የእንስሳት መድሀኒቶች ምርት ስራ እና የመሳሰሉትን ጨምሮ የግብርናውን ዘርፍ፣ በዘርፉ የሚሰጡ አገልግሎቶችን እና ተያያዥ የስራ ሂደቶችን ለማሳለጥ በዚህ አዋጅ መሰረት ልዩ ኢኮኖሚ ዞን እንዲሆን የተሰየመ ቦታ ነው፤

፯/ **"የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ፓርክ"** ማለት በጥናት፣ በማስተማር፣ እውቀትን በማልማት፣ በግብይት እና ተያያዥ አገልግሎቶች እና ስራዎችን በማከናወን የእውቀት፣ የፈጠራ፣ የምርምር እና ልማት፣ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ፣ የኢንፎርሜሽን እና ኮሚዩኒኬሽን ዘርፎችን የማስተዋወቅ እና ማልማት ስራዎችን ለማሳለጥ በዚህ አዋጅ መሰረት ልዩ ኢኮኖሚ ዞን እንዲሆን የተሰየመ ቦታ ነው፤

፰/ **"የአገልግሎት ፓርክ"** ማለት በሆቴል፣ ቱሪዝም እና ሆስፒታሊቲ፣ ኢንፎርሜሽን እና ኮሚዩኒኬሽን፣ በሎጂስቲክስ፣ በፋይናንስ እና ኮርፖሬት ተቋማት ዋና ማእከል፣ እና በመሳሰሉት ላይ ወይም ከእነዚህ በአንዱ



5/ **“Free Trade Zone’’** means a special economic zone designated under this Proclamation in which goods and services may be imported, stored, transformed, handled, manufactured, reconfigured and/or re-exported suspensive of customs duties and taxes;

6/ **“Agricultural Zone”** means a special economic zone designated under this Proclamation to facilitate the agricultural sector, its services and associated activities including agro-processing, agricultural extension, apiculture, fishery, input supply services, dry and cold storage and warehousing operations, livestock marshalling and inspection, livestock feeding or fattening, abattoir, veterinary product manufacturing, and associated activities;

7/ **“Science and Technology Park”** means a special economic zone designated under this Proclamation to facilitate the promotion and development of knowledge, innovation, research and development, science, technology, information and communication sectors through associated research, teaching, incubation, commercialization, and related services and activities;

8/ **“Service Park’’** means a special economic zone designated as such under this Proclamation with a dedicated package of policy benefits and purpose-built infrastructure focusing on one or more types

https://t.me/customsclearingagents

አገልግሎት ላይ ትኩረት አድርጎ እና ራሱን የቻለ የፖሊሲ ድጋፍ እና ዘርፍ-ተኮር መሰረተ-ልማት ኖሮት አገልግሎት እንዲሰጥ በዚህ አዋጅ መሰረት ልዩ ኢኮኖሚ ዞን እንዲሆን የተሰየመ ቦታ ነው፤

of services including hotels, tourism and hospitality, information and communication, logistics, finance and corporate entities headquarters, and the like;

፱/ **"የሎጂስቲክስ ፓርክ"** ማለት በውስጡ የሎጂስቲክስ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ለማቀፍ የሚችል ሆኖ የካርጎ ማጣመር እና መለየት፣ ማሸግ፣ መለያ መስጠት፣ የስርጭት፣ የክፍት ወይም ዝግ መጋዘን፣ የትራንዚት ጉዞ መጋዘን፣ የኮንቴይነር ጭነት ጣቢያ፣ የእቃዎች ማንቀሳቀሻ መሳሪያ እና የመሳሰሉትን የሚያካትት እንደ የውስጥ መንገድ፣ የሀይል መስመር፣ የውሀ ማስተላለፊያ፣ የቆሻሻ እና የውሀ መውረጃ መስመሮች ያሉ መሰረተ-ልማቶች የሚሟሉለት የለማ አካባቢ ነው፤

9/ **"Logistics Park"** means an estate developed for the establishment of enterprises engaged in logistic services including cargo aggregation and segregation, packaging, labeling, distribution, open storage or closed storage, ambient condition storage for transit period, a container freight station, material handling equipment, and possesses infrastructure like internal roads, power line, water distribution, sewage and drainage lines;

፲/ **"የጉምሩክ ክልል"** ማለት የኢትዮጵያ የግዛት ክልል ነው፤

10/ **"Customs Territory"** means the territory of Ethiopia;

፲፩/ **"ዕቃ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት"** ማለት ማናቸውንም ዕቃ ወይም አገልግሎት ወደ ጉምሩክ ክልል እንዲገባ ማድረግ ነው፡፡

11/ **"Import"** means to cause the entry of goods or services into customs territory;

፲፪/ **"ዕቃ ወደ ውጪ ሀገር መላክ"** ማለት ማናቸውንም ዕቃ ወይም አገልግሎት ከጉምሩክ ክልል ወይም ከልዩ ኢኮኖሚ ዞን ማስወጣት ወይም ከአንዱ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ወደ ሌላ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ወይም በልዩ የኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ከአንድ ተጠቃሚ ወደ ሌላ ተጠቃሚ እንዲተላለፍ ወይም እንዲወጣ ማድረግ ነው፡፡

12/ **"Export"** means to cause the exit of goods or services from a customs territory or a special economic zone, or the transfer of goods and services from one special economic zone to another zone, or from one special economic zone end-user to another special economic zone end-user;

፲፫/ **"የጉምሩክ ቁጥጥር"** ማለት የሀገሪቱን የጉምሩክ ሕግ ለማስከበር የሚወሰድ እርምጃ ነው፤

13/ **"Customs Control"** means measures applied to ensure compliance with customs laws of the country;

https://t.me/customsclearingagents

https://t.me/customsclearingagents

፲፬/ "የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ" ማለት የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ዲዛይን የማድረግ፣ የመገንባት፣ ፋይናንስ የማድረግ፣ ወይም በባለቤትነት የመያዝ ስራ ላይ እንዲሰማራ በዚህ አዋጅ መሰረት ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ነው፤

፲፭/ "የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ንዑስ-አልሚ" ማለት የተወሰነ የልዩ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ክፍልን ዲዛይን ለማድረግ፣ ለመገንባት፣ ፋይናንስ ለማድረግ፣ ወይም በባለቤትነት ለመያዝ በዚህ አዋጅ እና በንዑስ አልሚ ስምምነት መሰረት ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ነው፤

፲፮/ "የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳዳሪ" ማለት የልዩ ኢኮኖሚ ዞንን በዚህ አዋጅ እና በልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳዳሪ ስምምነት መሰረት ለማስተዳደር፣ ለመንከባከብ፣ ለመጠገን፣ አገልግሎት ለመስጠት እና ለማስተዋወቅ በዚህ አዋጅ መሰረት ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ነው፤

፲፯/ "የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት" ማለት በዚህ አዋጅ እና በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት ስምምነት መሰረት በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ትርፍ በሚያስገኝ የኢኮኖሚ እንቅስቀሴ ውስጥ ለመሳተፍ በዞኑ ውስጥ የለማ መሬት ወይም ህንፃ በንዑስ ሊዝ ወይም በኪራይ የያዘ ድርጅት ነው፤

፲፰/ "የአልሚነት ስምምነት" ማለት ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ዲዛይን ለማድረግ፣ ለመገንባት፣ ለማልማት ወይም በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ሌሎች አገልግሎቶችን ለመስጠት በኮሚሽኑ እና በልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው፤

14/ **“special economic zone developer”** means an entity licensed under this Proclamation to engage in the design, construction, finance, or ownership of a special economic zone;

15/ **“Special Economic Zone Sub-Developer”** means an entity licensed under this Proclamation to engage in the design, construction, finance, or ownership of a part of a special economic zone in accordance with this Proclamation and sub-developer agreement;

16/ **“Special Economic Zone Operator”** means an entity licensed under this Proclamation to operate, maintain, repair, service or promote a special economic zone in accordance with this Proclamation and zone operator agreement;

17/ **“Special Economic Zone Enterprise”** means any entity licensed under this Proclamation and possesses a developed land or building within a special economic zone through sub-lease or rent in order to engage in an economic activity for profit in accordance with this Proclamation and an enterprise agreement;

18/ **“Developer Agreement”** means a contract concluded between the Commission and a special economic zone developer to design, construct, develop, or provide other services within a special economic zone;

https://t.me/customsclearingagents
https://t.me/customsclearingagents

፲፱/ **"የንዑስ አልሚነት ስምምነት"** ማለት የልዩ ኢኮኖሚ ዞንን የተወሰነ ክፍል ዲዛይን ለማድረግ፣ ለመገንባት፣ ለማልማት ወይም ሌሎች አገልግሎቶችን ለመስጠት በኮሚሽኑ እና በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ንዑስ አልሚ መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው፤

፳/ **"የአስተዳዳሪነት ስምምነት"** ማለት ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ለማስተዳደር፣ ለመንከባከብ፣ ለማስተዋወቅ ወይም በልዩ የኢኮኖሚ ዞን ውስጥ አገልግሎቶችን ለመስጠት በኮሚሽኑ እና በልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳዳሪ መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው፤

፳፩/ **"የድርጅት ስምምነት"** ማለት በኮሚሽኑ እና በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው፤

፳፪/ **"ዕቃ"** ማለት የተገዙ፣ የተሸጡ ወይም በሰዎች መካከል በሊዝ የሚተላለፉ ሁሉንም ዓይነት ምርቶች፣ ዕቃዎች፣ ሸቀጣ-ሸቀጦች፣ እንስሳት፣ ጓዞች፣ ቁሶች፣ ማእድኖች፣ ግብዓቶች፣ ኦርጋኒክ ንጥረ-ነገሮች፣ ካልቸር፡ እፅዋት፡ ዘር፣ ነዳጅ፣ ማሺነሪ፣ መሳሪያዎች፣ መለዋወጫዎች እና ተመሳሳይ እቃዎች ማለት ነው፤

፳፫/ **"የተተወ ዕቃ"** ማለት ባለቤቱ በዕቃው ላይ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት በመፈጸም እንደማይወስደው በጽሁፍ ለጉምሩክ ኮሚሽን መግለጫ የሰጠበት፣ ወይም በልዩ ዞን አስተዳዳሪ አሰራር መሠረት እንደተተወ የሚቆጠር፣ ወይም በሌላ አግባብ እንደተተወ የተረጋገጠ ዕቃ ነው፤

19/ **"Sub-Developer Agreement"** means a contract concluded between the Commission and a special economic zone sub-developer to design, construct, develop or provide other services in a part of a special economic zone;

20/ **"Operator Agreement"** means a contract concluded between the Commission and a special economic zone operator to operate, maintain, promote, or provide services within a special economic zone;

21/ **"Enterprise Agreement"** means a contract concluded between the Commission and a special economic zone enterprise;

22/ **"Goods"** include all kinds of products, wares, articles, merchandise, animals, baggage, materials, minerals, organic substances, cultures, plants and seeds, fuel, machinery, equipment, spare parts and similar items purchased or sold or leased between persons;

23/ **"Abandoned Good"** means goods in respect of which the owner has notified Customs Commission in writing that it will not collect the goods by performing customs procedures, or goods that are deemed as abandoned according to the procedures of a special economic zone operator, or are confirmed as abandoned through other procedures;

https://t.me/customsclearingagents

፳፬/ **"ማምረት"** ማለት የኢንዱስትሪ ሂደትን በመጠቀም ማንኛውም የማዘጋጀት፣ የመለወጥ፣ የመገጣጠም ወይም የመቀያየር፣ የግብርና ልማት ወይም የማዕድን ፍለጋ እና ልማት፣ ወይም ሂደቶችን በማንዋል፣ ሜካኒካል፣ ኬሚካል፣ ወይም ባዮ-ኬሚካል መንገድ፣ በማቀዝቀዝ፣ በመቁረጥ፣ በማሻሻል፣ በመቀላቀል፣ ቁስን በማውጣት፣ እንደገና በመስራት፣ ወይም በሪኢንጂነሪንግ አሰራር ምርትን ለማምረት፣ ለመፍጠር፣ ለመገጣጠም፣ ለመለወጥ ወይም እቃን ወደ ነበረበት ለመመለስ የሚከናወን ተግባር ነው፤

፳፭/ **"አገልግሎት"** ማለት የመንግሥት ሥራ ተግባራዊ በማድረግ ማእቀፍ የሚቀርብን አገልግሎት ሳይጨምር በየትኛውም ዘርፍ የሚሰጥ ግኡዛዊ ህልውና የሌለው የሚሸጥ አገልግሎት ነው፤

፳፮/ **"ለውጭ ባለሀብት የተከለከሉ ኢንቨስትመንቶች ብሔራዊ ዝርዝር"** ማለት በጉምሩክ ክልል እና በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ለውጪ ኢንቨስትመንት ተሳትፎ ዝግ የሆኑ ዘርፎችን ዝርዝር የያዘ በቦርዱ የሚታተም ማስታወቂያ ነው፤

፳፯/ **"ሀብት"** ማለት መብት ወይም ንብረትነቱ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ተጠቃሚው የሆነ ማንኛውም የሚንቀሳቀስ፣ የማይንቀሳቀስ ወይም የማይዳሰስ ንብረት ነው፤

፳፰/ **"መሬት"** ማለት የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ኢንቨስትመንት እንዲከናወንበት የተሰየመ ማንኛውም መሬት ነው፤

24/ **"Manufacture"** means any formulation, alteration, assembling or processing, or agricultural development, or mine exploration and development, or activity carried out by using industry, and includes processes that make, produce, assemble, transform, or otherwise bring into existence or treat a good, by manual, mechanical, chemical or bio-chemical methods, refrigeration, cutting, polishing, blending, beneficiation, remaking and re-engineering;

25/ **"Service"** means an intangible**,** tradable act including service in any sector except services provided in the exercise of governmental authority;

26/ **"National Negative List of Foreign Investments"** means a bulletin published by the Board consisting of sectors closed to foreign investment within the customs territory and in special economic zones;

27/ **"Asset"** means any movable or immovable property or intangible property rights and interests belonging to special economic zone end-user;

28/ **"Land"** means land designated for purposes of carrying out special economic zone investment;

https://t.me/customsclearingagents
https://t.me/customsclearingagents

፳፱/ **"የለማ መሬት"** ማለት አስፈላጊ መሰረተ-ልማቶች የተሟሉለት መሬት ነው፤

፴/ **"ሊዝ"** ማለት የልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬት የመጠቀም መብት የሚገኝበት የመሬት ይዞታ ስሪት ውል ነው፤

፴፩/ **"ንዑስ ሊዝ"** ማለት የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ ወይም ንዑስ አልሚ በምደባ፣ በሊዝ ወይም በንዑስ ሊዝ የወሰደውን የለማ ወይም ያልለማ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬት ክፍል ለድርጅት ወይም ሌላ ተጠቃሚ በውል ስምምነት ማስተላለፍ ነው፤

፴፪/ **"ማልማት መጀመር"** ማለት እንደአግባብነቱ፡-

ሀ) የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ ሲሆን እንደ መንገድ፣ ውሀ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ ስልክ፣ የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ አገልግሎት፣ እንዲሁም የህንፃዎችን ግንባታ የመሰረት ሥራ መጀመር፣ ወይም

ለ) የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት ሲሆን በልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬት ላይ በፀደቀው ዲዛይን መሰረት ለመስራት ከተፈቀደው ግንባታ ወይም ሕንፃ ቢያንስ የመሰረት ሥራ ማጠናቀቅ ነው፡፡

፴፫/ **"የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ነዋሪ"** ማለት በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ እንዲኖር በኮሚሽኑ ፈቃድ የተሰጠው የተፈጥሮ ሰው ነው፤

29/ **"Developed Land"** means land furnished with essential infrastructure;

30/ **"Lease"** means a contract regarding land tenure by which a right of use of special economic zone land is acquired;

31/ **"Sub-Lease"** means the contractual transfer of a parcel of developed or undeveloped special economic land which the developer or sub-developer acquires through allocation, lease or sub-lease to an enterprise or other end-user;

32/ **"Commencement of Development"** means, depending on the context:

a) in case of a special economic zone developer, the beginning of construction of foundation works of infrastructure such as road, water, power, telephone, dry and liquid sewerage treatment facilities, as well as foundation work of buildings; or

b) in case of special economic zone enterprise, the completion of at least the foundation of a structure or building on special economic zone land in accordance with the approved design;

33/ **"Special Economic Zone Resident"** means a natural person granted a certificate of residence by the Commission to reside within a special economic zone;

https://t.me/customsclearingagents

https://t.me/customsclearingagents

፴፬/ "የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ተጠቃሚ" ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ስራዎችን የሚያከናውን አልሚ፣ አስተዳዳሪ፣ ድርጅት፣ ሰራተኛ፣ ነዋሪ ወይም ማንኛውም ሌላ አካል ነው፤

፴፭/ "ኮርፖሬሽን" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፳፮/፪ሺ፯ መሰረት የተቋቋመው የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ነው፤

፴፮/ "የመሬት ባንክ ይዞታ" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፳፮/፪ሺ፯ አንቀፅ ፭(፪) መሰረት ከክልል አስተዳደሮች ለኮርፖሬሽኑ የተላለፈ መሬት ነው፤

፴፯/ "በክልል አስተዳደር የተመደበ መሬት" ማለት ለልዩ ኢኮኖሚ ዞን ልማት ስራ እንዲውል በክልል ወይም ከተማ አስተዳደሮች በቀጥታ አልሚ ለሚሆን አካል የተመደበ፣ የኮርፖሬሽኑ የመሬት ባንክ ይዞታ ስርዓት ክፍል ያልሆነ መሬት ሲሆን፣ የስያሜ ማመልከቻ ቀርቦበት ቦርዱ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የመሬት ክፍል ምደባ እና ቁጥጥርን ጨምሮ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ህጉ ሙሉ ለሙሉ ተፈፃሚ የሚሆንበት መሬት ነው፤

፴፰/ "የኢንቨስትመንት አዋጅ" እና "የኢንቨስትመንት ደንብ" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹/፪ሺ፲፪ እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር ፬፻፸፬/፪ሺ፲፪ ነው፤

34/ **"Special Economic Zone End-User"** means a developer, operator, enterprise, employee resident or other entity who undertakes activities within a special economic zone in accordance with this Proclamation;

35/ **"Corporation"** means the Industrial Parks Development Corporation established pursuant to Council of Ministers Regulation No.326/2014;

36/ **"Land Bank Plot''** means land transferred to the Corporation by regional administrations in accordance with Article 5(2) of the Council of Ministers Regulation No.326/2014;

37/ **"Land Allocated by Regional Administration''** refers to all such land which does not form part of the Corporation's land bank system, but is directly allocated by regional or city administrations to potential economic zone developer in respect of which the special economic zone laws, including plot allocation and regulation, apply in entirety once an application for designation is submitted and a decision is issued by the Board;

38/ **"Investment Proclamation"** and **"Investment Regulation"** means, respectively, the Investment Proclamation No.1180/2020 and Council of Ministers Investment Regulations No.474/2020;

https://t.me/customsclearingagents

፴፱/ "መንግሥት" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያ ሪፐብሊክ መንግስት ነው፣

፵/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀፅ ፵፯ መሰረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን፣ ለዚህ አዋጅ ዓላማ የድሬዳዋ እና አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፤

፵፩/ "ቦርድ" ማለት በኢንቨስትመንት አዋጅ እንደገና የቋቋመው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ ነው፤

፵፪/ "ኮሚሽን" ማለት በኢንቨስትመንት አዋጅ እንደገና የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ነው፤

፵፫/ "አግባብነት ያለው አካል" ማለት የልዩ ኢኮኖሚ ዞንን በሚመለከቱ የተወሰኑ ጉዳዮች ወይም መልክዓ-ምድራዊ ቦታዎች ላይ የቁጥጥር ሥልጣንና ኃላፊነት ያለው የፌዴራል፣ የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር አካል ነው፤

፵፬/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፵፭/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

፫. <u>ተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ ማንኛውም ልዩ የኢኮኖሚ ዞን፣ ከልዩ ኢኮኖሚ ዞን ጋር ተያይዞ በሚሰሩ ስራዎች፣ እንዲሁም በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ወይም ከልዩ ኢኮኖሚ ዞን ጋር በተገናኘ ማንኛውንም ሥራ በሚሠራ ሰው ሁሉ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

39/ **"Government"** means the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

40/ **"Region"** means any state established under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, and for purposes of this Proclamation includes Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

41/ **"Board"** means the Ethiopian Investment Board re-established under the Investment Proclamation;

42/ **''Commission''** means the Ethiopian Investment Commission re-established under the Investment Proclamation;

43/ **"Appropriate Authority"** means an organ of the federal, regional or city administration having regulatory powers and duties over particular subject matters or geographic areas relating to special economic zones;

44/ **"Person"** means any natural or juridical person;

45/ any expression in masculine gender also applies to feminine gender.

**3. <u>Scope of application</u>**

This Proclamation shall apply in the territory of Ethiopia to all special economic zones, activities undertaken in connection with special economic zones, as well as to any person conducting any activity within or in relation to special economic zones.

https://t.me/customsclearingagents

## ፬. ዓላማዎች

ይህ አዋጅ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፡

፩/ የግል ዘርፉ በአምራች ኢንዱስትሪ፣ በግብርና፣ በንግድ፣ በአገልግሎት እና ሌሎች ልማታዊ ኢንቨስትመንቶች ላይ እንዲሳተፍ ማበረታታት፣

፪/ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለመሳብ፣ የኢኮኖሚ ክላስተሮችን ለመፍጠርና ለማስተዋወቅ፣ የስራ ዕድሎችን ለመፍጠር፣

፫/ የወጪ ንግድ አፈጻፀምን ማሳደግ፣ የገቢ ንግድ ዕቃዎችን በሀገር ውስጥ ምርቶች የመተካት አቅም ማሳደግ፣ የኋልዮሽና የፊትዮሽ ትስስርን ማጠናከር፣ በዓለማቀፍ የንግድ ሰንሰለት የሚኖር ቁርኝትን ማስፋፋት እና ዘላቂ ዕድገት ማምጣት፣

፬/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የኢንቨስትመንት እና የንግድ ከባቢ ሁኔታን ቅልጥፍና እና አመቺነትን የሚያሻሽል የኢኮኖሚ ሪፎርም መተግበር፣ ኢትዮጵያን በቀጠናዊ፣ በአህጉራዊ እና ዓለማቀፍ ንግድ እና የገቢያ ትስስር ውጤታማ በሆነ መንገድ ተወዳዳሪ ለማድረግ የሚያስችል አቅም የሚያጠናክር ሁሉን አቀፍ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስርአት መዘርጋት፤

፭/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስያሜ፣ ልማት፣ አስተዳደር እና ቁጥጥርን የሚመራ፣ እንዲሁም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ተጠቃሚዎች እንቅስቃሴ፣ መብት እና ግዴታዎችን የሚያቋቁም የሕግ ማእቀፍ መዘርጋት፡፡

## 4. Objectives

This Proclamation shall have the following objectives:

1/ encourage private sector participation in manufacturing, agriculture, trade, services and other productive investments;

2/ attract foreign direct investment, create and promote economic clusters, create decent jobs;

3/ enhance export performance, strengthen national capacity in import substitution, build backward and forward linkage, increase integration into global value chains, and generate sustainable growth;

4/ provide within special economic zones a robust policy framework for experimenting deeper economic reforms that improve the efficiency and conduciveness of the investment and business environment; deploy a comprehensive special economic zone regime that strengthens Ethiopia's capacity to effectively compete in regional and international trade and global value chains;

5/ establish a regulatory framework that guides the designation, development, operation, and regulation of special economic zones, and institutes the activities, rights and obligations of special economic zone end-users.

https://t.me/customsclearingagents

## ክፍል ሁለት

## ስለ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን አሰያየም

**፭. ልዩ የኢኮኖሚ ዞን እንዲሰየም ስለሚያመለክቱ አካላት**

፩/ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ማናቸውም የግል ባለሀብት፣ ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው ክልላዊ ወይም የፌዴራል መንግስት አካል፣ ወይም የመንግስት-የግል ልማት አጋርነት በሚያቀርበው ማመልከቻ መሰረት በቦርዱ ይሰየማል።

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም አመልካች የአልሚነት መብት የሚኖረው አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የተቋቋመ ድርጅት ሲሆን ብቻ ነው፡፡

**፮. የልዩ የኢኮኖሚ ዞን ስያሜ ማመልከቻ ስለሚያሟላቸው ሰነዶች**

፩/ የሚከተሉት ሰነዶች ከማመልከቻ ጋር ተያይዘው ለኮሚሽኑ መቅረብ አለባቸው፡ ሰነዶቹ አጥጋቢ በሆነ ደረጃ የተሟሉ መሆናቸውን መረጋገጥ አለበት፤

ሀ) የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ፕሮጀክቱ የኢኮኖሚ እና ንግድ አዋጭነት ጥናት፣

ለ) የስራ እድል ፈጠራ አቅም፣

ሐ) የዕውቀት፣ ክህሎት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር አቅም፣

መ) የወጪ ንግድን የማጠናከር ወይም የገቢ ንግድ እቃዎችን የመተካት አቅም፣

ሠ/ የኋልዮሽ እና የፊትዮሽ ትስስር፣

## PART TWO

## DESIGNATION OF SPECIAL ECONOMIC ZONE

**5. Entities that Submit Application for Designation of a Special Economic Zone**

1/ A special economic zone shall be designated by the Board based on an application submitted by a private investor, or pertinent regional or federal government entity, or public-private development partnership.

2/ The stipulation of Sub-Article (1) of this Article notwithstanding, an applicant will acquire a developer's right only when a company is duly constituted in accordance with the pertinent legislation.

**6. Documentary Requirements of Special Economic Zone Designation Application**

1/ The following documents shall be presented to the Commission along with the application. It shall be ensured that the documents are complete to a satisfactory extent;

a) economic and commercial feasibility study of special economic zone project;

b) job creation potential,

c) transfer of knowledge, skill and technology potential,

d) potential to increase export or substitute import products,

e) backward and forward linkages,

https://t.me/customsclearingagents
https://t.me/customsclearingagents

ረ) ዞኑ ለተፈጥሮ ሀብቶች፣ ለህዝብ ማእከላት እና መሰረተ-ልማቶች ያለው ቅርበት፣ እንዲሁም ፕሮጀክቱን ለማካሄድ የሚያስችል የመንገድ እና የሀይል አቅርቦት፣ ወይም ይህ ባልሆነ ጊዜ መሰረተ ልማቶች በቀጣይ የሚሟሉ ስለመሆኑ ከሚመለከተው ተቋም የጽሑፍ ዋስትና፣

ሰ) እንደ ኢንቨስትመንቱ ባህርይ የውሀ ጥናት ውጤት እና ውሀ ስለመኖሩ ማረጋገጫ፣

ሸ) ስልታዊ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ፣ የማህበራዊ እና አካባቢያዊ ተፅእኖ ግምገማ እና የአካባቢ አያያዝ እቅድን አስመልክቶ አግባብነት ካለው የፌደራል ወይም የክልል አካል ለፕሮጀክቱ ይሁንታ የተሰጠ ስለመሆኑ ማረጋገጫ፡ እንዲሁም የፕሮጀክቱ ማህበራዊ አካታችነት እና ዘላቂ ማህበራዊ ተጠቃሚነት ዓላማዎችን አስመልክቶ ጥቅል እቅድ፣

ቀ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሸ) ድንጋጌ ቢኖርም አልሚው ስልታዊ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ፣ የማህበራዊ እና አካባቢያዊ ተፅእኖ ግምገማ እና የአካባቢ አያያዝ እቅድ ስያሜ ከተሰጠው በኋላ ባሉት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ይችላል፡፡

በ) በጊዜ የተገደበ እና ግልፅ አመላካች ምእራፎች ያሉት የልዩ ኢኮኖሚ ልማት እቅድ፣

f) proximity to resources, population centers and infrastructure, including road and power necessary for pursuing the project, or failing such, written guarantees from the appropriate authority that such infrastructure will be availed,

g) depending on the investment's nature - a hydrological study and proof of water availability,

h) proof of strategic environmental impact assessment, social and environmental impact assessment report and environmental management plan clearance issued in respect of the project by the appropriate federal or regional authority, as well as a generic plan regarding social inclusiveness and sustainable social benefit objectives of the project,

i) the stipulation of Sub-Article (1)(g) of this Article notwithstanding, the developer may submit proof of strategic environmental impact assessment, social and environmental impact assessment report and environmental management plan within six months of after a designation decision is taken,

j) a time-bound and milestone-based special economic zone development plan,

https://t.me/customsclearingagents
https://t.me/customsclearingagents

ተ) በሚለማው መሬት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ እና መሬቱ ልማቱን ከሚገድብ ማናቸውም ነገሮች ነፃ ስለመሆኑ ማስረጃ፣ ወይም የዞን ስያሜው በቦርዱ ቢፀድቅ የሚለማውን መሬት በተመለከተ ለአመልካቹ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የሚሰጥ ስለመሆኑ መሬቱ ከሚገኝበት ክልል ካቢኔ ወይም ተመሳሳይ ከፍተኛ የመንግስት መዋቅር የማረጋገጫ ደብዳቤ፣ እና

ቸ/ የታሰበው ፕሮጀክት የሚተገበርበት አካባቢ የመሬት አጠቃቀም ማስተር ፕላን ያለው እንደሆነ ከፕላኑ ጋር የተጣጣመ መሆኑን የሚያስረዳ ከሚመለከተው አካባቢያዊ መስተዳድር የሚሰጥ ማስረጃ፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ ሌሎች ለልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስያሜ አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶችን በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ለንዑስ አልሚ ማመልከቻም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

፯. **ባለብዙ ዘርፍ ወይም ባለ አንድ ዘርፍ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ስለመሰየም**

፩/ አንድ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን የኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የንግድ ቀጠና፣ የሎጂስቲክስ ፓርክ፣ እና/ወይም ሌላ የአገልግሎት ዘርፍ ኢንቨስትመንት በተቀናጀ ሥርዓት የሚከናወንበት ባለብዙ ዘርፍ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ተብሎ ሊሰየም ይችላል።

፪/ ባለ አንድ ዘርፍ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን በንግድ ቀጣና፣ ወይም በኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ወይም የግብርና ዞን፣ ወይም በአገልግሎት ፓርክ፣

k) proof of title over the proposed land and clearance from any encumbrance, or a guarantee letter from the regional cabinet or analogous higher governance structure of the area in which the land is located confirming that the applicant will be issued with a holding title over the land within six months should the Board approve the designation, and

l) where the project implementation area has a land use master plan, proof of compatibility of the proposed project with local land use master plan issued by the pertinent local administration.

2/ Without prejudice to the stipulations of Sub article (1) of this Article, the Board may, through a Directive, establish additional conditions required for designation of a special economic zone.

3/ The stipulations of Sub-Article (1) of this Article shall apply, mutatis mutandis, to a sub-developer application.

7. **Designation of multi-purpose or uni-purpose economic zone**

1/ A special economic zone may be designated as a multi-purpose site where industrial park, trade zone, logistics park and/or other service sector investment is conducted under a unified regime.

2/ A special economic zone may be designated as as a uni-purpose site where an investment focuses solely on activities pertinent to a free trade zone, or industrial park, or agriculture,

https://t.me/customsclearingagents
https://t.me/customsclearingagents

ወይም በሌላ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስራ ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገ ኢንቨስትመንት የሚከናወንበት ባለ አንድ ዘርፍ ዞን ተደርጎ ሊሰየም ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሰረት የሚሰየም ባለ አንድ ዘርፍ እና ባለ ብዙ ዘርፍ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን የዞን-አቀፍ ስፓሻል ልማት እቅድ መሠረት መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

፬/ ቦርዱ በማንኛውም ጊዜ ወይም ባለአንድ ዘርፍ የስያሜ ማመልከቻ ጋር በተያያዘ የመንግስትን የፖሊሲ ፍላጎት በማጣቀስ እና የራሱን መለኪያዎች በማውጣት ማናቸውም ልዩ ኢኮኖሚ ዞን በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ እንዲቋቋም ሊወስን ይችላል፡፡ ለዚህ አላማ ሀገር-አቀፍ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ልማት ስፓሻል ልማት እቅድ እንዲኖረው እና ተገቢው መሰረተ ልማት በእቅድ በተመራ መልኩ እንዲዘረጋ ያደርጋል፡፡

፰. **<u>የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስያሜ ማሻሻያ ማመልከቻ</u>**

፩/ ማናቸውም የኢንቨስትመንቱን አይነት ወይም ባህርይን በመሰረታዊነት የሚቀይር የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ማሻሻያ ስያሜ በቦርዱ ይወሰናል።

፪/ የነባር ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ማስፋፊያ ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ቦርዱ አዲስ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስያሜ ጥያቄ ሲቀርብ የሚስተናገድበትን ሂደት እና ቅድመ-ሁኔታዎችን በመከተል ሊሰይም ይችላል።

፱. **<u>የኖረ የኢንቨስትመንት ድርጅትን ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስለማሳደግ</u>**

፩/ ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ደረጃ ለማደግ የወሰነ ማንኛውም የኢንቨስትመንት ድርጅት ለኮሚሽኑ ማመልከት ይችላል።

or service park, or any other zone activity.

3/ A multi-purpose or uni-purpose special economic zone designated pursuant to Sub-Articles (1) and (2) of this Article must be according to a zone-wide spatial development plan.

4/ The Board may, at any time or in relation to any specific designation application, decide to articulate the government's policy preference and formulate its own standards to determine that a special economic zone shall be established only in certain geographical areas. For such purpose, the Board shall adopt a national special economic zone spatial development plan and a scheme for planned development of the appropriate infrastructure.

8. **<u>Modification of Special Economic Zone Designation</u>**

1/ The designation of any modification of a special economic zone that significantly affects the type or nature of its investment shall be determined by the Board.

2/ Where an expansion project of an existing special economic zone is initiated, the Board may issue a designation decision following the same procedure and conditions applied in respect of a new application for designation.

9. **<u>Upgrading an Existing Enterprise into a Special Economic Zone</u>**

1/ An existing company that intends to be upgraded into a special economic zone can apply to the Commission.

https://t.me/customsclearingagents

፪/ በዚህ አዋጅ እና በማስፈፀሚያ ሕግ ላይ የተመለከቱ፡ አነስተኛ የስያሜ መስፈርቶች እና ስነ-ስርአቶች በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ላይ ለተመለከተ ማመልከቻም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፲. **<u>የነባር ኢንዱስትሪ ፓርኮች የልዩ ኢኮኖሚ ዞንነት ስያሜ</u>**

፩/ ማናቸውም ነባር የኢንዱስትሪ ፓርክ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ደረጃ ለማግኘት የስያሜ ማመልከቻ ማቅረብ ወይም የስያሜ ሂደትን ማለፍ አይጠበቅበትም፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የኢንዱስትሪ ፓርኩ ጥያቄ የኢንቨስትመንቱን አይነት ወይም ባህርይ መሰረታዊ በሆነ መልኩ ማስፋፋትን ወይም ተጨማሪ መሬት ማግኘትን የሚያካትት ከሆነ በስያሜ ሂደት ማለፍ ይኖርበታል።

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ነባር የኢንዱስትሪ ፓርኩ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስያሜ በሚያገኝበት ወቅት ስልታዊ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ፣ የማህበራዊና አካባቢያዊ ተጽዕኖ ግምገማ እና የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ ያልነበረው ከሆነ በሚመለከተው አካል የጸደቀ ሰነድ ስያሜ ባገኘ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ነባር የኢንዱስትሪ ፓርክ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስያሜ ቢያገኝም ለልማት፡ ሥራ ወሳኝ የሆኑ መሰረተ ልማቶች በአጥጋቢ ደረጃ መሟላታቸው መረጋገጥ ይኖርበታል። ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

2/ The designation criteria and procedures provided for under this Proclamation and its executive instruments shall apply to an application specified under sub-article (1) of this Article.

10. **<u>Designation of Existing industrial Parks as Special Economic Zone</u>**

1/ An existing industry park shall not be required to submit a designation application or undergo designation procedures to attain a special economic zone status.

2/ The stipulation under Sub-Article (1) of this Article notwithstanding, when an industrial park intends to engage in major expansion of the type or nature of its investment or involves in the acquisition of additional land, its request shall undergo designation procedures.

3/ Without prejudice to the stipulation of Sub-Article (1) of this Article, where, at the time of the transition to a special economic zone status, the industrial park does not possess strategic environmental impact assessment, environmental and social impact assessment, and environmental management plan, it must submit such documents approved by the appropriate authority within six months of its designation.

4/ Without prejudice to the stipulation of Sub-Article (1) of this Article, an industrial park must satisfactorily prove the availability of land and other critical infrastructure required for development though designated as a special economic zone. The details shall be provided in a Directive to be issued by the Board.

https://t.me/customsclearingagents

## ፲፩. አነስተኛ ካፒታል

፩/ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን እንዲሰየምለት የጠየቀ አመልካች በወቅቱ የምንዛሪ ዋጋ ቢያንስ ከሰባ አምስት ሚሊዮን (፸፭ ሚሊዮን) የአሜሪካ ዶላር ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ካፒታል ያለው መሆን አለበት፡፡

፪/ ጠቅላላው ካፒታል በማስረጃ በተረጋገጠ የገንዘብ መዋጮ፣ የአገልግሎት መስጫ መሳሪያ፣ ህንጻ፣ የሥራ ማስኬጃ ካፒታል፣ በብድር ዋስትና፣ ወይም በማናቸውም ተመሳሳይ መንገድ ፋይናንስ ሊደረግ የሚችል ሆኖ፣ በዞኑ ልማት እና ፋይናንስ እቅድ መሰረት በአግባቡ የተደለደለ፡ ከዞን ስያሜ ማመልከቻ ጋር አብሮ የሚገባ እና በቦርዱ የሚፀድቅ መሆን አለበት።

፫/ አነስተኛ ካፒታልን በተመለከተ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተመለከተው ቢኖርም ቦርዱ በውስን ሁኔታዎች የዘርፉን ልዩ ባህርይ ግምት ውስጥ በማስገባት መስፈርቱን በመመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል።

፬/ ጠቅላላ ካፒታልን በተመለከተ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ የተደነገገው ቢኖርም በተረጋገጠ ገንዘብ ፋይናንስ የሚደረገው የካፒታሉ አነስተኛ መጠን ምን ያህል መሆን እንደሚኖርበት ቦርዱ በመመሪያ ይወስናል።

## ፲፪. በስያሜ ማመልከቻ ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ

፩/ ኮሚሽኑ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስያሜ ማመልከቻ ሲቀርብለት ማመልከቻውን በተቀበለ በአምስት ተከታታይ ቀናት ውስጥ የተሟሉ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ አለበት። ማመልከቻው ያልተሟላ ከሆነ ይህንኑ ገልጾ ለአመልካቹ በፅሁፍ መመለስ አለበት።

## 11. Minimum capital

1/ An applicant for designation of a special economic zone must commit a minimum equivalent exchange of Seventy-Five Million (75,000,000) US Dollars as capital.

2/ The capital may be financed through proven cash contribution, machinery, building, working capital, debt financing, or any similar model, and appropriately allocated based on the zone's development and financial plans submitted under the designation application and approved by the Board.

3/ The stipulation of Sub-Article (1) of this Article notwithstanding, the Board may, in exceptional circumstances and based on a sector's unique features, qualify the minimum capital through a Directive.

4/ In respect of sources of capital, the stipulation of Sub-Article (2) of this Article notwithstanding, the Board may, through a directive, determine the minimum monetary investment that must be evidenced by the applicant as part of the capital.

## 12. Decision on Designation Application

1/ The Commission shall, within Five consecutive days of receipt of an application for designation of a special economic zone, verify whether the documents are complete. Where the application is incomplete, it shall notify the applicant in writing.

https://t.me/customsclearingagents
https://t.me/customsclearingagents

፪/ ኮሚሽኑ ማመልከቻው ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት ሰላሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ መርምሮ አስተያየቱን ለቦርዱ ማቅረብ አለበት።

፫/ ቦርዱ በቀረበው ማመልከቻ ላይ ኮሚሽኑ የሚሰጠውን አስተያየት መሰረት በማድረግ በሰላሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ይወስናል።

፬/ ኮሚሽኑ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት ተከታታይ ቀናት ውስጥ የቦርዱን ውሳኔ እና ማብራሪያ ለአመልካቹ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት።

፭/ የስያሜ ማመልከቻ ተቀባይነት አለማግኘት አመልካቹ ወደ ፊት በተመሳሳይ ወይም ሌላ መሬት ወይም ኢንቨስትመንት ሃሳብ ላይ ማመልከቻ ከማቅረብ የሚከለክለው አይሆንም።

## ክፍል ሶስት

## የቦርዱ እና የኮሚሽኑ ስልጣንና ኃላፊነት

### ፲፫. የቦርዱ ተግባርና ኃላፊነት

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነቶች አሉት፤

፩/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስያሜ፣ መቋቋም፣ ልማት፣ አስተዳደር፣ ቁጥጥር እና ተቋማዊ ግንባታን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች እና ሕጎችን በተመለከተ ስትራቴጂክ አመራር እና ውሳኔዎችን መስጠት፣

፪/ ይህን አዋጅ እና አዋጁን ተከትሎ የሚወጣውን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስችሉ መመሪያዎችን ማውጣት፣

፫/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞንን የሚመለከቱ ህጎች ተፈፃሚነትን መቆጣጠር፣

2/ The Commission shall, within Thirty consecutive days of receipt of the application, assess the application and submit its assessment to the Board.

3/ The Board shall, based on recommendation of the Commission, issue its decision within Thirty consecutive days.

4/ Within Five consecutive days after a decision, the Commission shall in writing notify the applicant the Board's decision and the explanations thereof.

5/ A rejection of a designation application shall not preclude the applicant from re-submitting another application with regard to the same or different land or investment proposal.

## PART THREE

## POWERS AND DUTIES OF THE BOARD AND COMMISSION

### 13. Powers and Duties of the Board

The Board shall have the following powers, duties and responsibilities:

1/ provide strategic guidance and decisions in respect of policy and laws pertaining to designation, establishment, development, operation, regulation and institution building of special economic zones;

2/ issue Directives necessary for implementation of this Proclamation and Regulation issued hereunder;

3/ oversee the implementation of special economic zone laws;

https://t.me/customsclearingagents

https://t.me/customsclearingagents

፬/ የሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት በልዩ ኢኮኖሚ ዞን የአንድ ማዕከል አገልግሎት እንዲያቀርቡ መመሪያ መስጠት፣

፭/ ከልዩ ኢኮኖሚ ዞን ጋር በተያያዘ የኮሚሽኑን እና ሌሎች አካላት ስራዎች መከታተል፣ በአንድ ማዕከል ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶች ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዙ እንዲሁም የተናበቡና ቅንጅታዊ አሰራር የተረጋገጠላቸው መሆኑን መከታተል፣

፮/ ለልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚዎች፣ አስተዳዳሪዎች እና ድርጅቶች ተፈፃሚ የሚሆኑ ዝርዝር የኢንቨስትመንት መስፈርቶችን እና ሁኔታዎችን መወሰን፤

፯/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ግንባታ፣ ፕላን፣ የመሬት ምደባ እና አጠቃቀም፣ የመሬት ልማት አሰራር፣ የመሰረተ-ልማቶች አቅርቦት፣ እና የፋሲሊቲ አጠቃቀም እና ዝግጁነትን የሚመለከቱ መስፈርቶች እና ደረጃዎችን ማውጣት፣

፰/ ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ከሌሎች ኢኮኖሚ ዞን ሥርዓቶች ጋር የሚኖራቸውን ዓለም-አቀፋዊ ተወዳዳሪነት ለማሳደግ የሚያስችል ጠቅላላ የዞን ፕላን አሰራር ማፅደቅ፣

፱/ ኮሚሽኑ በሚያቀርበው ምክረ-ሀሳብ መሰረት ልዩ የኢኮኖሚ ዞን እንዲሰየም፣ የተሰየመ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን እንዲሻሻል፡ ወይም ስያሜው እንዲሰረዝ መወሰን፣

፲/ ኮሚሽኑ ወይም ሌላ የመንግስት አስፈፃሚ አካል የሰጠውን የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ በመቃወም በልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ፣ አስተዳዳሪ፣ ድርጅት ወይም የዞን ሌላ አካል በሚቀርብ ቅሬታ ላይ መወሰን፣

4/ instruct pertinent government agencies to deploy services within the one stop service system of special economic zones;

5/ follow-up activities of the Commission and other entities in relation to special economic zones; ensure and follow up that one stop services organized within special economic zones are efficient, effective, technology-based, harmonized and coordinated;

6/ determine details of investment criteria and conditions applicable to special economic zone developers, operators and enterprises;

7/ set requirements and standards concerning construction, special economy zone planning, land allocation and uses, earth movement, utilities connection, and facility occupancy and fitness for use as relating to special economic zones;

8/ approve general planning of zones to enhance their international competitiveness with other special economic zone regimes;

9/ based on recommendation by the Commission, approve or reject an application for designation of a special economic zone, amend a designation, or revoke a designation;

10/ decide on complaints submitted by any special economic zone developer, operator, enterprise, or other entity within zones challenging a final administrative decision of the Commission or any other executive entity;

https://t.me/customsclearingagents

፲፩/ ወደ ልዩ ዞን የሚገቡ ማሽኖች ያላቸውን ቴክኖሎጂ በተመለከተ ዘመኑን የዋጁ እና የተፈለገውን ዓላማ ሊያሳኩ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

፲፪/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ላይ የሚሰጡ አገልግሎቶች በኤሌክትሮኒክ በታገዘ መንገድ እንዲሰጡ ማድረግ እና ይህንንም እየተተገበረ መሆኑን ማረጋገጥ፣

## ፲፬. የኮሚሽኑ ተግባርና ኃላፊነቶች

፩/ ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነቶች አሉት፤

ሀ) ልዩ የኢኮኖሚ ዞንን የሚመለከቱ የመንግስት ፖሊሲዎች፣ ህጎች እና ፕሮግራሞችን ማስፈጸም፣

ለ) በልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚነት፣ አስተዳዳሪነት፣ ድርጅትነት የሚሳተፉ ብቃት ያላቸው ባለሀብቶችን በተደራጀ መንገድ መለየትና መመልመል፣ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ኢንቨስትመንት ለማስፋፋት ወይም ለማቆየት የሚያስችል ሁሉን-አቀፍ የድህረ ኢንቨስትመንት ድጋፍ አገልግሎት መስጠት፣

ሐ)ልዩ የኢኮኖሚ ዞን እንዲሰየም የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን መቀበል፣ የቀረቡ ሰነዶች የተሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ የሚሰየሙ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ጥያቄዎችን ማጣራት፣ ውሳኔ እንዲያገኙ ለቦርዱ ምክረ-ሀሳብ ማቅረብ፣ የቦርዱን ውሳኔዎች ማሳወቅ፣

መ) የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅቶች፣ አስተዳዳሪዎች፣ ወይም ሌሎች ተቋማት ፈቃድ ለማግኘት የሚያቀርቧቸውን

11/ ensure that machineries and technology deployed in special economic zones are up-to-date and capable of delivering the intended services; the details shall be issued in a Board Directive;

12/ facilitate and ensure that services provided within special economic zones are assisted and delivered through electronic mechanisms;

## 14. Duties and Responsibilities of the Commission

1/ The Commission shall have the following powers, duties and responsibilities:

a) implement the government's policies, laws and programs with regard to special economic zones;

b) proactively promote and attract productive investors participating as special economic zone developers, operators and enterprises, provide holistic aftercare support to realize investment expansion and retention;

c) receive applications for special economic zone designation, verify completeness of documents, screen and facilitate decision by the Board, inform decisions of the Board;

d) receive applications of special economic zone enterprises, operators and other entities within zones for licensing, screen the same and decide;

https://t.me/customsclearingagents

ማመልከቻዎች መቀበል፣ መመርመር እና መወሰን፣

ሠ) የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ኢንቨስትመንቶችን በተመለከተ ፈቃድ ለመስጠት የሚያስችሉ ቅድመ-ሁኔታዎች እና ደረጃዎችን ማውጣት፣ የሚሰሩት የስራ ዘርፍ በሚመለከታቸው አካላት ቁጥጥር የሚደረግበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የቴሌኮም ድምፅ እና ኢንተርኔት አገልግሎት ድርጅቶች፣ ሆስፒታሎች፣ ክሊኒኮች፣ የመድሀኒት እና የመድሀኒት መሸጫ መደብሮች፣ የጉምሩክ አገናኞች፣ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት፣ የነዳጅ ዘይት እና ጋዝ ድርጅቶች፣ የህግ አገልግሎት፣ የሂሳብ እና ኦዲት አገልግሎት፣ የምህንድስና እና አርኪቴክቸር አገልግሎት፣ ትምህርት ቤቶች፣ መዋዕለ-ህፃናት እና ኢንስቲትዩቶች በልዩ ኢኮኖሚ ዞኖች ውስጥ አገልግሎት እንዲሰጡ መፍቀድ፣

ረ) በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የሚከለከሉ ተግባራትን ዝርዝር አስመልክቶ ለቦርዱ ምክረ-ሀሳብ ማቅረብ፣

ሰ) መንግስት የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ልማትን በተመለከተ በሚከተለው ፖሊሲ እና አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት ለልዩ ኢኮኖሚ ዞን የሚውሉ መሬቶች በአግባቡ መመደባቸው እና መልማታቸውን ማረጋገጥ፣ በልዩ ኢኮኖሚ ዞንነት የሚሰየሙ መሬቶችን ለመለየት፣ ዘርዝሮ ለማመልከት እና ለአልሚዎች ለማቅረብ እንዲቻል ከክልል እና ከተማ አስተዳደሮች ጋር የስራ ግንኙነት መፍጠር፣

e) in respect of investments, set conditions and standards required for the issuance of license, authorize the provision of an occupation or activity within a zone including telecom voice and data service companies, hospitals, clinics, pharmacies and pharmaceutical companies, customs brokers, air transportation services, oil and gas companies, legal services, accounting and audit services, engineering and architectural services, schools, nurseries, institutes - provided that their activities shall be regulated by the competent authorities;

f) recommend to the Board a list of activities prohibited within special economic zones;

g) ascertain the orderly allotment and development of special economic zone land, engage with regional and city administrations to identify, map and avail land to developers to be designated as special economic zones in line with the government's policy and pertinent laws on special economic zones development;

https://t.me/customsclearingagents

ሸ) በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የመሬት ክፍሎች አመዳደብን በተመለከተ የወጡ ደንብ እና መመሪያዎችን መፈጸም፣ የመሬት አጠቃቀም አሰራሮችን መመስረት እና ተግባራዊ ማድረግ፣

ቀ) ከልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚዎች አስተዳዳሪዎች እና ድርጅቶች ጋር ስምምነት መፈጸም፣ የኢንቨስትመንት ስራዎቻቸው የሚመሩባቸውን ሁኔታዎች መወሰን፣ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እና ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር የንግድ ፈቃድ መስጠት፣

በ) ልዩ ኢኮኖሚ ዞኖችን መቆጣጠር፣ አግባብነት ያላቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች እና እርምጃዎችን መውሰድ፣ ወይም እንደሁኔታው የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ የኢንቨስትመንት ወይም ንግድ ፈቃድ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ ለቦርዱ ምክረ-ሀሳብ ማቅረብ፣

ተ) የንዑስ ሊዝ፣ የህንፃዎች ሽያጭ ወይም ኪራይ ስምምነቶች በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት እንዲከናወኑ ማድረግ፣ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ተጠቃሚዎች መካከል የሚደረጉ የንዑስ ሊዝ፣ የሽያጭ ወይም ኪራይ የስምምነት ውሎችን ማረጋገጥ፣ እንደተገቢነቱ የንዑስ-ሊዝ ይዞታ የምስክር ወረቀት ወይም የባለቤትነት ካርታ መስጠት፣

ቸ) የልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሰረተ-ልማቶች ሥራ፣ አስተዳደር ወይም ጥገና በፕላን እና በተፈረሙ ስምምነቶች መሰረት እንዲካሄዱ መፍቀድ፣ ለግንባታ እና መሰረታዊ አገልግሎቶች አቅርቦት፣ የመሰረተ-ልማቶች ሥራ፣ ህንፃዎች፣ እና

h) execute regulation and directives on the allocation of land parcels within special economic zone, adopt and implement guidelines for land uses;

i) conclude agreement with special economic zone developers, operators, and enterprises, define conditions of their investment within zones, and issue investment permits and issue business licenses in collaboration with authoritative organ;

j) regulate special economic zones, take appropriate administrative decisions and actions, and as the case may be, recommend to the Board to suspend or revoke the permit or license of a special economic zone developer;

k) ensure sub-lease, building sale or rental agreements are concluded in accordance with the system put in place, verify sub-lease, sale or rental agreements signed between special economic zone end-users, as appropriate issue a sub-leasehold certificate or title deed;

l) approve the development, operation or maintenance of special economic zone infrastructure in accordance with plans and agreements signed, issue permits for the construction of utilities, infrastructure, buildings, and

https://t.me/customsclearingagents

ፋሲሊቲዎች አጠቃቀም ፈቃድ መስጠት፣

ኀ) የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ተጠቃሚዎች መብቶች መከበራቸው፣ ግዴታዎች በአግባቡ መፈፀማቸውን ማረጋገጥ፣

ነ) ከዞን አስተዳዳሪ ጋር በመቀናጀት በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ክልል በመደበኛነት የሚገቡ እና የሚወጡ ስራተኞች ሬጂስተር ማዘጋጀት፡ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎች ሬጂስተር መያዝ፣

ኘ) በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎች ወደ ዞኑ የሚገቡበትን የፈቃድ እና ቁጥጥር ሁኔታ መምራት፣

አ) የልዩ ኢኮኖሚ ዞንን የሚመለከቱ የፖሊሲ ጉዳዮችን ለመለየት የሚያስችሉ ጥናቶችን ማካሄድ፣ በቦርዱ ውሳኔ እንዲያገኙ ማድረግ፣

ከ) በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ለሚካሄዱ የኢንቨስትመንት ስራዎች ሊሰጡ ስለሚገቡ ማበረታቻዎች ሥልጣን ላለው አካል ምክረ-ሀሳብ ማቅረብ፣

ኸ) የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅቶች እና ሌሎች ተጠቃሚዎች ፈቃድ እና መሰል አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች የሚስተናገዱበት እና ውሳኔ የሚያገኙበት የተቀናጀ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ማደራጀት እና ማስተዳደር፣ እንዲሁም አገልግሎቶቹ በኮሚሽኑ በቀጥታ የማይሰጡ ከሆነ ከተቋማት ጋር በመተባበር በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የአንድ ማዕከል አገልግሎት በተቀናጀ መልክ መዘርጋቱ እና በተሟላ መልኩ መሰጠቱን ማረጋገጥ፣ የተሠጡ አገልግሎቶች መረጃ በማዕከላዊ የመረጃ ቋት እንዲያዝ ለማስቻል

facility occupancy;

m) ensure that rights of special economic zone end-users are respected, and obligations properly discharged;

n) in coordination with a zone operator, maintain a register of employees that regularly enter and exit special economic zones, organize a register of residents domiciled within special economic zones;

o) authorize and regulate access of service providing persons to special economic zones;

p) conduct studies to identify policy issues of relevance to special economic zones, cause decisions are taken by the Board;

q) put forward recommendations to the competent authority regarding the incentives granted to investments within special economic zones;

r) organize and administer an efficient one stop service system through which special economic zone enterprises and other end-users channel their applications for permits, approvals, licenses and related services, and where services are not directly handled by the Commission, coordinate with other entities to ensure that one stop services are streamlined and fully deployed within special economic zones; ensure that in respect of delivered services

https://t.me/customsclearingagents

ለሚመለከታቸው መንግስታዊ ተቋማት የተደራጀ መረጃ ማስተላለፍ፣

ሠ) የልዩ ኢኮኖሚ ዞን እቅድ፣ ልማት እና አስተዳደር ሀላፊነቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ከአካባቢ የመንግስት መዋቅሮች ጋር የምክክር እና የቅንጅት አሰራሮችን መመስረት፣

ዐ) በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የግብአቶች ትስስር ሥርዓት መፍጠር፣ ከሀገራዊ ኢኮኖሚው ጋር የኋልዮሽ እና ፊትዮሽ ትስስር የሚፈጠርበትን ትልም መተግበር፣ የቴክኖሎጂ፣ የእውቀት እና የክህሎት ሽግግርን ማሳለጥ፣ ለዚህ ዓላማ ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት ጋር መተባበር፣

ዘ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በልዩ ኢኮኖሚ ዞኑ ተፈጻሚ የሚሆኑ የአካባቢ ጥበቃ መመሪያዎችን፣ የሰራተኛ እና ማህበራዊ ኢንሹራንስ ፖሊሲን የሚመለከቱ አሰራሮች እንዲወጡ ማድረግ፤ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ሰራተኛ ሀይል ቅጥር እና ስልጠናን በተመለከተ የሚመለከታቸውን ተቋማት ማስተባበር፣

ዠ) ሀገራዊ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ፕሮግራምን እና የልዩ ኢኮኖሚ ዞኖች እና የድርጅቶች የስራ አፈፃፀምን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃ መያዝ፣

organized information is conveyed to the pertinent government entities to facilitate retention in a central database;

s) create consultation and coordination procedures with local governance structures to implement duties in relation to the planning, development and operation of zones;

t) create a scheme for linkage of inputs within special economic zones, implement schemes on forward and backward linkages with the national economy, facilitate the transfer of technology, knowledge and skill, and cooperate with the competent authorities to that end;

u) in collaboration with the appropriate authorities, cause the issuance of directives on environmental protection and guidelines on labor and social insurance policies applicable within special economic zones; coordinate the relevant agencies with regard to the recruitment and training of special economic zone workforce;

v) maintain up to date data on the performance of the national special economic zone program and with respect to special economic zones and enterprises;

https://t.me/customsclearingagents

https://t.me/customsclearingagents

የ) በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ በሚገኙ ተጠቃሚዎች፣ እንዲሁም በተጠቃሚዎች እና የመንግስት አካላት መካከል የሚከሰቱ አስተዳደራዊ ቅሬታዎች እና አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚያስችል የቅሬታ አፈታት ሥርዓት ማደራጀት፣

w) organize a complaint handling mechanism to address administrative grievances, help the resolution of disputes arising within special economic zones among end-users, as well as between end-users and government entities;

ደ) የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ተጠቃሚዎችን የመሬት ልማት እና ግንባታ አፈፃፀም፣ የፋብሪካ እና ህንፃ አጠቃቀም፣ የአምራች እና የወጪ ንግድ አፈፃፀም፣ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ሰራተኞች ቁጥር ሁኔታ፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን የያዘ ሪፖርት በየወቅቱ ማዘጋጀት፣ ለቦርዱ እና ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ማቅረብ፣

x) prepare and submit to the Board and other relevant bodies periodic reports pertaining to special economic zone end-users' land development and construction performance, factory and building utilization, manufacturing and export trade performance, employment of domestic and foreign workers, delivery of one-stop-shop services, and other important information;

ጀ) ከሚመለከታቸው የዘርፍ መስሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር አዳዲስ ምርቶች ለማምረት ወይም ነባሩን ለማስፋፋት፣ የተሳለጠ የገቢ እና ወጪ ንግድ፣ እና እሴትን የጨመረ የሎጂስቲክስ ዞን አገልግሎት ለመዘርጋት እንዲቻል እና ኢንቨስተሮች ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞኖች እንዲሳቡ ለማድረግ የሚያግዝ ስትራቴጂ እንዲፀድቅ ማመቻቸት፣

y) in consultation with sectoral ministries, facilitate the adoption of strategies that expand or create new productive capacity, facilitate import-export trade and value-added logistics zone services, and attract investors into special economic zones.

፪/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞኖች የቁጥጥር እና ድጋፍ ሥራዎችን ብዛት፣ ውስብስብነት፣ እና ልዩ ሙያዊ ፍላጎት ፍጹም አስፈላጊ ካደረገው የኮሚሽኑ ተግባርና ሀላፊነቶች ራሱን ችሎ በሚደራጅ ተቋም እንዲከናወኑ ቦርዱ ሊወስን ይችላል።

2/Where the multiplicity, complexity and demand for unique expertise of regulatory and facilitation functions so require, the Board may decide that the Commission's duties and responsibilities be carried out by an agency that is autonomously organized to such effect.

https://t.me/customsclearingagents

https://t.me/customsclearingagents

## ክፍል አራት

## የፈቃዶች አሰጣጥ እና የአንድ ማእከል አገልግሎት

**፲፭. የልዩ የኢኮኖሚ ዞን አልሚ የኢንቨስትመንት ፈቃድ**

፩/ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን የተሰየመለት ማንኛውም ባለሀብት የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ ወይም ንዑስ አልሚ ለመሆን ለኮሚሽኑ በማመልከት ስምምነት መፈራረም እና የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማግኘት አለበት።

፪/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የቀረበው ማመልከቻ መስፈርቶቹን የሚያሟላ ሆኖ ካገኘው ማመልከቻው በቀረበ በሰባት ተከታታይ ቀናት ውስጥ የኢንቨስትመንት ፈቃዱን መስጠት አለበት።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት የሚሰጠው ፈቃድ የልዩ ኢኮኖሚ ዞኑ በውስጡ እንዲያደራጅ እና እንዲሰራ የተፈቀደውን የዘርፍ አይነት ማመላከት አለበት፡፡

**፲፮. የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳዳሪ የኢንቨስትመንት ፈቃድ**

፩/ ማንኛውም ባለሀብት የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳዳሪ ለመሆን ከኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማግኘት አለበት።

፪/ አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች አሟልቶ ለኮሚሽኑ ማቅረብ ይኖርበታል፡-

ሀ) ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች እና ተያያዥ አገልግሎቶች የመስጠት ልምድ ያለው መሆኑን የሚገልጽ ዝርዝር መግለጫ፣

## PART FOUR

## ISSUANCE OF PERMITS AND ONE STOP SERVICES

**15. Special Economic Zone Developer Investment Permit**

1/ An investor who receives designation of special economy zone shall apply to the Commission, enter into agreement, and secure investment permit as special economic zone developer or sub-developer.

2/ Where the Commission verifies that the application submitted in accordance with Sub-Article (1) of this Article complies with the requirements, it shall issue the investment permit within Seven consecutive days of the submission.

3/ The permit issued in accordance with Sub-Article (2) of this Article shall indicate the sector in which the zone is authorized to establish and operate.

**16. Special Economic Zone Operator Investment Permit**

1/ Any investor must secure an investment permit from the Commission to become a special economic zone operator.

2/ The applicant shall secure an investment permit in accordance with Sub-Article (1) of this Article when it fulfils the following requirements and submits the same to the Commission:

a) declaration demonstrating availability of qualified personnel and experience in rendering related services;

https://t.me/customsclearingagents

ለ) የዞኑ ህንፃዎች እና ፋሲሊቲዎች አስተዳደር፣ አያያዝ፣ ጥገና፣ ማስተዋወቅ፣ የገቢ ምንጮች እና የአሰባሰብ ዘዴዎች፣ እና የኢስክሮ ሂሳብ አደረጃጀትን የሚያሳይ እሴት የታከለበት የአገልግሎት አሰጣጥ እና አስተዳደር ስራዎች እቅድ መግለጫ።

ሐ) በሚመለከተው አካል የጸደቀ የማህበራዊና አካባቢያዊ ተጽዕኖ ግምገማ እና የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ፡፡

፫/ ኮሚሽኑ ማመልከቻው መስፈርቶቹን የሚያሟላ ሆኖ ካገኘው ማመልከቻው በቀረበ በሰባት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የኢንቨስትመንት ፈቃዱን መስጠት አለበት።

፬/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ ወይም ንኡስ አልሚ ያለማውን ዞን ማስተዳደር ከፈለገ የአስተዳዳሪነት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማውጣት አለበት፡፡

**፲፯. <u>የልዩ የኢኮኖሚ ዞን ድርጅት የኢንቨስትመንት ፈቃድ</u>**

፩/ ማንኛውም ባለሀብት የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት ለመሆን ከኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

፪/ አመልካቹ የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ አለበት፡

ሀ) የፕሮጀክት ሀሳብ፣

ለ) የሽያጭ እቅድ፣

ሐ) የድርጅቱ የፋይናንስ ሁኔታ መግለጫ፣

መ) በሚመለከተው አካል የጸደቀ የማህበራዊና አካባቢያዊ ተጽዕኖ ግምገማ እና የአካባቢ

b) administrative and financial plan demonstrating service value proposition and operations plan for zone buildings and facilities management, maintenance, repairs, marketing, revenue streams and collection mechanisms, and escrow account arrangements;

c) social and environmental impact assessment and environmental management plan duly approved by the appropriate entity;

3/ Where the Commission verifies that the application complies with the requirements, it shall issue an investment permit within seven consecutive days of the submission.

4/ A special economic zone developer or sub-developer who seeks to operate its own zone must apply for an operator investment permit.

**17. <u>Special economic zone enterprise investment permit</u>**

1/ Any investor must secure an investment permit from the Commission to become a special economic zone enterprise.

2/ The applicant must submit the following documents:

a) project proposal;

b) sales plan;

c) declaration of financial standing;

d/ social and environmental impact assessment and environmental

https://t.me/customsclearingagents
https://t.me/customsclearingagents

አያያዝ ዕቅድ፡፡

፫/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚቀርብ ማመልከቻ መስፈርቶቹን የሚያሟላ ሆኖ ካገኘው ማመልከቻው በቀረበ በሶስት ተከታታይ ቀናት ውስጥ የኢንቨስትመንት ፈቃዱን መስጠት አለበት፡፡

፲፰. **የንግድ ምዝገባ**

፩/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጠው እና በልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚነት፣ አስተዳዳሪነት ወይም ድርጅትነት መስራት የሚፈልግ ማንኛውም ባለሀብት አግባብነት ባለው የንግድ ህግ የተመለከቱ ሰነዶችን ለኮሚሽኑ በማቅረብ ማመልከት ይኖርበታል፡፡

፪/ ኮሚሽኑ ለአመልካቹ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

፲፱. **የንግድ ስራ ፈቃድ ስለመስጠት**

፩/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ባለሀብት በኮሚሽኑ የንግድ ስራ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር እንደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ፣ ንዑስ አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት የንግድ ስራ መስራት አይችልም።

፪/ የንግድ ፈቃድ ለማግኘት ባለሀብቱ የተዘጋጀውን ፎርም በመጠቀም ለኮሚሽኑ ማመልከት አለበት።

፫/ ኮሚሽኑ በአግባቡ የተሟላ ማመልከቻን ከተቀበለበት እና ክፍያ ከተፈጸመበት እለት አንስቶ ባሉት ሶስት ተከታታይ ቀናት ውስጥ የንግድ ስራ ፈቃድ መስጠት አለበት።

management plan duly approved by the appropriate entity;

3/ Where the Commission verifies that the application submitted in accordance with Sub-Article (1) of this Article complies with the requirements, it shall issue an investment permit within Three consecutive days of the submission.

18. **Commercial registration**

1/ Any investor intending to carry out business as a special economic zone developer, operator or enterprise shall present to the Commission documents specified under the appropriate commercial law.

2/ The Commission shall issue commercial registration certificate to the applicant.

19. **Issuance of business license**

1/ No investor issued with investment permit can carry out a special economic zone developer, sub-developer, operator or enterprise business except in accordance with a business license issued by the Commission.

2/ To receive a business license, an investor must apply to the Commission using a prescribed form.

3/ The Commission shall issue a business license within three consecutive days from the date on which a duly completed application is received and payment of the prescribed fee is effected.

https://t.me/customsclearingagents

https://t.me/customsclearingagents

**፳. <u>ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚሰጥ ፈቃድ</u>**

ተፈፃሚነት ባለው ሕግ መሰረት አግባብነት ባለው የክልል ወይም የፌዴራል መንግስት ተቋም የሚሰጠው ፈቃድ፣ ቁጥጥር እና ክትትል እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ ትምህርት ቤቶች፣ ኢንስቲትዩቶች፣ መዋዕለ-ህፃናት፣ ሆስፒታሎች፣ ክለቦች፣ የሳይንስ፣ የምርምር፣ የህክምና እና የባህል ማዕከላት እና ሌሎች ትምህርታዊ፣ የጤና እና ማህበራዊ ተግባራትን የሚያከናውኑ ተቋማት በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ እንዲቋቋሙ እና ስራ እንዲሰሩ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

**፳፩. <u>የአንድ ማዕከል አገልግሎት</u>**

፩/ ኮሚሽኑ በእያንዳንዱ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፣ ይከታተላል።

፪/ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ሥርዓት የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ተጠቃሚዎች ፈቃድ እና የንግድ ፈቃድ ለማግኘት የሚያስችሉ ማመልከቻዎች የሚያቀርቡበት፣ እንዲሁም የተሳለጠ አገልግሎት የሚያገኙበት ማእከል ሆኖ ይደራጃል።

፫/ ኮሚሽኑ የሚመለከታቸውን ተቋማት ወደ ተቀናጀ መስመር የማምጣት፣ ስራዎቻቸውን የማስተባበር እና የአንድ ማዕከል አገልግሎቱ በተናበበ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ መሰጠቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

፬/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት ያለበት ተቋም ብቃት ያለው ተወካይ በመመደብ በአንድ ማእከል ውስጥ ገብቶ አገልግሎት የመስጠት ወይም በመግባቢያ ስምምነት ኮሚሽኑን በመወከል አገልግሎቱ እንዲሰጥ የማድረግ ግዴታ አለበት፤ ተቋሙ የልዩ ኢኮኖሚ ዞንን ባህርይ እና ፍላጎት ግምት

**20. <u>Permit Issued to Other End-Users</u>**

The Commission shall authorize the physical establishment and operation of schools, institutes, nurseries, hospitals, clubs, scientific, research, medical and cultural centers, and other educational, health and social activities within special economic zones, provided that the activities shall be subjected to licensing, regulation and supervision by the appropriate federal or regional authority in accordance with the applicable law.

**21. <u>One stop service</u>**

1/ The Commission shall set up, administer and supervise one stop services within each special economic zone.

2/ The one stop service platform shall be used by all special economic zone end-users to channel applications for permits and licenses and to obtain facilitation services.

3/ The Commission shall bring into line all competent entities, coordinate their functions, and ensure that one stop services are provided in streamlined and efficient manner.

4/ An entity required to provide service in special economic zone shall have a duty to deliver the services by assigning a qualified representative in the one stop service or by delegating its powers to the Commission through a memorandum of understanding; such entity shall set up a structure and

https://t.me/customsclearingagents

ውስጥ ያስገባ መዋቅር እና የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አለበት።

፭/ ኮሚሽኑ የሚከተሉትን የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች ለልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት ይሰጣል፤

ሀ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠት፣ እድሳት፣ ማሻሻያ፣ ለውጥ ወይም ምትክ መስጠት፣ ወይም የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ፈቃድ መስጠት፣

ለ) የንግድ የምስክር ወረቀት መስጠት፣ ወይም ለውጥ፣ ማሻሻያ ወይም ምትክ መስጠት፣

ሐ) የመመስረቻ ፅሁፍ እና የመመስረቻ ፅሁፍ ማሻሻያዎችን ጨምሮ ሰነዶችን ማረጋገጥ፣

መ) የንግድ ስራ ፈቃድ፣ እድሳት ወይም ምትክ መስጠት፣

ሠ) የንግድ ስም የምስክር ወረቀት ምዝገባ፣ ምትክ፣ ማሻሻያ እና ስረዛ፣

ረ) የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅቶች ማህበር ምዝገባ፣ እድሳት ወይም ስረዛ፣

ሰ) የውጭ ቀጥታ ካፒታል ምዝገባ እና የምዝገባውን የምስክር ወረቀት ቅጂ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማስተላለፍ፣

ሸ) የግንባታ እና አጠቃቀም ፈቃድ መስጠት፣ እድሳት፣

ቀ) የስራ ፈቃድ መስጠት፣ እድሳት፣ ምትክ እና ስረዛ፣

operational procedure tailored to the nature and needs of special economic zones.

5/ The Commission shall provide the following one stop services to a special economic zone developer, operator or enterprise:

a) issuance, renewal, amendment, change or replacement of investment permit, or investment expansion permit;

b) issuance, change, amendment, or substitution of commercial registration certificate;

c) authentication of documents, including memorandum of association and amendments thereto;

d) issuance and renewal of business license, or substitute business license;

e) registration, substitution, amendment, or cancellation of trade name certificate;

f) registration, renewal or revocation of association of special economic zone enterprises;

g) registration of foreign direct capital, send copy of the certificate to the National Bank of Ethiopia;

h) issuance, renewal of construction and use permit;

i) issuance, renewal, replacement and cancellation of work permit;

https://t.me/customsclearingagents
https://t.me/customsclearingagents

በ) ከአሰሪና ሰራተኞች ጋር የተያያዙ ምዝገባዎች፣

ተ) የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ነዋሪ የምስክር ወረቀት መስጠት፣

ቸ) ስልታዊ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ፣ የማህበራዊና አካባቢያዊ ተፅእኖ ግምገማ ጥናትና የአካባቢ አያያዝ እቅድ በሚመለከተው አካል የማስፀደቅ እና ምስክር ወረቀት የመስጠት ስራዎችን ማሳለጥ፣

ኀ) የነዋሪነት ፈቃድ ወይም ቪዛ ወይም እድሳት አሰጣጥን ማሳለጥ፣

ነ) የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅቶችን ታክስ-ነክ እና የወጪ ንግድ ማበረታቻ ምዝገባ ማሳለጥ፣

ኘ) የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ነጻ ተጠቃሚነት እና እቃዎችን ያለውጭ ምንዛሬ የማስገባት ፈቃድ ማሳለጥ፣

አ) የገቢ ግብር እፎይታ ተጠቃሚነት አገልግሎቶችን ማሳለጥ፣

ከ) የቀረጥ እና ግብር እፎይታ መብት ካለው አንድ ድርጅት ተመሳሳይ መብት ወዳለው ሌላ ድርጅት የሚደረግ የእቃዎች ማስተላለፍ ስራን ማሳለጥ፣

ኸ) በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የሚገኙ አሰሪዎች እና ሰራተኞች የታክስ መለያ ቁጥር ለማግኘት እንዲመዘገቡ እና እንዲያገኙ ማመቻቸት፣

ወ) የጉምሩክ አገልግሎትን ማመቻቸት፣

ዐ) ስምምነት መግባት እንደተጠበቀ ሆኖ የባንክ፣ ኢንሹራንስ፣ እቃ ላኪ እና

j) registrations pertaining to employers and workers relations;

k) issuance of special economic zone residency certificate;

l) facilitate approval of strategic environmental impact, social and environmental impact assessment, and environmental management plan, and the issuance of certificates;

m) facilitating the issuance and renewal of visa and residence permits;

n) facilitating the registration of enterprises for tax and export incentives;

o) facilitating the grant of customs duty and tax exemptions, and franco-valuta importation of goods;

p) facilitating the grant of income tax exemptions;

q) facilitating the transfer of construction goods from an enterprise entitled to customs duty and tax exemption to another enterprise possessing the same right;

r) facilitating registration and issuance of tax identification number to employers and employees within special economic zones;

s) facilitation of customs services;

t) subject to agreement, facilitating services relating to banking,

https://t.me/customsclearingagents

አስተላላፊ፣ ጉምሩክ አገናኝ እና ሌሎች አገልግሎቶች አሰጣጥን ማመቻቸት፣

ዘ) ከአሰሪዎች እና ሰራተኞች የጡረታ መዋጮዎች አሰባሰብን ማመቻቸት፣

ዠ) አማራጭ የክርክር መፍቻ መንገዶችን ጭምር በመጠቀም ቅሬታዎችን ማስተናገድ እና አለመግባባቶች እንዲፈቱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

የ) የግብአት-ምርት ጥመርታን በተመለከተ የሚደረጉ ጥናቶችን ማስተባበር፣ መከታተል፣ ደረጃዎች እንዲወጡ ማድረግ፣

፮. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፭) ድንጋጌ ቢኖርም ከኮሚሽኑ የንግድ ምዝገባና የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጠው እና በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ በተለይ በንግድ እና አገልግሎት መስጠት ስራዎች ላይ የሚሰማራ የሀገር ውስጥ ሆነ የውጭ ድርጅት የንግድ ፈቃድ እና ተመሳሳይ ሰነዶችን የመስጠት እና የመቆጣጠር ስራ በንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር አመቻችነት ይከናወናል፡፡

፯. ለተሳለጠ አገልግሎት አሰጣጥ ተመራጭ ሆኖ ሲገኝ ኮሚሽኑ በአንድ ማእከል አሰራር ከሚያከናውናቸው ስራዎች በተለይ ከፍተኛ የቴክኒክ ባህሪ ያላቸው የስራ ሂደቶች በሌላ አካል እንዲከናወኑ ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

፳፪. **በልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳዳሪ የሚቀርቡ አገልግሎቶች**

የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳዳሪ የውሀ፣ የኤሌክትሪክ፣ የቴሌኮም፣ የፈሳሽ እና የደረቅ ቆሻሻ የማስወገድ

insurance, courier and freight forwarding, customs brokerage, and other services;

u) facilitate the collection of pension contributions from employers and employees;

v) handle complaints and facilitate the resolution of disputes - including through the use of alternative dispute resolution methods;

w) coordinate the study and publication of input-output coefficients, follow through, and ensure the adoption of standards;

6/ The stipulation of Sub-Article (5) of this Article notwithstanding, the issuance of business license and related documents and the regulation of domestic and foreign investments issued with commercial registration and investment permit by the Commission and engaged in trading and service provisions within special economic zones shall be facilitated by the Ministry of Trade and Regional Integration.

7/ Where such measure is desired in the interest of efficient service provision, the Commission may delegate to another entity some of the services it renders within the one stop shop, particularly those that exhibit higher technical feature.

22. **Services Provided by a Special Economic Zone Operator**

A special economic zone operator shall have the obligation to organize an administrative

https://t.me/customsclearingagents

እና ሌሎች አስፈላጊ አገልግሎቶችን በቀጥታ ራሱ ወይም በሶስተኛ ወገን አቅራቢ አማካኝነት በዞኑ ውስጥ ለመስጠት የሚያስችል የአስተዳደር ሥርዓት የማደራጀት ግዴታ አለበት።

## ፳፫. የአገልግሎት ክፍያ እና ቅጣት

፩/ ኮሚሽኑ ለልዩ ኢኮኖሚ ዞን ተጠቃሚዎች የሚሰጣቸው ፈቃዶች፣ የምስክር ወረቀቶች፣ ምዝገባዎች እና ስምምነቶችን ጨምሮ ለሚያቀርባቸው ሌሎች አገልግሎቶች ክፍያ፣ እንዲሁም ይህን አዋጅ እና አዋጁን ተከትሎ የሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ ሲጣስ ለሚጣሉ አስተዳደራዊ ቅጣቶች መቀጮ ይሰበስባል።

፪/ ለኮሚሽኑ ከአገልግሎቶች እና አስተዳደራዊ ቅጣቶች ጋር በተያያዘ የሚከፈል ማንኛውም ገንዘብ ወይም ቅጣት በቦርዱ በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

፫/ ቦርዱ የሚሰበሰብ የአገልግሎት ገንዘብ ምጣኔን በተመለከተ የሚያሳልፈው ውሳኔ መንግስት አገልግሎቱን ለማመቻቸት ያወጣውን ወጪን እና አገልግሎቱን ለማዘመን የሚያስፈልገውን በጀት መሰረት በማድረግ ይሰላል።

## ክፍል አምስት

## የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ተጠቃሚዎች መብቶች፣ ግዴታዎች እና የኢንቨስትመንት ሥራ ስለሚያከናውኑበት ሁኔታ

## ፳፬. የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ መብቶች

፩/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ዲዛይን የማድረግ፣

system for the provision of water, electricity, telecom, removal of liquid and solid waste, and other services within each special economic zone either directly or through third party providers.

## 23. Service Charges and Fines

1/ The Commission shall collect fees and fines from special economic end-users for services it renders, including licenses, permits, certificates, registrations, and agreements, and for administrative sanctions imposed in respect of violations of this Proclamation and Regulations and Directives issued hereunder.

2/ In connection with services and administrative sanctions, any fee or fine collected by the Commission shall be determined through a Directive to be adopted by the Board.

3/ In determining a service fee regime, the Board shall be guided by the principle of recouping government expenses incurred in connection with availing and further improving the service facilities.

## PART FIVE

## RIGHTS AND OBLIGATIONS OF SPECIAL ECONOMIC ZONE END-USERS AND CONDITIONS UNDER WHICH THEY UNDERTAKE INVESTMENT ACTIVITY

## 24. Rights of a Special Economic Zone Developer

1/ Any special economic zone developer shall have the following rights:

a) design, construct, develop, exploit

https://t.me/customsclearingagents

የመገንባት፣ የማልማት፣ የመጠቀም እና ተያያዥ የሆኑ አገልግሎቶችን የመስጠት፣

ለ) የለማ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬትን በንዑስ-ሊዝ ለድርጅት ወይም እውቅና ለተሰጠው አካል የማስተላለፍ፣

ሐ) በቦርዱ ሲፈቀድ የለማ ወይም ያልለማ መሬትን በንዑስ-ሊዝ ለንዑስ አልሚ የማስተላለፍ፣

መ) ህንፃዎችን፣ ግንባታዎችን እና ሌሎች ተንቀሳቃሽ ሀብቶችን ለድርጅት የማከራየት ወይም የመሸጥ፣

ሠ) መሰረተ-ልማትን ጨምሮ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን፡ የዞን መሬት እና ሀብትን በንዑስ አልሚነት ለማልማት፣ ለማስተዳደር፣ ለማስተዋወቅ እና በአገልግሎት ሰጪነት ለመሳተፍ ከሚሹ ሶስተኛ ወገኖች ጋር ስምምነት የመፈራረም፣

ረ) ልዩ የኢኮኖሚ ዞንን የማስተዋወቅ፣ እነዚህን ተግባራት የሚፈፅም አስተዳዳሪ የመሾም፣ የማስተዋወቅ ስራዎችን ከኮሚሽኑ አጠቃላይ መርሆች ጋር በመናበብ በቅንጅት ወይም በተናጠል የማከናወን፣

ሰ) አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት ብድር፣ የብድር ዋስትና ወይም ሌሎች የገንዘብ ምንጮችን ለማግኘት በኢትዮጵያ እና ከኢትዮጵያ ውጪ ባሉ የፋይናንስ ገበያዎች ላይ የመሳተፍ፣

ሸ) ከአገልግሎት ሰጪዎች ጋር በሚደረግ የኮሚሽን ስምምነት መሰረት በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ አገልግሎት የማቅረብ፣

special economic zone, and provide related services;

b) sub-lease a developed special economic zone land to an enterprise and authorized entity;

c) transfer developed or undeveloped land to a sub-developer through sub-lease when such is authorized by the Board;

d) rent or sell buildings, constructions, and other moveable assets to enterprises;

e) enter into contract with third parties for sub-development, operation, promotion, and servicing of special economic zone, zone lands and assets, including on-site infrastructure;

f) promote a special economic zone or appoint an operator to undertake such activities, carry-out promotion works jointly or unilaterally, provided that they are generally coordinated with the Commission's policies;

g) subject to the applicable laws, participate in financial markets both in Ethiopia and abroad in order to obtain loans, fund guarantees and other financial resources;

h) provide services within special economic zones on the basis of commission agreements concluded with service providers;

https://t.me/customsclearingagents

ቀ) በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት የቀረጥ እና ታክስ ነፃ ጥቅሞች እና ሌሎች ማበረታቻዎችን የማግኘት፣

በ) አግባብነት ባለው ህግ መሰረት ኢትዮጵያዊያንና የውጭ ሀገር ዜጎችን በማኔጅመንት እና ቴክኒካል የስራ መደቦች የመቅጠር፣

ተ) በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች፣ በአልሚ ስምምነት እና በአልሚ ፈቃድ ላይ በተመለከቱ ተግባራት ላይ የመሳተፍ እና ሌሎች መብቶችን የመጠቀም፡፡

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ለንዑስ-አልሚ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ ፊደል ተራ (ለ) መሰረት አልሚው መብቱን በሚያስተላልፍበት ወቅት የንዑስ አልሚውን እና የድርጅቱን እንዲሁም ሌሎች ባለመብቶችን መብት በማይነካ መልኩ መሆን አለበት፡፡

## ፳፭. <u>የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ ግዴታዎች</u>

፩. ማንኛውም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ) በአልሚ ፈቃድ፣ ወይም በአልሚ ወይም አስተዳዳሪ ስምምነት በተገለጸው አግባብ እና በዚህ አዋጅ መሰረት ለአንድ ማዕከል የሚያገለግሉ ቢሮዎችን እና መገልገያዎችን በዞኑ ውስጥ የመገንባት፣

i) enjoy customs duty and tax exemptions and other incentives pursuant to this Proclamation and applicable laws;

j) employ Ethiopian and foreign nationals in management and technical positions in accordance with the appropriate laws;

k) engage in activities permitted under this Proclamation, Regulations and Directives enacted hereunder, a developer agreement and developer license, and exercise other rights;

2/ The stipulations of Sub-Article (1) of this Article shall apply, mutatis mutandis, to a sub-developer.

3/ Where a developer transfers its rights to third parties according to Sub Article 1 Paragraph (b) of this article, it shall do so only in a manner that does not prejudice the rights of sub-developers, enterprises and other end users.

## 25. <u>Obligations of a special economic zone developer</u>

1/ Any special economic zone developer shall have the following obligations:

a/ construct service facilities including office space and amenities for use by one stop shop as stipulated in a developer license, or developer or operator agreement, and in compliance with the requirements of this Proclamation;

https://t.me/customsclearingagents

ለ) ለጉምሩክ ኮሚሽን አገልግሎት የሚውል አግባብነት ካለው ሕግ ጋር የሚጣጣም መሰረተ-ልማት የማቅረብ፣

ሐ) በሕግ እና በአልሚ ስምምነት ውስጥ በተገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከኢንቨስትመንት ፈቃድ ይዘት ጋር በሚስማማ አግባብ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ልማትን የመጀመር እና የማጠናቀቅ፣

መ) በግንባታ ወቅት የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና እርዳታ፣ የካፌ እና የንጽህና መስጫን ጨምሮ አስፈላጊ አገልግሎቶችን የመስጠት፣ የግንባታ ሰራተኞችን ደህንነት እና ጤንነት የማረጋገጥ፣

ሠ) ልዩ ኢኮኖሚ ዞን በደረጃ በሚለማበት ጊዜ የተቀመጡ ልዩ የአፈፃፀም ሁኔታዎችን የማክበር፣

ረ) ቦርዱ ካልፈቀደ በቀር ማንኛውም በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የሚገኝ ያልለማ መሬት ወደ ተጠቃሚ እንዳይተላለፍ የማድረግ፣

ሰ) ከልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬት ዋጋ እና ማስተላለፍ ስራዎች ጋር በተያያዘ እሴት ካልተጨመረባቸው አሰራሮች የመቆጠብ፣

ሸ) መሰረተ-ልማቶችን እና ተያያዥ አገልግሎቶችን የማቅረብ፣

ቀ) የዞን መሰረተ-ልማቶች፣ ማሽኖች እና ቦታዎች ጥበቃ፣ ጥገና እና መተካት አገልግሎትን ጨምሮ ለድርጅቶች የተመደቡ ቦታዎች በአግባቡ መያዛቸውን የማረጋገጥ፣

b/ avail on-site infrastructure that is compliant with the applicable laws for purposes of services offered by Customs Commission;

c/ commence and complete special economic zone development in compliance with the terms of the investment permit within the period specified under the law and a developer agreement;

d/ during construction, provide necessary facilities including first aid, cafeterias, toilets, and ensure the security and well-being of construction workers;

e/ adhere to specified performance requirements in respect of phased development of a special economic zone;

f/ ensure that no un-developed economic zone land is transferred to an end-user except through a specific authorization by the Board;

g/ refrain from speculative economic zone land pricing and transfer activities;

h/ provide infrastructure and related services;

i/ ensure the proper management of spaces and facilities allocated to enterprises, including maintenance, repair and replacement of onsite infrastructure, machinery and parts;

https://t.me/customsclearingagents

በ) ዋና ዋና የግንባታ ምእራፎችን፣ የዞን አስተዳደር፣ የፋብሪካ ሼዶችና ሕንፃዎች አጠቃቀም፣ የሰራተኞች መረጃ፣ የወጪ ንግድ እና ሌሎች አፈፃፀሞችን የሚመለከት የአፈፃፀም ሪፖርት በቂ መረጃ የመያዝ እና ለኮሚሽኑ በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት የማስገባት፣

ተ) የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ክልልን ከጉምሩክ ክልል ለመለየት የሚያስችል በቂ መለያ የመገንባት፣

ቸ) አግባብነት ያለው የደህንነት መከታተያ ቴክኖሎጂ መትከልን ጨምሮ በቂ የመስክ ላይ የደህንነት ጥበቃ መስጠት ወይም እንዲሰጥ የማድረግ፣

ኀ) ከልዩ ኢኮኖሚ ዞን ልማት ጋር የተያያዘ ክህሎት እና እውቀት ለኢትዮጵያዊያን የሚተላለፍበትን ሁኔታ የማመቻቸት፣

ነ) በዚህ አዋጅ፣ አግባብነት ባላቸው ሕጎች ወይም በኢንቨስትመንት ፈቃድ ላይ የተመለከቱ ሌሎች ግዴታዎችን የማክበር፡፡

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ለንዑስ አልሚ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## ፳፮. <u>የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳዳሪ መብቶች</u>

ማንኛውም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳዳሪ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡

፩/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳዳሪ ሥምምነት እና ፈቃድ መሰረት ልዩ ኢኮኖሚ ዞንን የማስተዳደር፣ የመንከባከብ እና የማስተዋወቅ፣

j/ maintain adequate record of its activities and submit to the Commission a quarterly report on construction milestones, operation of zone, use of factory sheds and buildings, employment statistics, export, and other performances;

k/ construct adequate enclosure to segregate a special economic zone's area from the customs territory;

l/ provide or cause to be provided adequate on-site security, including the installation of appropriate surveillance technology;

m/ facilitate the transfer of skills and knowledge to Ethiopians in respect of special economic zone development, and

n/ comply with other obligations specified in this Proclamation, other applicable laws, or the investment permit.

2/ The stipulations of Sub Article (1) of this Article shall apply mutatis mutandis to a sub-developer.

## 26. <u>Rights of a Special Economic Zone Operator</u>

Any special economic zone operator shall have the following rights:

1/ operate, manage and promote a special economic zone in accordance with an operator agreement and license;

https://t.me/customsclearingagents
https://t.me/customsclearingagents

፪/ የእለት ተእለት እንቅስቃሴን ለመምራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ማውጣት፣

፫/ በአልሚው ስም መሰረታዊ አቅርቦቶችን እና አገልግሎቶችን በክፍያ እንዲቀርብ የማድረግ፣

፬/ አገልግሎቶችን ለመስጠት ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ስምምነት የመፈራረም፡፡

## ፳፯. <u>የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳዳሪ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳዳሪ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

፩/ ኢንቨስትመንቶችን በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ፣ በአስተዳደር ስምምነቱ ወይም በንግድ ፈቃዱ መሰረት ማከናወን፣

፪/ ልዩ ኢኮኖሚ ዞንን ማስተዳደር፣ መንከባከብ፣ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ንብረቶች እና መሰረተ-ልማቶቸ በማናቸውም ጊዜ ለአገልግሎት ዝግጁ ሆነው የሚቆዩበትን ሁኔታ የመጠበቅ፣

፫/ ህንፃ እና መሰረተ-ልማቶችን የማሻሻል፣ በዞን ውስጥ የሰዎች እና ተሽከርካሪዎች የተሳለጠ እንቅስቃሴ፣ የተሽከርካሪዎች ማቆሚያ እና የካርጎ ተርሚናሎች፣ የእሳት አደጋን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስፈልግ የሰው ሀይል እና ተሽከርካሪዎች ስምሪት፣ የደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻዎችን ማስወገድ ስርአት፣ የጋራ መጠቀሚያ ቦታዎች ጽዳት፣ እና የአረንጓዴ ቦታዎች እና መሰረተ-ልማቶች ንፅህና እና እንክብካቤ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥራዎችን የማከናወን፣

፬/ ለአንድ መስኮት አገልግሎት እና ለጉምሩክ አገልግሎት የሚሆን ቢሮ እና መሰረተ-ልማት፣ የህጻናት ማቆያ፣ አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ መሰረተ-ልማት የማዘጋጀት፣

2/ adopt operational procedures to guide routine activities;

3/ deliver utilities and services on behalf of the developer for a charge;

4/ conclude agreement with third parties for the provision of services.

## 27. <u>Obligations of a Special Economic Zone Operator</u>

Any special economic zone operator shall have the following obligations:

1/ ensure that investments are carried out in compliance with this Proclamation, Regulation or Directives enacted hereunder, operator agreement and license;

2/ operate, maintain the special economic zone, and keep its assets and utilities in operational condition;

3/ implement measures involving the modification of buildings and infrastructure, efficient management of the movement of people and vehicles within a special economic zone, use of parking space and cargo terminals, deployment of fire and accident prevention and control system, removal of liquid and solid waste, cleanliness of common spaces, and maintenance of common space, green areas, and infrastructure;

4/ maintain office space and facilities for one stop shop and customs services, avail day-care facility, prepare disability-friendly infrastructure;

https://t.me/customsclearingagents

፭/ በቦርዱ ፈቃድ ለንዑስ አልሚዎች ወይም ለተለዩ ተጠቃሚዎች ካልሆነ በስተቀር ያልለማ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬትን ለሶስተኛ ወገን ከማስተላለፍ የመቆጠብ፣

፮/ በዚህ አዋጅ፣ አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች ወይም በፈቃድ ስምምነት ላይ የተመለከቱ የማህበራዊ እና አካባቢያዊ ግዴታዎችን የማክበር፣

፯/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ አገልግሎቶች ያለምንም አድሎ መሰጠታቸውን የማረጋገጥ፣

፰/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ሰላምና ደህንነትን ማረጋገጥ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ከመንግሥት የጸጥታ አካላት ጋር በመተባበር መስራት፣

፱/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬት ልማት እና ግንባታን፣ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳደር፣ የፋብሪካዎች እና ህንፃዎች አጠቃቀም፣ የሰራተኞች መረጃ፣ ስለ ወጪ ንግድ እና መሰል አፈፃፀሞች በየሩብ አመቱ ለኮሚሽኑ ሪፖርት የማቅረብ፣

**፳፰. <u>የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት መብቶች</u>**

ማንኛውም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡

፩/ በዚህ አዋጅ፡ በኢንቨስትመንት ፈቃድ እና ንግድ ፈቃድ ላይ በተመለከቱ ሁኔታዎች መሰረት የኢንቨስትመንት ስራዎቹን በነፃነት የመስራት፣

፪/ በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተሰጡ የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ማበረታቻዎችን የማግኘት፣

5/ refrain from transferring un-developed special economic zone land to third parties - except to sub-developers or specific end-users in accordance with authorization by the Board;

6/ comply with social and environmental obligations provided for in this Proclamation, other applicable laws, and license agreement;

7/ ensure, within a special economic zone, the provision of services without discrimination;

8/ ensure peace and security within a special economic zone, and where necessary, work in coordination with government security agencies;

9/ submit to the Commission quarterly report regarding special economic zone land development and construction, special economic zone operation, use of factory and buildings, employment statistics, exports, and other performances.

**28. <u>Rights of a Special Economic Zone Enterprise</u>**

Any special economic zone enterprise shall have the following rights:

1/ freely undertake its investment activities in accordance with the terms of this Proclamation, investment permit and license;

2/ receive customs duty and tax incentives provided for under this Proclamation and applicable laws;

https://t.me/customsclearingagents

፫/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬትን በንዑስ-ሊዝ የማግኘት፣ ህንፃ በባለቤትነት የመያዝ ወይም የመሸጥ፣ ሌሎች የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በኪራይ የመያዝ፣

፬/ እቃዎችና አገልግሎቶችን ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ማስገባት ወይም ከልዩ ኢኮኖሚ ዞን የማስወጣት፣ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ እቃዎችን የመሸጥ፡፡

## ፳፱. የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት ግዴታዎች

ማንኛውም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

፩/ በድርጅት ኢንቨስትመንት ፈቃድ ስምምነት እና/ወይም ፈቃድ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማልማት መጀመር እና ማጠናቀቅ፣

፪/ ኢንቨስትመንቱን እና ሌሎች ስራዎችን ከኢንቨስትመንት ፈቃድ ስምምነት፣ ኢንቨስትመንት ፈቃድ እና አግባብነት ያለው ሕግ ጋር በተጣጣመ መንገድ ማከናወን፣

፫/ በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባለው ሕግ የተመለከቱ የአካባቢ፣ ማህበራዊ እና የስራ ሁኔታ ግዴታዎችን ማክበር፣

፬/ የሥራ ሁኔታ እና ምርታማነትን የሚመለከት ስርዓት መዘርጋት፣ የጤና አገልግሎት ሽፋን፣ የህፃናት ማቆያ፣ አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ መሰረተ-ልማት፣ ካፌ እና እንደአስፈላጊነቱ የትራንስፖርት አገልግሎት ማቅረብ፣

፭/ ስለ ሠራተኞች፣ የምርት ሥራ፣ ወጪ ንግድ፣ የቴክኖሎጂ፣ የእውቀት እና የክህሎት ማስተላለፍ እና ሌሎች አፈፃፀሞችን አስመልክቶ በየሩብ አመቱ ለኮሚሽኑ እና ለአስተዳዳሪው ሪፖርት ማቅረብ፡፡

3/ acquire land on a sub-lease basis, possess or sell buildings, or rent other immovable assets;

4/ move goods and services into or out of a special economic zone, sell goods within a special economic zone.

## 29. Obligations of special economic zone enterprise

Any special economic zone enterprise shall have the following obligations:

1/ commence and complete development within the period specified in enterprise investment agreement and/or permit;

2/ carry out investments and other activities in compliance with the investment agreement, permit and applicable laws;

3/ comply with environmental, social and labor obligations specified under this Proclamation and applicable laws;

4/ put in place a system on work conditions and productivity, provide access to health care coverage, day-care, disability-friendly infrastructure, cafeterias, and where appropriate, transportation;

5/ quarterly submit to the Commission and the operator a report on employment, production, export, transfer of technology, knowledge and skills, and other performances.

https://t.me/customsclearingagents

**፴. የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ሌሎች ተጠቃሚዎች መብትና ግዴታ**

፩/ ማንኛውም ሰው የልዩ ኢኮኖሚ ዞን የተጠቃሚነት ደረጃ የሚይዘው ከኮሚሽኑ ፈቃድ ሲያገኝ ብቻ ነው።

፪/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን የተጠቃሚነት ፈቃድ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ዝርዝሮች እና ፈቃድ የሚሰጥበት አግባብ፣ ሰራተኞች፣ ነዋሪዎች፣ አገልግሎት ሰጪ ሶስተኛ ወገኖች፣ የአንድ መስኮት አገልግሎት ሰጪዎች፣ እና የክልል እና የፌዴራል መንግሥት ተቋማትን ጨምሮ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ሌሎች አካላት ኃላፊነት ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፫/ የተፈቀደለት ሠራተኛ ሆነ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የሚኖር ወይም መገኘት የሚገባው ማንኛውም ሰው እንደሁኔታው በአልሚው ወይም በአስተዳዳሪው የተሰጠ የማንነት መለያ መታወቂያ ይኖረዋል።

፬/ በዚህ አዋጅ ወይም ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ በግልፅ ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውም የፌዴራል፣ የክልል ወይም የአካባቢ አስተዳደር አካል ወይም ግለሰብ ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን መግባት ወይም በዞኑ ሥራ ጣልቃ መግባት አይችልም፡ ሆኖም ይህ ክልከላ ለጸጥታ ሥራ፡ ወይም ለሥራ ሁኔታ ቁጥጥር አላማ፡ ወይም በአልሚው ወይም አስተዳዳሪው ፈቃድ ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን የሚገቡ ሰዎችን አይመለከትም፡፡

**30. Rights and obligations of other special economic zone end-users**

1/ A person attains a special economic zone end-user status only upon receipt of a permit from the Commission.

2/ Particulars and procedures for the issuance of special economic zone end-user permit, responsibilities of entities operating within a special economic zone including workers, residents, third party service providers, one stop service providers, and regional and federal governance agencies shall be specified in a directive to be issued by the Commission.

3/ Any authorized person, whether employed, residing or required to be present within a special economic zone, shall have an identity card issued by the developer or operator, as the case may be.

4/ No federal, regional or local administrative entity or person shall enter into or interfere with an economic zone activities except where such is expressly permitted under this Proclamation or Directives enacted hereunder, provided that such restriction shall not impede the entry of persons to a special economic zone for purposes of maintaining security or labor inspection, or where such is authorized by the developer or operator.

https://t.me/customsclearingagents

https://t.me/customsclearingagents

**፴፩. የማይንቀሳቀስ እና ተንቀሳቃሽ ንብረት መያዣ፣ ዋስትና እና ማረጋገጥ መብቶች**

፩/ ማንኛውም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ፣ ንዑስ አልሚ ሥልጣን የተሰጠው አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት ከፋይናንስ ተቋማት ብድር ለማግኘት የለማ መሬት ወይም የማይንቀሳቀስ እና የሚንቀሳቀስ ሀብቱን አግባብ ባለው ሕግ መሰረት በመያዣነት ወይም በዋስትና ለመስጠት ይችላል።

፪/ ኮሚሽኑ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ በማይንቀሳቀሱ ወይም በሚንቀሳቀሱ ንብረቶች ላይ ያሉ መብቶችን ለማስተላለፍ፣ በንዑስ-ሊዝ ያዥነት፣ በዋስትና፣ በልዩ ጥቅም፣ በወለድ አግድ፣ ወይም ከማስያዣነት ጋር የሚገናኙ ውሎችን፣ እንዲሁም ከግንባታ ዲዛይን እና ንዑስ ሊዝ ያዥነት የምስክር ወረቀቶች ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ያረጋግጣል።

፫/ ኮሚሽኑ አግባብነት ካለው አካል ጋር በመተባበር ለማረጋገጥ እና ለምዝገባ የሚያገለግል ሥርዓት ያደራጃል፣ ክፍያ በማስከፈል ለልዩ ኢኮኖሚ ዞን ተጠቃሚዎች እና ሶስተኛ ወገኖች አገልግሎትን ተደራሽ ያደርጋል።

**፴፪. አካባቢን የሚመለከቱ ህጎች**

፩/ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር አካባቢን የሚመለከቱ የፌዴራል እና የክልል ሕግ ድንጋጌዎች በመላው የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

፪/ አግባብነት ያለው የፌዴራል ወይም የክልል የአካባቢ ጥበቃ አካል በአንድ ማዕከል አገልግሎት አካባቢን የሚመለከቱ ሕጎች፣ ደረጃዎች፣ ስልታዊ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ፣

**31. Movable and Immovable Property Mortgage, Pledge and Authentication Rights**

1/ Any special economic zone developer, sub developer, authorized operator, or enterprise may, in accordance with the appropriate law, mortgage or pledge its developed land or other immovable or movable asset to obtain loan from financial institutions.

2/ The Commission shall authenticate contracts and documents pertaining to transfer of rights created on movable or immovable properties located within economic zones, and to sub leaseholds, or any other agreement relating to security, surety, privileges, liens or mortgages, as well as documents relating to construction design and sub-leasehold certificate.

3/ In coordination with the competent authority, the Commission shall establish a system for registration and documentation, and make the service accessible to special economic zone end-users and third parties upon payment of fee.

**32. Environmental Legislations**

1/ Unless provided otherwise, the pertinent provisions of the federal and regional environmental laws shall apply across all special economic zones.

2/ The appropriate federal or regional environmental protection agency shall deploy officers within the one stop service to monitor the application, supervision,

https://t.me/customsclearingagents

ማህበራዊ አካባቢና ተፅዕኖ ግምገማ አተገባበር፣ የማህበራዊና የአካባቢ አያያዝ እቅድ አፈፃፀምና የጥበቃ አሰራሮች፡ የአስተዳደር እና የቅነሳ ሂደቶችን በተመለከተ የአተገባበር፣ የክትትል፣ የጥበቃ እና የአፈፃፀም ሥራዎችን የሚከታተሉ ባለሙያዎችን የመመደብ ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት

## በልዩ ኢኮኖሚ ዞን በኢንቨስትመንት ዘርፍ የመሳተፍ መብት

### ፴፫. በኢንቨስትመንት ዘርፍ ስለመሳተፍ

፩. አግባብነት ባለው ሕግ በግልፅ ከተከለሉ መስኮች ውጪ የልዩ የኢኮኖሚ ዞን ስርዓት ለውጪ ኢንቨስትመንቶች ሰፊ የመሳተፍ እድልን የሚሰጥ ሆኖ በቦርዱ ይደራጃል፡፡

፪. ቦርዱ በየዓመቱ በጉምሩክ ክልል እና በልዩ ኢኮኖሚ ዞኖች ለውጪ ኢንቨስትመንት ዝግ የሆኑ ዘርፎችን ዝርዝር ማስታወቂያ ያወጣል፡፡

፫. የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከኮሚሽኑ ጋር በመመካከር በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የሚከናወኑና በሥልጣኑ ማእቀፍ ስር የሚወድቁ የንግድና የአገልግሎት ስራዎች ዝርዝር በመመሪያ ያወጣል፡፡

### ፴፬. የፋይናንስ አገልግሎት አደረጃጀት እና አስተዳደር

፩/ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ወይም ይሁንታ ያገኙ የውጭ እና የሀገር ውስጥ የፋይናንስ ተቋማት በልዩ ኢኮኖሚ ዞን አገልግሎት የማቅረብ መብት አላቸው፡፡

protection and enforcement of environmental norms, standards, strategic environmental assessment, social and environmental impact assessment, environmental and social management plans, safeguards, management and mitigation schemes.

## PART SIX

## RIGHT OF PARTICIPATION IN INVESTMENT SECTOR WITHIN SPECIAL ECONOMIC ZONE

### 33. Participation in Investment Sectors

1/ Except in respect of areas specifically reserved under the applicable laws, the special economic zone regime shall be organized by the Board as availing the widest possible opportunity to foreign investments.

2/ The Board shall publish annually a bulletin on National Negative List of Foreign Investments applicable in respect of the customs territory and within special economic zones.

3/ In consultation with the Commission, the Ministry of Trade and Regional Integration shall issue a list of trading and service activities that shall be carried out within special economic zones and fall within its mandate.

### 34. Setting Up and Operation of Financial Service

1/ Foreign and domestic financial institutions got permission or authorization by National Bank of Ethiopia have the right to render their services within special economic zones.

https://t.me/customsclearingagents

፪/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን በፋይናንስ አገልግሎት ላይ የሚሰማሩ ተቋማትን አስመልክቶ ተቋማቱ የሚመረጡበት መስፈርት፣ ደረጃ እና የአሰራር እና የፈቃድ አሰጣጥ ሁኔታ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፫/ አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት የተሰጡ የባለሀብት መብቶች እንደተጠበቁ ሆኖ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የልዩ ኢኮኖሚ ዞንን ሳቢነት፣ ተወዳዳሪነት እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ራሱን የቻለ የፋይናንስ እና የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሪፎርም ያካሂዳል፡ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል።

፬/ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተለይ፦

ሀ) ከኢንቨስትመንት እና ወጪ ንግድ የተገኘ ገንዘብ ወደ ውጪ ማስተላለፍን፣ የውጭ ሀገር ገንዘብ የባንክ አካውንት መክፈትን፣ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ለግብይት የሚያገለግሉ የገንዘብ አይነቶችን እና መሰል ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረገ፣

ለ) የኢንቨስትመንቱን ልዩ ባህርይ፣ የወጭ ንግድ የማሳደግ ብሔራዊ ትልምን፣ የኢንዱስትሪዎችን የግብዓት ፍላጎት፣ እና መሰል ጉዳዮችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የሚገኙ ባለሀብቶች ከኢንቨስትመንት ሥራቸው የሚያገኙትን የውጭ ምንዛሪ ይዘው የሚቆዩበት እና የሚጠቀሙበት፣ በጉምሩክ ክልል ውስጥ ተፈፃሚ ከሚደረገው አሰራር የተሻለ ጥቅም የሚሰጥ ስርአትን፣

የሚገዛ መመሪያ ያወጣል።

2/ In respect of institutions involved in financial services within special economic zones, the National Bank of Ethiopia shall issue Directive regulating the selection criteria, standards, and operational and licensing requirements.

3/ Without prejudice to rights of investors recognized under the applicable laws, the National Bank of Ethiopia shall carry out tailored reforms relating to finance and foreign currency management, and establish procedures that support and facilitate the attractiveness, competitiveness and effectiveness of special economic zones.

4/ In particular, the National Bank of Ethiopia shall issue Directive to regulate, among others: -

a/ the remittance of funds earned from investments and exports, the opening of foreign currency accounts, and types of currencies used as medium of transaction within special economic zones;

b/ the retention and utilization of foreign currencies earned from investment activities that present to investors operating within special economic zones greater benefit than is the case in the customs territory and is based on particular considerations affecting the investments, including the nature of the investment activity, national export drive, and industry input requirements.

https://t.me/customsclearingagents

https://t.me/customsclearingagents

## ክፍል ሰባት

## ስምምነት የመግባት ግዴታ

### ፴፭. ስምምነት

፩/ ማናቸውም አልሚ፣ ንዑስ አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከማግኘቱ በፊት ከኮሚሽኑ ጋር ስምምነት መግባት አለበት።

፪/ የአልሚ ስምምነቱ የሚከተሉት ነጥቦችን መያዝ አለበት፡-

ሀ) የስምምነቱን ዓላማ፣

ለ) የሚለማው መሬት መልከዓ-ምድራዊ ወሰን፣

ሐ) የፋይናንስ ግዴታዎች፣ የስልታዊ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ፣ የማህበራዊና የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እና የአካባቢ አያያዝ እቅድ ግዴታዎች፣

መ) የፕሮጀክት ግንባታ የሚጀመርበት እና የሚጠናቀቅበት ግልፅ የጊዜ ገደብ፣

ሠ) መሬትን ላልተፈለገ ዓላማ ማዋልን እና ያልለማ መሬትን ያለፈቃድ ማስተላለፍን የሚከለክል ድንጋጌ፣

ረ) የግንባታ ቦታዎችን ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ዘዴ፣

ሰ) በፕሮጀክቱ ልማት ሂደት ጥቅም ላይ የሚውሉ ከጊዜያዊ ሰራተኛ ማረፊያዎች፣ ካፌዎች እና ቢሮዎች ጋር የተያያዙ ግንባታዎችን የሚመለከቱ ደረጃዎች እና የጊዜ ገደብ፣

## PART SEVEN

## REQUIREMENT OF ENTERING INTO AGREEMENT

### 35. Agreement

1/ A developer, sub-developer, operator or enterprise must enter into agreement with the Commission before an investment permit is issued.

2/ A developer agreement shall comprise the following essential elements:

a/ purpose of the agreement;

b/ geographical boundaries of the land to be developed;

c/ financial obligations, requirements relating to strategic environmental assessment, social and environmental impact assessment, and environmental management plans;

d/ clear time-frame for commencement and completion of project construction;

e/ provisions that prohibit the use of land for unintended purposes and the transfer of undeveloped land without authorization;

f/ methods of ensuring the safety of the perimeter of a construction site;

g/ standards and time-frame pertaining to the construction of temporary worker dormitories, cafeterias and offices utilized in the course of project development;

https://t.me/customsclearingagents

https://t.me/customsclearingagents

ሸ) ከጉምሩክ ቀረጥ እና ግብር ነፃ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የመንገድ፣ የኤሌክትሪክ ሀይል፣ ቴሌኮም፣ ውሀ፣ የፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ፣ ሎጂስቲክስ፣ ደህንነት፣ የእሳት አደጋ መከላከያ፣ የግንባታ ማሽነሪዎች እና መሳሪያዎች፣ የህንፃ ግንባታ ንድፍ እና የግንባታ ዕቃዎች፣ የካፒታል ዕቃዎች፣ ተገጣጣሚ ዕቃዎች፣ መለዋወጫዎች፣ ሶፍትዌር፣ ተሽከርካሪዎች፣ የግል መገልገያ ዕቃዎች፣ ጥሬ ዕቃዎች፣ አላቂ የቤተ-ሙከራ እና የንድፍ ዕቃዎች፣ ለሰራተኞች የሚያስፈልጉ እና የሚሰጡ እንደ መድሀኒት ያሉ የደህንነት እና ጤና-ነክ ዕቃዎች፣ እና ዕቃዎችን ለማሸግ የሚያገለግሉ ኮንቴይነሮች ዝርዝር፣

ቀ) በዚህ አዋጅ ወይም አግባብነት ባለው ሕግ በዝርዝር ያልተመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች።

፫/ ማናቸውም አስተዳዳሪ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) ላይ የተመለከቱ አግባብነት ያላቸው ጉዳዮችን እና በዚህ አዋጅ በአንቀፅ ፳፮ እና ፳፯ ላይ የተመላከቱ መብትና ግዴታዎችን ያካተተ የአስተዳዳሪ ስምምነት መፈረም አለበት።

**፴፮. <u>የድርጅት ስምምነት</u>**

፩/ አስቀድሞ ከአልሚው ወይም ንዑስ አልሚው ይሁንታ የማግኘት ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ድርጅት ከአልሚው ወይም ንዑስ አልሚው የተወሰነ መሬት ክፍልን በንዑስ-ሊዝ ከማግኘቱ በፊት ወይም በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ሕንፃ ከመያዙ ወይም ከመከራየቱ በፊት ከኮሚሽኑ ጋር ስምምነት መግባት አለበት።

h/ a list of items to be imported free from customs duty and tax pertaining to road, electric power, telecom, water, liquid waste disposal, logistics, security, fire accident prevention, infrastructure construction machinery and materials, building construction design and construction materials, capital goods, accessories, spare parts, software, motor vehicles, personal effects, raw materials, consumable laboratory and design materials, safety and health related materials such as medicines found to be necessary and issued to workers, and containers used to pack various goods;

i/ other matters not specified under this Proclamation or the applicable law.

3/ An operator shall sign operator agreement specifying the applicable rights and obligations specified under sub-article (2) of this Article and Articles 26 and 27 of this Proclamation.

**36. <u>Enterprise Agreement</u>**

1/ Without prejudice to its obligation to priorly obtain assurance from the developer or sub-developer, an enterprise must enter into agreement with the Commission before it obtains a land parcel from a developer or sub-developer, or acquires or rents a building within a special economic zone.

https://t.me/customsclearingagents

https://t.me/customsclearingagents

፪/ ስምምነቱ እንደአግባብነቱ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፴፭ ላይ የተመለከቱ ዝርዝሮች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ስለምርት እና የወጭ ንግድ፣ የስራ እና ሰራተኞች አያያዝ፣ እና ስልጠና እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ማካተት አለበት።

፫/ ድርጅቱ በአንቀፅ ፴፭ ንዑስ አንቀፅ (፪) ላይ በተመለከተው አግባብ ዕቃዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ እና ግብር ነፃ እንዲያስገባ ኮሚሽኑ ያመቻቻል፡፡

## ክፍል ስምንት

## የልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬት፣ የማይንቀሳቀስ እና የሚንቀሳቀስ ንብረት ስለመያዝ

### ፴፯. የልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬት ስፋት እና የአጠቃቀም ምጣኔ

፩/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ ጠያቂነት በልዩ ኢኮኖሚ ዞንነት የሚሰየም መሬት ዝቅተኛ ስፋት ከሀምሳ ሄክታር በታች ሊሆን አይችልም።

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ቦርዱ እጅግ በተለየ ሁኔታ የፕሮጀክቱን ልዩ ባህርይ መሰረት በማድረግ የሚሰየም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬት ስፋት ያነሰ እንዲሆን ሊወስን ይችላል።

፫/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ለፋብሪካ ህንፃዎች፣ ሼዶች፣ ንግድ ሥራ፣ የጋራ አገልግሎት መጠቀሚያ፣ ለመሰረተ-ልማት፣ መኖሪያዎች፣ መሰል ሕንፃዎች እና ለምርት እና አገልግሎት ሥራ የሚውለው መሬት አጠቃላይ መጠን በዞኑ ይዞታ ስር ካለው ጠቅላላ መሬት ከ፶ በመቶ በታች ወይም ከ፸፭ በመቶ በላይ መሆን አይችልም፡፡

2/ In addition to the appropriate elements specified under Article 35 of this Proclamation, the agreement shall include conditions regarding production and export, employment and workers management, and training and technology transfer.

3/ The Commission shall facilitate for the enterprise to import goods free from customs duty and tax in accordance with the list indicated in Sub-Article (2) of Article 35.

## PART EIGHT

## ACQUISITION OF SPECIAL ECONOMIC ZONE LAND, MOVABLE AND IMMOVABLE PROPERTY

### 37. Size and functional proportion of special economic zone land

1/ The minimum size of land subjected to designation application by a special economic zone developer shall not be less than fifty hectares.

2/ The stipulation under Sub-Article (1) of this Article notwithstanding, the Board may, in very exceptional circumstances and based on peculiarities of a project, decide to designate a special economic zone having a lesser size of land.

3/ The total size of land in any special economic zone to be used for factory buildings, sheds, setting up businesses, common use facilities, infrastructure, residence and related buildings, and production and service amenities shall not be less than 50 percent or exceed 75 percent of the total land under possession.

https://t.me/customsclearingagents

## ፴፰. የልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬት አመዳደብ፣ ልማት እና አጠቃቀም ሥርዓት

፩/ ከልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬት ልማት እና አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ሁሉም ሕጎች ወይም ደረጃዎች በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ ብቻ ይመራሉ።

፪/ መሬት ስለማግኘት፣ የመሬት ይዞታን፣ የከተማ ወይም የገጠር መሬት አጠቃቀምን እና የጨረታ ሥርዓትን የሚመለከቱ ማናቸውም ሌሎች የሕግ ወይም አስተዳደራዊ ሥርዓቶች የልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬትን በተመለከተ ተፈፃሚነት የላቸውም።

፫/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬት ምዝገባ፣ ክፉይ መሬትን በሊዝ ስለመስጠት፣ በንዑስ-ሊዝ ስለመያዝ፣ የባለቤትነት ካርታዎች፣ የሊዝ ያዥነት የምስክር ወረቀት፣ የህንፃዎች ደረጃ፣ የህንፃ አጠቃቀም፣ የፕሮጀክት መሬት ልማት፣ ግንባታ፣ እና የደህንነት እና መሰረተ-ልማት አገልግሎቶችን የሚመለከቱ ዝርዝር ድንጋጌዎች ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ፡፡

## ፴፱. ለልዩ ኢኮኖሚ ዞን ልማት የሚውል መሬት ስለሚገኝበት አግባብ

በስያሜ ማመልከቻ ላይ የሚገለጽ መሬት አመልካቹ ከኮርፖሬሽኑ የመሬት ባንክ የሚያገኘው፣ በክልል መስተዳድር የሚመደብ፣ ወይም በግል ወይም በመንግስት ሊዝ ያገኙ እጅ የሚገኝ የለማ ወይም ያልለማ መሬትን የሚመለከት ሊሆን ይችላል።

## 38. Designated Special Economic Zone Land Allocation, Development and Use Regime

1/ All norms or standards in respect of the development and use of special economic zone land shall be regulated exclusively by this Proclamation and Regulations enacted hereunder.

2/ Any other legal or administrative regime defining the terms of access to land, tenure of land, and the use of urban or rural land and bidding system shall not apply in respect of designated special economic zone land.

3/ Details regarding special economic zone land site registration, plot leasing, sub-lease, title deeds, leasehold certificate, building standard, occupancy, site development, construction, and safety and supply of utilities shall be specified in a Directive to be enacted by the Board.

## 39. Acquisition of Land Dedicated for Special Economic Zone Development

Designation may involve a developed or undeveloped land which the applicant may acquire from the land bank plot held by the Corporation, or land allocated by a regional administration, or from private or public leaseholders of such land.

https://t.me/customsclearingagents
https://t.me/customsclearingagents

## ፵. በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የሚገኝ የለማ ወይም ያልለማ መሬት ስለመመደብ

፩/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የሚገኝ የለማ ወይም ያልለማ መሬት ያለቦርዱ የፅሁፍ ፈቃድ ለሌላ አካል ጥቅም ሊተላለፍ አይችልም።

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ ላይ በተመለከተው ሥርዓት መሰረት የለማ ወይም ያልለማ መሬት ለልዩ ኢኮኖሚ ዞን ንዑስ አልሚ፣ ለድርጅት ወይም ለተፈቀደለት ሌላ ተጠቃሚ ሊተላለፍ ይችላል። በዚህ አግባብ የሚያዘው ከፍተኛ የመሬት መጠን እና የሚጠበቁ ሌሎች ጉዳዮች ዝርዝር በደንብ ወይም በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፫/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳዳሪ የአስተዳዳሪ ስምምነቱ በኮሚሽኑ ሲፀድቅ እና የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሲሰጥ በአልሚው ወይም ንዑስ-አልሚው ስም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬትን ሊይዝ ወይም ሊያስተዳድር ይችላል።

፬/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት የድርጅት ስምምነቱ በኮሚሽኑ ሲፀድቅ እና የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሲሰጥ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ መሬት በንዑስ ሊዝ ሥርዓት ሊይዝ ይችላል፡፡

## 40. Allocation of a developed or Undeveloped Special Economic Zone Land

1/ No parcel of developed or undeveloped land of a special economic zone may be alienated for use by any entity without the written permission of the Board.

2/ Without prejudice to the stipulation of Sub-Article (1) of this Article, a developed or undeveloped land may be allocated to a special economic zone sub-developer, enterprise, or other authorized end-user in accordance with procedures specified under this Proclamation and Regulations or Directives enacted hereunder. In respect of a special economic zone sub-developer, the maximum ratio of land size that can be acquired in accordance with such procedure and other required conditions shall be prescribed in a Regulation or Directive.

3/ A special economic zone operator may possess and administer a special economic zone land on behalf of a developer or sub-developer upon approval of an operator agreement and issuance of investment permit by the Commission.

4/ A special economic zone enterprise may possess land within a special economic zone through a sub-lease system upon approval of an enterprise agreement and issuance of investment permit by the Commission.

https://t.me/customsclearingagents

**፵፩. በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የሚገኝ ያልለማ መሬት ለልዩ ዓላማ ስለመመደብ**

፩/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ማናቸውንም ያልለማ መሬት ለየትኛውም አላማ ቢሆን ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ አይፈቀድም።

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ማናቸውም ነባር ድርጅት በተለይ ስለ ካፒታል፣ የኢኮኖሚ አዋጭነት፣ የፋይናንስ አቅም፣ እና የግንባታ ማጠናቀቂያ ጊዜን አስመልክቶ ቦርዱ ያወጣቸውን መስፈርቶች ካሟላ እና ስምምነት ከገባ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የሚገኝ ያልለማ መሬት ክፍልን ለመያዝ እና የማምረቻ እቃዎችን፣ ህንፃዎችን እና ተያያዥ መሰረተ-ልማቶችን ለመገንባት ይችላል።

፫/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የሚገኝ የለማ ወይም ያልለማ መሬት ለሠራተኞች መኖሪያ ግንባታ ዓላማ ለልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ፣ ንዑስ አልሚ ወይም ድርጅት ሊመደብ ይችላል፡ ሆኖም ቦርዱ ፈቃድ የሚሰጠው ፕሮጀክቱ ከልዩ ኢኮኖሚ ዞኑ ማስተር ፕላን ጋር የተጣጣመ ስለመሆኑ፣ የቤት ችግርን በማስወገድ ረገድ የሚኖረውን አስተዋፅኦ፣ የአመልካቹን የፋይናንስ አቅም፡ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች ግምት ውስጥ በማስገባት እና አመልካቹ የፈቃዱን ሁኔታዎች አስመልክቶ ስምምነት የገባ እንደሆነ ብቻ ነው።

**41. Allocation of undeveloped special economic zone land for special purposes**

1/ Undeveloped special economic zone land may not be transferred to any end user for any purpose.

2/ The stipulation of Sub-Article (1) of this Article notwithstanding, an existing enterprise may acquire an undeveloped parcel of land situated within a special economic zone to construct manufacturing plants, buildings, and associated infrastructure, provided that it complies with the specific requirements established by the Board regarding capital, economic feasibility, financial capacity, and construction milestones, and enters into a specific agreement to such effect.

3/ The stipulation of Sub-Article (1) of this Article notwithstanding, a developed or undeveloped land situated within a special economic zone may be allocated to a developer, sub-developer, or enterprise for purposes of constructing employees' residential quarter where such is authorized by the Board, provided that the Board shall dispense the authorization only after evaluating the compatibility of the proposed project with the zone's master plan, the contribution of the project to alleviate housing shortages, the financial capacity of the applicant, and other relevant factors, and where the applicant enters into a specific agreement regulating the terms and conditions of the authorization.

https://t.me/customsclearingagents

፬/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የሚገኝ የለማ ወይም ያልለማ መሬት ለሰራተኞች መመገቢያ እና ተያያዥ መሰረተ-ልማት ግንባታ አገልግሎት ለድርጅት እንዲመደብ ቦርዱ ሊወስን ይችላል። ሆኖም የፕሮጀክት ሀሳቡ ከልዩ ኢኮኖሚ ዞን ማስተር ፕላን ጋር የሚጣጣም እና የደህንነት ጥበቃ ደረጃዎችን የሚያሟላ መሆን ይኖርበታል።

፭/ የልህቀት ማዕከል፣ የኢንኩቤሽን ማዕከል፣ የምርምር ማዕከል፣ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር ማዕከል፣ የማከማቻ አገልግሎት መስጫ፣ የጥራትና ቁጥጥር አገልግሎት መስጫ፣ ቤተ-ሙከራዎች እና ተመሳሳይ መሰረተ-ልማቶችን ጨምሮ ስትራቴጂያዊ ለሆኑ አገልግሎቶች አላማ የሚውል የልዩ ኢኮኖሚ ዞን የለማ ወይም ያልለማ መሬት የአልሚውን የመሰረተ-ልማት ወጪ ብቻ በሚሸፍን የሊዝ ሂሳብ እንዲመደብ ቦርዱ ሊያዝ ይችላል። ሆኖም ይህ የአልሚው ግዴታ ተፈፃሚ የሚሆነው አስቀድሞ በአልሚ ስምምነት ላይ ሲገለፅ ብቻ ነው።

፮/ ቦርዱ በኮርፖሬሽኑ ይዞታ ስር የሚገኝ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬት ከፍተኛ እሴት ላለው የንግድ አገልግሎት ስራ እንዲለማ የሚቀርብ ጥያቄን በተመለከተ የቀረበው ፕሮጀክት ከማስተር ፕላኑ እና ከዞኑ ስፓሻል ልማት እቅድ ጋር የሚጣጣም መሆኑን በማረጋገጥ ሊፈቅድ ይችላል።

4/ Notwhitstanding the stipulation of Sub-Article (1) of this Article the Board may decide to allocate a special economic zone land parcel to an enterprise for purposes of constructing employee canteen and associated infrastructure, provided that the proposal is compatible with the special economic zone's master plan and complies with safety standards.

5/ The Board may require the special economy zone developer to allocate a developed or undeveloped land parcel situated within a special economic zone to cater for requirements of strategic services, including centers of excellence, incubation centers, research centers, university-industry linkage centers, storage facilities, quality control facilities, laboratories, and similar infrastructure; such land parcel may be allocated on the basis of offsetting infrastructure development expenses, provided that any such obligation is stipulated in advance in a developer agreement.

6/ The Board may authorize the Corporation to develop a special economic zone land in its possession for high-end business services provided that the project is compatible with the zone master plan and the zone's spatial development plan.

https://t.me/customsclearingagents

**፵፪. <u>በኮርፖሬሽኑ የተያዘ መሬት በጨረታ ስለመመደብ</u>**

፩/ ኮርፖሬሽኑ በመሬት ባንክ የያዘው መሬት ለልዩ ኢኮኖሚ ዞን መጠቀሚያ የሚሆን የመኖሪያ ቤት መሰረተ-ልማት ግንባታ ለማካሄድ በጨረታ እንዲተላለፍ ጨረታ ሊያወጣ ይችላል።

፪/ የቤት አልሚዎች ልምድን፣ የፋይናንስ እቅድ፣ የፋይናንስ አቅም እና ዋስትናን ጨምሮ የአካባቢ፣ የማህበራዊ እና የዓለማቀፍ ሰራተኞች ድርጅት ዝርዝር ደረጃዎችን መሰረት በማድረግ፣ የመሬት አጠቃቀም መስፈርቶችን፣ በተመጣጣኝ የኪራይ ሥርዓት ለመገዛት ያላቸውን ፍላጎት እና የግንባታውን የጊዜ ማእቀፍ አስመልክቶ የሚቀመጡ መለኪያዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ይመዘናሉ።

፫/ ቦርዱ በተሻለ ደረጃ መስፈርቶቹን ለሚያሟላ ተጫራች መሬት እንዲሰጥ ይወስናል፡፡

**፵፫. <u>በኮርፖሬሽኑ የተያዘ መሬት ያለጨረታ ስለመመደብ</u>**

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀፅ ፵፪ ድንጋጌ ቢኖርም ኮርፖሬሽኑ በማንኛውም የቤት አልሚ ማመልከቻ ላይ በመመርኮዝ መሬት በጨረታ ሂደት ውስጥ ሳይገባ እንዲመደብ የሚቀርብን ጥያቄ ሊቀበል ይችላል።

፪/ የቤት አልሚው የአንቀፅ ፵፪ ቴክኒካዊ መስፈርቶችን የሚያሟላ ከሆነ እና የቀረበው ፕሮጀክት፡-

ሀ) ለልዩ ኢኮኖሚ ዞኑ በተለየ ሁኔታ ተግዳሮት የሆነ የቤት አቅርቦት ችግርን ለመቅረፍ አስፈላጊነቱ ከተረጋገጠ፣

**42. <u>Allocation of Land Held by the Corporation Through Auction</u>**

1/ The Corporation may initiate auction proceedings to allocate land held under its land bank for purposes of constructing housing infrastructure for use by a special economic zone.

2/ Housing developers shall be evaluated on the basis of experience, financial plans, including financial capacity and guarantees, proposed environmental, social and International Labor Organization-specific standards, and taking into consideration requirements of land use, affordable rental regime, and construction milestones.

3/ The Board shall approve the allocation of land to the highest evaluated proposal.

**43. <u>Allocation of Land Held by the Corporation Without Auction</u>**

1/ The stipulation of Article 42 of this Proclamation notwithstanding, the Corporation may accept a proposal by a housing developer for allocation of land without auction procedures.

2/ The Corporation shall submit its application to the Commission where the applicant complies with the technical requirements set under Article 42, and the proposed project:

a) is considered particularly crucial to alleviate acute housing supply challenges affecting the special economic zone;

https://t.me/customsclearingagents

ለ) የራስ አቅም በመጠቀም በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚጠናቀቅ ከሆነ፣

ሐ) በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ይኖራሉ ተብለው የሚገመቱ ሰራተኞችን ትርጉም ባለው ደረጃ ማስተናገድ የሚችል ከሆነ፣

ኮርፖሬሽኑ ጥያቄውን ለኮሚሽኑ ማቅረብ ይችላል።

፫/ ቦርዱ በኮሚሽኑ ምክረ-ሀሳብ መሰረት የመሬቱን ምደባ ሊያፀድቅ ይችላል።

## ፵፬. የመኖሪያ ቤት አልሚ ስምምነት የመግባት ግዴታ

፩) በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ በጨረታ ወይም በቀጥታ ምደባ መሬት የተሰጠው የቤት ፕሮጀክት አልሚ ከኮሚሽኑ እና ከልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚው ወይም ሕጋዊ ውክልና የተሰጠው አስተዳዳሪ ጋር ስምምነት መግባት አለበት።

፪) ስምምነቱ ከአስራ ስምንት ወራት የማይበልጥ የግንባታ ስራዎች ማጠናቀቂያ ምእራፎችን፣ የተፈቀዱ የመሬት አጠቃቀም አይነቶችን፣ ከዓለማቀፉ የሰራተኞች ድርጅት የሰራተኞች መኖሪያ መመሪያ ጋር የሚጣጣም የሕንፃ ዲዛይን እና ቤቶች ህግጋት፣ የመኖሪያ እፍጋት፣ እና ኮርፖሬሽኑ የሚያስቀምጠውን የአፈፃፀም ዋስትና የሚገልጽ መሆን አለበት።

፫/ በቦርዱ በሌላ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር የቤትአልሚው በአካባቢው የሊዝ ዋጋ እና በልዩ ኢኮኖሚ ዞኑ ውስጥ ለመሰረተ ልማት የወጣ ወጪን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሚተመነው መሰረት የሊዝ ዋጋ መክፈል አለበት።

b) can be completed in a shorter period of time using own capital, and

c) is capable of benefiting a significant proportion of employees projected to be retained within the special economic zone.

3/ The Board may approve the land allocation based on recommendation of the Commission.

## 44. Requirement to enter a housing development agreement

1/ A housing project developer granted a special economic zone land parcel through auction or direct allocation shall enter into agreement with the Commission and the developer, or the operator if so authorized.

2/ Such agreement shall specify construction milestones whose timeframe shall not exceed eighteen months, the permitted types of uses of the land, building designs and housing regulation that comply with International Labor Organization's Workers Housing Recommendation, residential density, and any performance bond which the Corporation may impose as appropriate.

3/ Unless decided otherwise by the Board, the housing developer shall pay a lease price which shall be fixed based on local lease values of such land and taking into account infrastructure expenses invested on the special economic zone land.

https://t.me/customsclearingagents

፵፭. **የመሬት ምደባ ሕጎች እና አሰራሮች ሲጣሱ ስለሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች**

ፈቃድ ሳይገኝ ወይም የዚህን አዋጅ እና ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ ላይ የተመለከቱ ሁኔታዎችን በጣሰ መልኩ የሚደረግ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬት ክፍልን ለሶስተኛ ወገን የማስተላለፍ ድርጊት የአልሚነት ወይም አስተዳዳሪነት ፈቃድ እገዳ ወይም ስረዛን ጨምሮ የአስተዳደር ቅጣት ያስከትላል።

፵፮. **ለመሬት፣ ህንፃ እና ንብረቶች የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ስለመስጠት**

፩/ በክልል አስተዳደር የተመደበ እና በመሬት ባንክ እንዲያዝ የታሰበን መሬት ኮርፖሬሽኑ በሳይት ፕላን ወይም ሌላ ተመሳሳይ ሥርዓት የመቀበል መብት የሚኖረው ሲሆን፣ የሚመለከተው የክልል መንግስት አካል የሊዝ ያዥነት የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

፪/ ኮርፖሬሽኑ መሬቱን በራሱ ሊያለማው ወይም በቦርዱ ውሳኔ ወደ ሌላ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ ወይም ንዑስ አልሚ በንዑስ-ሊዝ ሊያስተላልፍ ይችላል።

፫/ ከኮርፖሬሽኑ የመሬት ባንክ መሬት ያገኘ አልሚ የሊዝ ስምምነት የመግባት ግዴታ አለበት፡፡ ስምምነቱ ከተፈረመ ጊዜ ጀምሮ ባሉት ሰባት ተከታታይ ቀናት ውስጥ ከኮሚሽኑ የሊዝ ያዥነት የምስክር ወረቀት ያገኛል።

፬/ በዚህ አዋጅ መሰረት ከኮርፖሬሽኑ ነባር የዞን ልማት ወይም ከግል አልሚ መሬት ያገኘ ድርጅት የንዑስ ሊዝ ስምምነት የመፈረም ግዴታ አለበት። ስምምነቱ ከተፈረመ ጊዜ ጀምሮ ባሉት ሰባት ተከታታይ ቀናት ውስጥ

45. **Administrative Measures for Violations of Land Allocation Rules and Procedures**

The transfer of any economic zone land parcel to a third party without authorization or in violation of the rules established under this Proclamation and Regulations and Directives issued hereunder shall entail administrative measures, including the suspension or revocation of a developer or operator permit.

46. **Issuance of Title Documents for Land, Buildings and Assets**

1/ In relation to land allocated by regional administration and intended to be held in the land bank plot, the Corporation shall have the right to receive such land through site-plans or similar arrangements and secure a leasehold certificate from the appropriate regional agency.

2/ The Corporation may develop such land itself or transfer the same to other special economic zone developer or sub-developer through a sub-lease pursuant to a decision of the Board.

3/ A developer that secures land from the Corporation’s land bank plot shall conclude a lease agreement and receive a lease-hold certificate within Seven consecutive days of the signing of such agreement.

4/ An enterprise that acquires land parcel from the Corporation’s existing zone development or a private developer in accordance with procedures established under this Proclamation shall conclude a sub-lease agreement and receive a sub-leasehold

https://t.me/customsclearingagents

የንዑስ ሊዝ ያዥነት የምስክር ወረቀት ከኮሚሽኑ ያገኛል።

፭/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የፋብሪካ ህንፃ ወይም ተመሳሳይ ንብረት የገዛ ድርጅት ኮሚሽኑ በዘረጋው ሥርዓት መሰረት የሽያጭ ውል የገባ እንደሆነ ስምምነቱን ባደረገ በሰባት ቀናት ውስጥ ከኮሚሽኑ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ያገኛል። ውለታው የፋብሪካ ሼድ ወይም ተመሳሳይ ልማት ኪራይን የሚመለከት ከሆነ ኮሚሽኑ ውሉን ይመዘግባል።

፮/ የሊዝ ያዥነት ወይም የንዑስ-ሊዝ ያዥነት የምስክር ወረቀት እና የባለቤትነት ሰነዶች የሚያካትቱት ዝርዝር ጉዳይ በተመለከተ ቦርዱ መመሪያ ያወጣል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ስለ ግንባታ እና ፈቃድ አሠራሮች

### ፵፯. ስለሕንፃ ደንቦች

የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች ቢኖሩም የሕንፃዎች፣ የመሰረተ ልማቶች እና የተያያዥ መዋቅሮች ልማት እና ግንባታ ስራ በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ተከትሎ ኮሚሽኑ ከሚመለከተው ባለስልጣን ጋር በመቀናጀት በሚያወጣው መመሪያ ይመራል፡፡

### ፵፰. ዲዛይን ስለማፅደቅ እና የግንባታ ፈቃድ ስለመስጠት

፩/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሰረተ ልማት፣ የህንፃዎች፣ የመገልገያ ፋሲሊቲዎች ወይም ማንኛውንም ግንባታ ለማካሄድ የሚፈልግ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ፣ አስተዳዳሪ፣ ድርጅት ወይም አካል

certificate within Seven consecutive days of the signing of such agreement.

5/ A title deed shall be issued within seven consecutive days to an enterprise that purchases a factory building or similar facility within a special economic zone, provided that the enterprise shall conclude a sale agreement in accordance with a system put in place by the Commission; in case of rental of a factory shed or a similar facility, the Commission shall register the contract.

6/ Details of the contents of leasehold or sub-leasehold certificate and title deeds shall be specified through a Directive to be issued by the Board.

## PART NINE

## CONSTRUCTION AND PERMIT PROCEDURES

### 47. Building Norms

The stipulation of any other law notwithstanding, the development and construction of buildings, infrastructure and related structures within special economic zones shall be governed by this Proclamation and Directives to be adopted by the Commission in coordination with the competent authority.

### 48. Approval of Design and Issuance of Construction Permit

1/ Any special economic zone developer, operator, enterprise or entity intending to carry out construction of an economic zone infrastructure, building, facility, or any other construction shall submit a detailed project

https://t.me/customsclearingagents

ዝርዝር የፕሮጀክት ዲዛይን እና የግንባታ እቅድ በማስገባት ከኮሚሽኑ የግንባታ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

design and construction plan and secure a construction permit from the Commission.

፪/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት የሚቀርብ ማመልከቻ በአልሚነት፣ አስተዳዳሪነት ወይም ድርጅት ስምምነት ላይ ከተመለከቱ፡ አነስተኛ የዞን ዲዛይን መስፈርቶች ጋር የሚስማማ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

2/ Any application submitted by a developer, operator, or enterprise must demonstrate that the proposal complies with minimum zone design requirements stipulated under the developer or operator agreement.

፫/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት ከኮሚሽኑ ጋር የሚያደርገው ስምምነት የግንባታውን አፈፃፀም እና የሚጠናቀቅበት ዋና ዋና የጊዜ ምእራፎችን የሚይዝ መሆን አለበት።

3/ The agreement which a special economic zone developer, operator or enterprise concludes with the Commission shall, among others, regulate implementation of the construction and specific milestones of the project.

፬/ ኮሚሽኑ ፈቃዶችን ይሰጣል፣ አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል፡፡

4/ The Commission shall issue permits and follow through their implementation.

**፵፱. <u>የግንባታ ዕቃዎች መጠን ሰነድ ስለማረጋገጥ እና ማፅደቅ</u>**

**49. <u>Authentication and Approval of Bill of Quantity Document</u>**

፩/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ከሚተገበር ፕሮጀክት አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በአልሚ፣ አስተዳዳሪ፣ በድርጅት ወይም ሌላ አካል የሚቀርብ የግንባታ ሥራ ዝርዝርን የሚመለከት ሰነድ በኢትዮጵያ ወይም በውጭ ሀገር በሚገኝ ብቃት ያለው ባለሙያ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ ሆኖም ኢትዮጵያ ውስጥ ፈቃድ ባለው መሀንዲስ፣ አርክቴክት ወይም የግንባታ ዕቃዎች መጠን ሰርቬየር መረጋገጥ አለበት።

1/ A bill of quantity document submitted by a developer, operator, enterprise, or any other entity in respect of projects implemented within a special economic zone may be prepared by a competent professional in Ethiopia or abroad, but shall always be verified by an authorized engineer, architect or quantity surveyor in Ethiopia.

፪/ ኮሚሽኑ የቀረቡ ሰነዶችን ከመረመረ በኋላ የግንባታ ዕቃዎች መጠን ሰነዱን ሊያፀድቅ ወይም ውድቅ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2/ After examining all documents submitted, the Commission may approve or reject the bill of quantities document.

https://t.me/customsclearingagents
https://t.me/customsclearingagents

**፶. <u>የዲዛይን እና ግንባታ ማሻሻያ ወይም ማስፋፊያ ፈቃድ ስለመስጠት</u>**

፩/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ከሚከናወኑ ሥራዎች ጋር በተያያዘ ማናቸውም የፕሮጀክት ዲዛይን ወይም ግንባታ ማሻሻል ሥራ በአልሚ፣ በአስተዳዳሪ፣ በድርጅት ወይም ሌላ አካል ከመፈፀሙ በፊት በቅድሚያ በኮሚሽኑ መፈቀድ አለበት።

፪/ ለዚህ አላማ የሚቀርብ ማመልከቻ ፕሮጀክቱን ለማሻሻል ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን የሚያብራራ፣ ከልዩ ኢኮኖሚ ዞኑ ማስተር ፕላን እና ነባር መሰረተ-ልማቶች ጋር የሚጣጣም ስለመሆኑ ማረጋገጫ የሚሰጥ፣ የታሰበው ስራ የሰዎችን እና ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ የማያውክ መሆኑን የሚገልፅ፣ እንዲሁም የሰዎችን ጤና እና ደህንነት ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል።

፫/ ኮሚሽኑ ለቀረበው ጥያቄ ምላሹን በፅሁፍ በሰባት ተከታታይ ቀናት ውስጥ ያሳውቃል፡፡

**፶፩. <u>በአልሚ የሚካሄድ የፕሮጀክት ግንባታ ስለመጀመር እና ስለማጠናቀቅ</u>**

፩/ ማንኛውም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ የግንባታ ፈቃድ ካገኘበት ወይም የጅማሮ ስራዎችን በተመለከተ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከተሰጠበት እለት አንስቶ ባሉት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የግንባታ ስራ መጀመር አለበት።

፪/ አልሚው የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ የመንገድ ቅያሶችን፣ የመሰረታዊ አገልግሎት ልማቶችን፣ የደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ሥርዓት፣ የእሳት አደጋ መከላከያ፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት፣ የህፃናት ማቆያ፣ የአካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ መሰረተ-ልማት፣

**50. <u>Issuance of Permit for Modification or expansion of Design and Construction</u>**

1/ Any modification of design or construction of a project by a developer, operator, enterprise, or other entity in respect of undertakings within a special economic zone shall be subject to prior approval by the Commission.

2/ The application submitted for such purpose should state the reasons for the modification, assurance of its compatibility with the zone master plan and existing infrastructure, and that the envisaged work does not obstruct movement of people and vehicles and considers the health and safety of persons.

3/ The Commission shall communicate its decision in writing within Seven consecutive days.

**51. <u>Commencement and Completion of Project Construction by a Developer</u>**

1/ Any special economic zone developer shall commence construction work within six months from the date of issuance of a construction permit, or, in case of initial works, its investment permit.

2/ A developer shall complete all initial construction works including pavements, utilities, dry and liquid waste management system, fire prevention, one stop center, day-care facility, disability-friendly infrastructure, customs office, administrative buildings, and as the case may be, sheds and pollution

https://t.me/customsclearingagents

የጉምሩክ ቢሮ፣ የአስተዳደር ሕንፃዎች፣ እና እንደ አስፈላጊነቱ ሼዶች እና የብክለት መቀነሻ ስርዓት ግንባታዎችን ጨምሮ ሁሉን የመጀመሪያ ደረጃ ግንባታዎችን የግንባታ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከተሰጠበት እለት አንስቶ ባሉት ሰላሳ ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ አለበት።

፫/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም ኮሚሽኑ በአልሚው የቀረበ ማመልከቻን መሰረት በማድረግ እና የፕሮጀክቱን ስፋት እና ውስብስብነት ወይም ከአቅም በላይ የሆኑ ሌሎች ምክንያታዊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ጊዜውን ሊያራዝም ይችላል። ከፍተኛው የጊዜ ማእቀፍ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፬/ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌ ቢኖርም የፕሮጀክት እቅዶቹ አስቀድመው በኮሚሽኑ እስከፀደቁ ድረስ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚው የዞን ዋና ዋና መሰረተ-ልማቶችን እና አገልግሎት መስጫ ፋሲሊቲዎችን ደረጃ በደረጃ በሚከናወን የግንባታ ስራ እንዳያጠናቅቅ አይከለከልም፡፡

**፶፪. <u>በድርጅት የሚካሄድ ፕሮጀክት ግንባታ ስለመጀመር እና ስለማጠናቀቅ</u>**

፩/ የፋብሪካ ሕንፃ እና ተያያዥ ግንባታዎችን ለመገንባት ያቀደ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት የግንባታ ስራውን የግንባታ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከወሰደበት እለት አንስቶ ባለው ስድስት ወር ጊዜ ውስጥ መጀመር እና በአስራ ስምንት ወራት ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ አለበት።

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም በአልሚው ማመልከቻ መሰረት የፕሮጀክቱን ስፋት እና ውስብስብነት ወይም ከአቅም በላይ የሆኑ ሌሎች ምክንያታዊ

mitigation system within thirty-six months of the issuance of a construction or investment permit.

3/ The stipulation of Sub-Article (2) of this Article notwithstanding, the Commission may dispense additional time on the basis of an application by the developer, by considering the size or complexity of the project, or other reasonable grounds including a force majeure circumstance. The maximum timeframe shall be specified in a Board Directive.

4/ The stipulation of this Article notwithstanding, a developer shall not be precluded from engaging in phased development of major zone infrastructure and facilities, provided that such project plan is priorly approved by the Commission.

**52. <u>Commencement and Completion of Project Construction by Enterprise</u>**

1/ Any special economic zone enterprise who intends to install a factory building and related structures shall commence construction within Six months and complete within Eighteen months from the date of issuance of construction or investment permit.

2/ Notwithstanding the stipulation of Sub-Article (1) of this Article, the Commission may, based on an application by the enterprise, extend the time limit taking in to account the size or

https://t.me/customsclearingagents

ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ኮሚሽኑ ጊዜውን ሊያራዝም ይችላል።

፫ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው በሌሎች አካላት ለሚካሄዱ ግንባታዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**፶፫. <u>ፕሮጀክትን ካለማጠናቀቅ ጋር በተያያዘ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ</u>**

፩/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ ወይም ንዑስ አልሚ የተፈቀደለትን ተጨማሪ ጊዜ ጨምሮ የፕሮጀክቱን ግንባታ በዚህ አዋጅ ላይ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላጠናቀቀ፣ ቦርዱ ከኮሚሽኑ በሚመጣ ምክረ-ሀሳብ መሰረት የማስጠንቀቂያ አሰጣጥ ሂደትን በመከተል የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል።

፪/ ማንኛውም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት ወይም ሌላ አካል የተፈቀደለትን ተጨማሪ ጊዜ ጨምሮ የፕሮጀክቱን ግንባታ በዚህ አዋጅ ላይ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላጠናቀቀ ኮሚሽኑ የማስጠንቀቂያ አሰጣጥ ሂደትን በመከተል የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) መሰረት የኢንቨስትመንት ፈቃድ በታገደ ወይም በተሰረዘ ጊዜ ኮሚሽኑ ፈቃዱ ለታገደበት ወይም ለተሰረዘበት አካል የተሰጡ ማበረታቻዎች ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሱ፣ እንዲሁም አልሚን በተመለከተ የተሰጠው ስያሜ እንዲሰረዝ ለሚመለከተው አካል ምክረ-ሀሳብ ሊያቀርብ ይችላል።

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) መሰረት የኢንቨስትመንት ፈቃድ የታገደ ወይም የተሰረዘ እንደሆነ እና የተመለከተው

complexity of the project or other reasonable grounds.

3/ The provisions of this Article shall apply, mutatis mutandis, to any construction undertaken by other entities within a special economic zone.

**53. <u>Administrative Measure in Respect of Failure to Complete a Project</u>**

1/ Where a developer or sub-developer of special economy zone fails to complete construction within the time-frames indicated under this Proclamation, including the authorized extensions, the Board may, based on a recommendation from the Commission, suspend or revoke the developer investment permit, following notice procedures.

2/ Where an enterprise or other entity of special economy zone fails to complete construction within the time-frames indicated under this Proclamation, including authorized extensions, the Commission may suspend or revoke the investment permit, following notice procedures.

3/ Where an investment permit is suspended or revoked on the basis of sub-article (1) and (2) of this Article, the Commission may recommend to the competent authority that incentives approved in favor of the entity shall be withdrawn wholly or in part, and in the case of a developer, that withdrawal of the designation takes effect.

4/ Where an investment permit is suspended or revoked on the basis of Sub-Article (1) and (2) of this Article and the concerned entity had

https://t.me/customsclearingagents

አካል የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ንብረትን ለፋይናንስ ተቋማት በማስያዝ ብድር ወስዶ ከሆነ ኮሚሽኑ ስለፈቃዱ መታገድ ወይም መሰረዝ ለፋይናንስ ተቋማቱ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

taken loan from a financial institution by attaching a special economic zone asset, the Commission shall notify such institution in writing about the suspension or revocation.

## ክፍል አስር

## ስለ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ነዋሪነት

### ፶፬. የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ነዋሪ ስለመሆን

፩/ ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ ላይ የተደነገጉ መስፈርቶችን ሲያሟላ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ነዋሪ ሊሆን ይችላል።

፪/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ከዘጠና ቀናት በላይ ለመቆየት ያለመ ማንኛውም ሰው ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞኑ ከገባበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ በማመልከት እንደ ነዋሪ መመዝገብ አለበት።

፫/ የነዋሪነት መታወቂያ ለማግኘት ማመልከቻ ስለሚቀርብበት እና የምስክር ወረቀት ስለሚሰጥበት አግባብ፡ እንዲሁም የምስክር ወረቀት አይነት፣ የቆይታ ጊዜ፣ ተፈፃሚ የሚሆንበት አካባቢ፣ ተፈፃሚ ሁኔታዎች እና ክፍያን በተመለከተ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፬/ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ነዋሪ ምዝገባና መረጃ የማደራጀት እንዲሁም የቁጥጥር ሥራዎች በልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳዳሪ አማካኝነት በውክልና ወይም በሌላ አካል እንዲከናወን ሊወስን ይችላል፡፡

## PART TEN

## SPECIAL ECONOMIC ZONE RESIDENCY

### 54. Acquisition of Special Economic Zone Residency Status

1/ Any natural person meeting the requirements specified in this Proclamation and Regulation and Directive enacted hereunder may become a special economic zone resident.

2/ Any person who intends to stay within a special economic zone for more than Ninety days shall be registered as a resident by applying with the Commission within Five days of the date of first entry.

3/ The modalities for the application and issuance of a certificate of residency, including the types of certificates, duration, applicable site, conditions and fees shall be established in a Directive issued by the Commission.

4/ Subject to reporting obligations, the Commission may decide to delegate tasks pertaining to the registration of special economic zone residents, organization of the registry, and related regulatory works to a special economic zone operator or other entity.

https://t.me/customsclearingagents

**፶፭. <u>የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ነዋሪ መብትና ግዴታዎች</u>**

፩/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ነዋሪ የሚከተሉት መብቶች አሉት፡

ሀ) በተከለለ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ክፍል ውስጥ በነዋሪነት የምስክር ወረቀት ላይ ለተጠቀሰው ጊዜ የመኖር፣

ለ) በልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ ወይም አስተዳዳሪ አማካኝነት የሚቀርቡ አገልግሎቶችን ወይም አቅርቦቶችን በተመለከተ የተሻለ መግባባት እና ግንኙነት ለመፍጠር የሚያበቁ አደረጃጀቶችን የማቋቋም፣

፪/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ነዋሪ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉት፡

ሀ) በዚህ አዋጅ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር በግሉ ሊጠቀምባቸው ወደ ዞኑ ለሚያስገባቸው እቃዎች እና አቅርቦቶች አግባብነት ያላቸውን የጉምሩክ ቀረጥ፣ ታሪፍ፣ ግብር እና ሌሎች ክፍያዎችን የመክፈል፣

ለ) አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት የገቢ እና ሌሎች ግብሮችን የመክፈል፣

ሐ) የልዩ ኢኮኖሚ ዞኑን ህግና ደንብ አክብሮ የመኖርና የመንቀሳቀስ፣

**፶፮. <u>የልዩ ኢኮኖሚ ዞን የነዋሪነትን የምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ</u>**

ኮሚሽኑ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ነዋሪው በህግ የተመለከቱ ግዴታዎችን አጓድሎ ሲገኝ ወይም የነዋሪነት የምስክር ወረቀቱን ያገኘው በማሳሳት ወይም የሀሰት መረጃ በማቅረብ ከሆነ ለነዋሪው የ፺ ቀናት የቅድሚያ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት እና የመሰማት መብቱን በመጠበቅ የምስክር

**55. <u>Rights and Obligations of a Special Economic Zone Resident</u>**

1/ A special economic zone resident shall have the right to:

a/ live and reside in designated area of special economic zone for a duration specified in the certificate of residency;

b/ establish committees for enhanced communication and interaction with the developer and operator in respect of facilities and services availed within a special economic zone;

2/ A special economic zone resident shall have the obligation to:-

a) pay applicable customs duties, tariffs, taxes and other charges for goods and services admitted into a zone for personal use, unless it is provided otherwise;

b) pay personal income and other taxes in accordance with applicable laws;

c) comply with the special economic zone's laws and regulations.

**56. <u>Revocation of a certificate of residence</u>**

Subject to the provision of Ninety-days prior notice and implementation of due process safeguards, the Commission may revoke a certificate if a special economic zone resident fails to comply with the conditions of the law, or if the residency status was obtained

https://t.me/customsclearingagents

ወረቀቱን ሊሰርዝ ይችላል።

## ክፍል አስራ አንድ

## ለአልሚ፣ አስተዳዳሪ እና ድርጅት የሚሰጥ ማበረታቻ

**፶፯. ጠቅላላ የማበረታቻ ማዕቀፎች**

፩/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቁጥር ፭፻፲፯/፪ሺ፲፬ እና ደንቡን ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ ላይ የተደነገጉ ማበረታቻዎችን ያገኛል።

፪/ የዚህ አዋጅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም አልሚ፣ አስተዳዳሪ እና ድርጅት የሚከተሉትን ማበረታቻዎች ያገኛል።

ሀ) ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ለሚገቡ እና ከልዩ ኢኮኖሚ ዞን የሚወጡ እቃዎችን በተመለከተ ከሁሉም የቀረጥ እና ታክስ ክፍያ ነፃ የመሆን፣

ለ) ከጉምሩክ ክልል ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ለሚገቡ እቃዎች እና አገልግሎቶች የተጨማሪ እሴት ግብር ዜሮ ምጣኔ እና ቀጥተኛ ካልሆኑ የሀገር ውስጥ ግብሮች ነፃ የመሆን፣

ሐ) በባለሀብቱ በቀጥታ፣ በተቋራጭ ወኪሉ ወይም በተመዘገበ የሎጂስቲክስ ኦፕሬተር አማካኝነት ለራሱ ኢንቨስትመንት አገልግሎት የተገዙ የግንባታ ዕቃዎችን ከገቢ እና ሌሎች የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ነፃ ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን የማስገባት፣

through misrepresentation or false information.

## PART ELEVEN

## INCENTIVE GRANTED TO A DEVELOPER, OPERATOR OR ENTERPRISE

**57. General Scheme of Incentives**

1/ Any special economic zone developer, operator or enterprise issued with an investment permit shall be granted incentives specified under the Investment Incentives Regulation No.517/2022, and Directives issued thereunder.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, a developer, operator and enterprise shall be entitled to the following incentives.

a) exemption from payment of all types of taxes and duties for all imports and exports of goods into and out of a special economic zone;

b) zero rated VAT treatment and exemption from other indirect taxes for all goods and services entering a special economic zone from the customs territory;

c) right to import construction materials into the special economic zone for use by the investor free from all import and domestic taxes and duties, whether procured directly by the investor itself or through the agency of contractors or registered logistics operators;

https://t.me/customsclearingagents

መ) አግባብነት ያለውን ቀረጥ እና ታክስ በመክፈል እቃዎች እና አገልግሎቶችን ከልዩ ኢኮኖሚ ዞን ወደ ጉምሩክ ክልል የመላክ ወይም በጉምሩክ ክልል ለሚገኙ ነዋሪዎች የማቅረብ፣

ሠ) ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን በሚገቡ ማናቸውም የካፒታል ዕቃዎች ላይ ከሚከፈል ማንኛውም ቀረጥ እና ታክስ ክፍያ ነፃ የመሆን፣

ረ) ለባለአክሲዮኖች የሚከፈል የትርፍ ድርሻ ከገቢ ግብር ክፍያ ነፃ የመሆን፣

ሰ) የግብር እፎይታ በሚሰጥበት ወቅት በገቢ ግብር ላይ ተፈፃሚ ከሚደረግ የዊዝሆልዲንግ ሥርዓት ነፃ የመሆን፤

፫/ ዕቃ ወይም አገልግሎትን ወደ ውጪ በሚልኩ ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩ የውጭ ዜጎች ድርጅቱ የንግድ ፈቃድ ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ ለሚቆጠሩ አምስት ተከታታይ ዓመታት በደመወዛቸው ላይ የገቢ ግብር ክፍያ እፎይታ ያገኛሉ፡፡

፬/ በዚህ አዋጅ መሰረት በልዩ ኢኮኖሚ ዞኖች ውስጥ በአልሚዎች፣ በንዑስ አልሚዎች ወይም በድርጅቶች በሚያዙ የሊዝ ወይም የንዑስ ሊዝ ይዞታ መብቶች እና በሽያጭ ወይም በኪራይ ወይም በሌላ መንገድ በሚያዙ ቋሚ ንብረቶች ላይ የንብረት ታክስ አሰራር ቀሪ እንዲሆን ወይም የተለየ የንብረት ታክስ ምጣኔ ስርአት ተፈፃሚ እንዲደረግ አግባብነት ያለው አካል የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ሀገራዊ መርሀ-ግብር ልዩ አላማን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ይወስናል፡፡

፭/ ኮሚሽኑ ከገንዘብ ሚኒስቴር እና ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በመተባበር እና ቋሚ የጋራ ኮሚቴ በማደራጀት ማበረታቻዎች ለታለመላቸው አላማ

d) supply goods and render services from the special economic zone to the customs territory or to residents of the customs territory subject to payment of duties and taxes;

e) exemption from all types of taxes and duties for all capital goods entering into the special economic zone;

f) exemption from income tax on dividend distributed to shareholders;

g) exemption from withholding tax on income during tax holiday period.

3/ Foreign nationals employed by enterprises that export goods or services shall be exempt from taxes on employment income for Five consecutive years commencing from the date on which the enterprise obtains a business license.

4/ The appropriate authority shall take into consideration the unique objective of the national special economic zone scheme and decide to establish a mechanism to either waive or apply a favorable property tax regime in respect of lease-hold and sublease hold rights or immovable property rights acquired by developers, sub developers or enterprises through sale, rent or other procedures in accordance with this Proclamation.

5/ In coordination with the Ministry of Finance and the Customs Commission and by establishing a standing committee, the

https://t.me/customsclearingagents

መዋላቸውን ለመከታተል የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የአሠራር ስርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል።

Commission shall facilitate the establishment of a technology-assisted joint mechanism to ensure that incentives are being used for the intended purposes.

፮/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች ቢኖሩም አልሚዎች ከመሃል ኢትዮጵያ ርቀው በሚገኙ እና/ወይም ከፍተኛ የመሰረተ ልማት ችግር ባለባቸው ቦታዎች ወይም አካባቢዎች ሄደው ማልማት እንዲችሉ ቦርዱ ተጨማሪ ልዩ የማበረታቻ ስርዓት እንዲዘረጋ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

6/ The stipulations of Sub-Articles (1) and (2) of this Article notwithstanding, the Board may decide to establish additional incentives to attract investment in geographical areas that are further from the center and/or are affected by serious infrastructure deficit. The details shall be specified by a Regulation issued by Council of Ministeries.

**፶፰. <u>የግል መገልገያ ዕቃዎች</u>**

፩/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስራ ላይ የተሰማራ የውጭ ባለሀብት ወይም በውጭ ሀገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው የድርጅት ተቀጣሪ ወደ ኢትዮጵያ ለዚሁ አላማ የገባ እንደሆነ የግል መገልገያ ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ የማስገባት መብት አለው።

፪/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት ለኢንቨስትመንት አገልግሎት የሚውሉ የግል መገልገያ ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ የማስገባት መብት አለው።

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) መሰረት የግል መገልገያ ዕቃዎችን ያስገባ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) ተመሳሳይ መብት ላለው ሰው ያለቀረጥና ታክስ ክፍያ ማስተላለፍ፣ እንደገና ኤክስፖርት ማድረግ፣ ወይም

ለ) ተገቢውን ቀረጥና ታክስ በመክፈል ተመሳሳይ መብት ለሌለው ሰው ማስተላለፍ ይችላል፡፡

**58. <u>Personal effect</u>**

1/ A foreign investor, or an Ethiopian residing abroad, or a foreign employee of an enterprise operating within a special economic zone, entering Ethiopia for such engagement, shall have the right to import personal effects free of duties and taxes.

2/ A special economic zone developer, operator or enterprise shall have the right to import personal effects free of duties and taxes.

3/ Anyone importing personal effects pursuant to sub-article (1) and (2) of this Article may:

a/ transfer such personal effects to another person with similar privileges, or re-export without payment of duties and taxes, or

b/ transfer such personal effects to another person having no similar privileges subject to payment of duties and taxes.

https://t.me/customsclearingagents

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የግል መገልገያ ዕቃዎችን ማስተላለፍ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከማስተላለፉ በፊት ሥልጣን ካለው አካል ፈቃድ ማግኘት አለበት።

፭/ የግል መገልገያ ዕቃዎች እና ተጠቃሚዎች ዝርዝር ኮሚሽኑ የሚሰጠውን ምክረ-ሀሳብ መሰረት አድርጎ ሥልጣን ያለው አካል በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል አስራ ሁለት

## ሰራተኛን የሚመለከቱ ጉዳዮች፣ የውጭ ሀገር ዜጎች የስራ ፈቃድ፣ የመኖሪያ ፈቃድ፣ ቪዛ እና የክህሎት ሽግግር

### ፶፱. የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር እና አስተዳደር

፩/ የአሰሪ እና ሰራተኛ ሕጉ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ተፈፃሚ ይሆናል።

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም በሕግ፣ በኅብረት ስምምነት ወይም በሥራ ደንብ ለሠራተኛ የተሰጡ ጥቅሞችን ሳይነካ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ በሚገኙ አሰሪዎች እና ሰራተኞች መካከል የልዩ ኢኮኖሚ ዞንን ልዩ ባህርይ ግምት ውስጥ ያስገባ የስራ ውል ድርድር እንዲደረግ ኮሚሽኑ ሊፈቅድ ይችላል።

፫/ ለሕግ ተቃራኒ እስካልሆነ ድረስ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የሚሰሩ ሠራተኞች በየቀጣሪ ድርጅቶቹ የንግድ ሥራ አካሄድ እና በሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ይተዳደራሉ።

፬/ ኮሚሽኑ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ሥርዓታዊ በሆነ መንገድ ሠራተኞችን የመመልመል፣ ስልጠና የመስጠት፣ የመመዝገብ፣ የመመደብ እና የመቅጠር ሂደት ለማሳለጥ እንዲቻል

4/ A person who seeks to transfer an item pursuant to Sub-Article (3) of this Article shall secure approval from the competent authority before effecting any transfer.

5/ The list of personal effects and beneficiaries shall be prescribed in a Directive to be issued by the competent authority based on recommendation of the Commission.

## PART TWELVE

## LABOR AFFAIRS, EXPAT WORK PERMIT, RESIDENCE PERMIT, VISA AND TRANSFER OF SKILLS

### 59. Regulation and management of labor affairs

1/ The labor proclamation currently in force shall apply across all special economic zones.

2/ The stipulation of Sub-Article (1) of this Article notwithstanding, the Commission may, without prejudice to minimum benefits established under the law, collective agreement or work rules, authorize a labor contract to be negotiated between employers and employees operating within a special economic zone that takes into account the special economic zone's peculiar features.

3/ Employees within special economic zones shall be administered by enterprises according to their business requirements and employee work rules unless such are found to be contrary to law.

4/ The Commission shall, in collaboration with local labor bureaus and investors, cause the establishment of a labor service organization within each special economic zone to facilitate

https://t.me/customsclearingagents

ከአካባቢው የሰራተኞች ጉዳይ ቢሮ እና ከባለሀብቶች ጋር በመተባበር በእያንዳንዱ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን የሥራ አገልግሎት ተቋም እንዲደራጅ ያደርጋል።

፭/ ማንኛውም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት ሰራተኞች እና ሌሎች ነዋሪዎች ደህንነታቸው እና ጤንነታቸው በተጠበቀ ከባቢ የሚሰሩ መሆኑን ለማረጋገጥ አስገዳጅ የሥራ ጥበቃ እርምጃዎችን የመውሰድ ግዴታ አለበት።

**፷. የሰራተኞች ዝቅተኛ ደመወዝ እና ማትጊያ ሥርአት**

፩/ ኮሚሽኑ ዝቅተኛ የደመወዝ መጠን፣ የደመወዝ አይነት፣ የማትጊያ ሥርዓቶች፣ ዝቅተኛ የሰራተኛ መድህን፣ እና ሌሎች ለሰራተኞች የሚጠበቁ መብቶችን ለመወሰን፣ ተግባራዊ ለማድረግ እና ወጥ የሆነ ስርዓት ለመዘርጋት ከሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር፣ ከክልል ሠራተኛ ጉዳይ ቢሮዎች፣ የሠራተኛ ተወካዮች እና ከባለሀብቶች ጋር በትብብር ይሰራል።

፪/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተመለከቱ ጉዳዮች ወጥ በሆነ መንገድ በሠራተኞች እና ድርጅቶች መካከል በሚፈረሙ የስራ ውሎች ውስጥ መካተታቸውን ያረጋግጣል።

**፷፩. የሥራ ጉዳዮች ኮሚቴ ስለማቋቋም**

፩/ በእያንዳንዱ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የጋራ የሥራ ጉዳይ ኮሚቴ የሚባል ከኮሚሽኑ፣ ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም ከሚመለከተው ክልል ቢሮ፣ ከአስተዳዳሪ፣ ከድርጅቶች ተወካይ፣ እና ከሰራተኞች ተወካይ የተውጣጡ አባላትን የያዘ ተቋማዊ አደረጃጀት ይመሰረታል።

the systematic sourcing, training, registration, placement and recruitment of workforce within special economic zones.

5/ Any special economic zone operator or enterprise shall have the obligation to adopt mandatory labor protection measures to ensure that employees and other residents operate in safe and hygienic conditions.

**60. Minimum wage and benefit of employees**

1/ The Commission shall coordinate with the Ministry of Labor and Skills, local labor affairs bureaus, employees' representatives and investors to standardize and implement minimum wage levels, types of wages, award measures, minimum labor insurance, and other rights availed to employees.

2/ The Commission shall ensure that matters stated in sub-article (1) of this Article are uniformly included in contracts signed between enterprises and employees.

**61. Establishment of a Labor Affairs Committee**

1/ An institutional platform called labor affairs committee shall be established within each special economic zone comprised of representatives of the Commission, the Ministry of Labor and Skills, the Ministry of Industry or the pertinent regional counterpart, the operator, enterprises' representative, and employees' representative.

https://t.me/customsclearingagents

፪/ ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች አሉት፡

ሀ) የሠራተኞች መብቶች እና ግዴታዎች በኢንቨስትመንት ተቋሙ ማኔጅመንት እና በሠራተኞች መታወቃቸውን እና በአግባቡ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፣

ለ) ተከታታይ እና ወጥ የሆኑ የምክክር እና ግንኙነት መድረኮችን በመፍጠር በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፣ ውጥረት እና አለመግባባቶችን ይከላከላል፣

ሐ) ለምክክር እና አማራጭ የክርክር መፍቻ ዘዴዎች ቅድሚያ በመስጠት የግል እና የወል የሥራ ጉዳዮች እና አለመግባባቶችን ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ለመፍታት የሚያስችል፡ በአሰሪና ሰራተኛ ሕግ እና በዚህ አዋጅ የተመለከቱ መርሆዎችን መሰረት ያደረገ ሥርዓት ይዘረጋል፣

መ) ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የእውቀት፣ ክህሎት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ስለመደረጉ እና ምርታማነት ስለመጨመሩ ያረጋግጣል፣

ሠ) በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲሰፍን የሚያግዙ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

፫/ ኮሚሽኑ የኮሚቴውን ስራዎች ያስተባብራል፣ ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ እና የኮሚቴው አባላት አሰያየም ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

2/ The committee shall have the following duties and responsibilities:

a/ ensure that the rights and duties of workers are understood by the management of the investment entities and workers, and are implemented in practice;

b/ create conducive conditions and prevent tensions and conflicts within special economic zones by formulating a platform for continuous and structured consultation and engagement;

c/ devise mechanisms for efficient resolution of individual and collective labor issues and disputes in accordance with the principles enshrined under the labor law and this Proclamation, with priority accorded to dialogues and alternative dispute resolution mechanisms;

d/ in consultation with the Ministry of Industry, ascertain that the transfer of knowledge, skills and technology takes place and productivity increases within special economic zones;

e/ carry out other activities that help attain industrial peace within special economic zones;

3/ The Commission shall coordinate activities of the committee and facilitate that the committee discharges its responsibilities effectively. Detailed implementation and the designation of members of the committee

https://t.me/customsclearingagents

shall be specified in a Board Directive.

## ፷፪. ቪዛ እና የመኖሪያ ፈቃድ

፩) ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በአልሚዎች፣ አስተዳዳሪዎች፣ ወይም ድርጅቶች የሚቀጠሩ የውጭ ሀገር ሰራኞችን ቪዛ እና የመኖሪያ ፈቃድ አሰጣጥን ለማቀላጠፍ እንዲቻል በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ልዩ የኢሚግሬሽን ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል።

፪) ከኢንቨስትመንት ጋር ለተያያዘ ጉዞ ማንኛውም ከሀገሩ ውጪ ያለ የውጭ ሀገር ዜጋ ካለበት የውጭ ሀገር ሆኖ የኢትዮጵያ ቪዛ እንዲሰጠው ሊያመለክት ይችላል።

፫) ኮሚሽኑ በሚሰጠው ማረጋገጫ መሰረት ለልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ ወይም አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት ባለቤት ወይም ከፍተኛ ባለድርሻ ግለሰብ ለአምስት አመት የሚያገለግል የብዙ ጊዜ መመላለሻ ቪዛ ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።

፬) ኮሚሽኑ በሚሰጠው ማረጋገጫ መሰረት በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ለሚሰራ የውጭ ዜጋ ሰራተኛ፣ ስራ አስኪያጅ፣ ከዋና መስሪያ ቤት ለሚመጣ ስራ አስፈፃሚ፣ ለቦርድ አባል፣ ወይም ለከፍተኛ ባለሙያ ለሶስት አመት የሚያገለግል የብዙ ጊዜ መመላለሻ ቪዛ ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።

፭) ለውጭ ሀገር ሰራተኞች እና ለጥገኞቻቸው የሚሰጥ የመኖሪያ ፈቃድ ኮሚሽኑ እና አግባብነት ያለው የኢሚግሬሽን ተቋም በቅንጅት በሚፈጥሩት የተሳለጠ የአገልግሎት ሥርአት መሰረት ይከናወናል።

## 62. Visa and Residence Permit

1/ In coordination with the competent authorities, the Commission shall facilitate the establishment of a special immigration regime within economic zones to expedite the issuance of visas and residency permits of foreigners employed by developers, operators or enterprises.

2/ Any person who is outside his country of residence may apply for Ethiopian visa from a third country for purposes of investment-linked travel.

3/ Based on assurance from the Commission, a multiple entry visa valid for Five years or a residence permit may be issued to an owner or significant shareholder of a special economic zone developer, operator or enterprise.

4/ Based on assurance from the Commission, a multiple entry visa valid for Three Years or a residence permit may be issued to a foreigner working in a special economic zone, to a manager, executive from headquarters, a board member or high-level professional staff.

5/ The issuance of residence permit of expat personnel and their dependents shall be expedited through a coordinated work of the Commission and the competent immigration agency.

https://t.me/customsclearingagents
https://t.me/customsclearingagents

፮) የቪዛ እና የመኖሪያ ፈቃድ አሰጣጥ ሁኔታ እና ስነ-ስርአት ዝርዝር አግባብነት ያለው የኢሚግሬሽን ተቋም ከኮሚሽኑ ጋር በቅርበት በመተባበር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፷፫. <u>የውጭ ዜጎች ሠራተኞች የሥራ ፈቃድ</u>**

፩/ ማንኛውም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያለው የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ፣ ንዑስ አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት በከፍተኛ ማኔጅመንት፣ በተቆጣጣሪነት፣ በአሰልጣኝነት እና በሌሎች የቴክኒክ ሥራዎች ላይ የሚሰማሩ የውጭ ሀገር ባለሙያዎችን መቅጠር ይችላል።

፪/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን የውጭ ሀገር ባለሙያዎች የሥራ ፈቃድን ለመስጠት ኮሚሽኑ ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር ሊተባበር ይችላል፡፡

፫/ በኢንቨስትመንት አዋጁ እና አዋጁን ተከትለው በወጡ መመሪያዎች ላይ የተደነገጉ ከሥራ ፈቃድ አሰጣጥ እና ከተተኪ ኢትዮጵያዊያን ሥልጠና ጋር የተያያዙ ሥርዓቶች፣ መብቶች እና ግዴታዎች እንደአግባብነታቸው በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ተጠቃሚዎች ለሚቀርቡ የሥራ ፈቃድ ማመልከቻዎችም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**፷፬. <u>የዕውቀት፣ ክህሎት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር</u>**

፩/ ኮሚሽኑ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ከሚመለከታቸው ሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች የክህሎት፣ እውቀት እና ቴክኖሎጂ ልማት እና ሽግግርን የሚያጎለብቱ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

6/ The modalities and procedures for the issuance of visa and residence permits shall be specified in a Directive adopted by the competent immigration agency in close collaboration with the Commission.

**63. <u>Work permit of expat employees</u>**

1/ Any special economic zone developer, sub-developer, operator or enterprise possessing an investment permit may hire expat personnel for top management, supervisory, training or other technical functions.

2/ The Comission may collaborate with the Ministry of Labor and Skills when issuing the work permit of expat personnel within a special economic zone.

3/ Detailed procedures, rights and obligations specified under the Investment Proclamation and Directives enacted thereunder pertaining to the issuance of work permit and conditions involving the training of substitute Ethiopians shall apply *mutatis mutandis* to all work permit applications by special economic zone end-users.

**64. <u>Transfer of knowledge, skills and technology</u>**

1/ In coordination with the Ministry of Industry and pertinent agencies, the Commission shall ensure that special economic zones foster the development and transfer of skills, knowledge and technology.

https://t.me/customsclearingagents

፪/ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ከኮሚሽኑ፣ ከአልሚዎች፣ አስተዳዳሪዎች እና ከድርጅቶች ጋር በመተባበር ለኢትዮጵያዊያን ሰራተኞች የክህሎት እና እውቀት ሽግግርን የሚያጎለብቱ የቴክኒክ እና ሙያ ሥልጠና ፕሮግራሞችን ይነድፋል፣ ያደራጃል፣ አተገባበሩን ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል።

፫/ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከኮሚሽኑ፣ ከግብርና ሚኒስቴር እና ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲፋጠን የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ የመንግሥት እና ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅቶች አጋርነትን ጨምሮ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና እድገትን የማፋጠን፣ ምርታማነትና የምርት ጥራትን የማሳደግ፣ የግብዓት አቅርቦት እና የገበያ ትስስርን የማረጋገጥ፣ እንዲሁም ጥናትና ምርምር እንዲካሄድ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

፬/ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ የተጣሉበትን ኃላፊነቶች ውጤታማ በሆነ መንገድ እና በዘላቂነት ለመወጣት እንዲችል ተገቢ የሥራ ክፍሎቹ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ቅርንጫፍ በመክፈት ሥራ እንዲመሩ ያደርጋል፡፡

2/ In collaboration with the Ministry of Industry, the Commission, developers, operators and enterprises, the Ministry of Labor and Skills shall design and organize technical and vocational training programs that facilitate the transfer of skills and knowledge to Ethiopian workers; it shall set up mechanisms to follow through their implementation.

3/ In collaboration with the Commission, Ministry of Agriculture, and the Ministry of Innovation and Technology, the Ministry of Industry shall put in place a mechanism that facilitates technology transfer, including partnerships between government and special economic zone enterprises, to expedite the transfer and advancement of technology, increase productivity and quality of products, ensure supply of input and creation of market linkages, and cause the conduct of studies and research.

4/ The Ministry of Industry shall cause its administrative units open operations within special economic zones in order to discharge its responsibilities under this Proclamation more effectively and in a sustainable manner.

https://t.me/customsclearingagents

https://t.me/customsclearingagents

## ክፍል አስራ ሶስት

## የኢንቨስትመንት ዋስትና፣ ጥበቃ እና እንክብካቤ

**፷፭. እኩል እንክብካቤ የማግኘት መብት**

በሌላ ሁኔታ ካልተመለከተ በቀር ማንኛውም የውጭ ባለሀብት በግሉ ወይም ከሀገር ውስጥ ባለሀብት ጋር በመቀናጀት ያለ ምንም የባለቤትነት ገደብ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚነት፣ አስተዳዳሪነት ወይም ድርጅትነት መሳተፍ ይችላል፡፡

**፷፮. ዋስትና እና ጥበቃ**

፩) መንግሥት ለህዝብ አገልግሎት ዓላማ ሲፈለግ፣ አድሎን በማያስከትል መልኩ፣ ተገቢ የሕግ አካሄድን ተከትሎ፣ እና ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ ፈጣንና በተቀላጠፈ ሁኔታ ተከፍሎ ካልሆነ በስተቀር በማናቸውም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ኢንቨስትመንት ላይ የመውረስ እርምጃ ሊወስድ አይችልም።

፪) በውጭ ኢንቨስትመንት ላይ የመውረስ እርምጃ ተግባራዊ የተደረገ እንደሆነ የካሳ ክፍያው በዓለማቀፍ የፋይናንስ ገበያ ሊቀያየር በሚችል ገንዘብ መፈጸም አለበት።

፫) ከሕግ አግባብ ውጭ ንብረትን የመውረስ ሥራ የተፈፀመ እንደሆነ ንብረቱን እንዲለቅ የተደረገ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት ድርጊቱ ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮ ንብረቱ እስከተመለሰበት ጊዜ ድረስ በህግ መሰረት ከሚታሰብ ወለድ ጋር የተወሰደበት ኢንቨስትመንት እንዲመለስለት ይደረጋል።

፬) ስለ ንብረት አወራረስ እና ሕጋዊነት ስለማይኖረው የንብረት መውሰድ፣ ስለ ካሳ ክፍያ እና ንብረት አመላለስ ዝርዝር አግባብ

## PART THIRTEEN

## INVESTMENT GUARANTEE, PROTECTION AND TREATMENT

**65. National Treatment**

Unless provided otherwise, any foreign investor may participate as a special economic zone developer, operator or enterprise, individually or jointly with domestic investor, without any restriction of ownership threshold.

**66. Guarantee and Protection**

1/ No special economic zone investment may be subjected to an expropriation measure by the government except on non-discriminatory basis, when such is required for public purpose, and following due process, and subject to prompt and effective payment of adequate compensation.

2/ When expropriation applies in respect of a foreign investment, compensation shall be paid in currency convertible in international financial markets.

3/ Where any unlawful expropriation takes place, a special economic zone developer, operator or enterprise shall be entitled to restitution of its investment together with a legal interest calculated as of the time of the expropriation until restitution of the investment is effectuated.

4/ The provisions of the applicable law shall apply with respect to the manner of expropriation and determination of what

https://t.me/customsclearingagents

ባለው ሕግ የተደነገገው ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፭) በዚህ አንቀጽ የተደነገጉ ድንጋጌዎች በወንጀል ምክንያት አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት የሚፈፀም የንብረት መውረስ እርምጃን አያስቀሩም።

## ክፍል አስራ አራት

## ስለ ጉምሩክ አገልግሎት

### ፷፯. በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስለሚኖር የጉምሩክ ቁጥጥር

የልዩ የኢኮኖሚ ዞን ሙሉ የጉምሩክ ቁጥጥር ይደረግበታል፡፡

### ፷፰. የተሳለጠ የጉምሩክ አገልግሎት ስለመስጠት

የጉምሩክ ኮሚሽን በሌላ ሕግ የተቀመጠ ድንጋጌ ቢኖርም በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የተቀላጠፈ፣ ለዘርፉ ልዩ ትኩረት ያደረገ፣ እና በዘርፉ ፍላጎት የተቃኘ የጉምሩክ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአሠራር መመሪያ ያወጣል፤ ይፈጽማል፡፡

### ፷፱. ወደ ሀገር ስለሚገባ ወይም ከሀገር ስለሚወጣ ዕቃ

፩/ ከልዩ ኢኮኖሚ ዞን ወደ ጉምሩክ ክልል የገባ ዕቃ ከውጭ ሀገር እንደገባ ዕቃ ተቆጥሮ ተገቢው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ይፈጸምበታል፡፡

፪/ ከልዩ ኢኮኖሚ ዞን ወደ ውጭ ሀገር፣ ወይም ከጉምሩክ ክልል ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን፣ ወይም ከአንዱ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ወደ ሌላ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን፣ ወይም በአንድ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ከሚገኝ አንድ ተጠቃሚ ወደ ሌላ

constitutes unlawful expropriation, compensation or restitution.

5/ Nothing under this Article shall preclude expropriation measure adopted pursuant to the appropriate penal law in relation to specific crimes committed by the investor.

## PART FOURTEEN

## CUSTOMS SERVICE

### 67. Customs Control in Special Economic Zone

A special economic zone is fully subject to customs control.

### 68. Establishment of Facilitative Customs Service

A stipulation under any law notwithstanding, the Customs Commission shall issue and implement an operational directive establishing the provision of tailored; facilitated and streamlined customs procedures within a special economic zone.

### 69. Customs Clearance of Imported or Exported Goods

1/ Goods brought into the customs territory from a special economic zone shall be treated as imported goods and be subject to appropriate customs procedures.

2/ Goods transferred from a special economic zone to a foreign country, or from the customs territory to a special economic zone, or from one special economic zone to another special economic zone, or from one user to

https://t.me/customsclearingagents
https://t.me/customsclearingagents

ተጠቃሚ የተላለፈ ዕቃ እንደ ወጪ ዕቃ ተቆጥሮ ተገቢው የጉምሩክ ስነ ስርዓት ይፈጸምበታል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት በተጠቃሚዎች መካከል በሽያጭ ወይም በሌላ ህጋዊ መንገድ የሚፈጸም የዕቃ ትልልፍ ወይም ቅብብሎሽ ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነጻ ይደረጋል፡፡

፬/ የጉምሩክ ኮሚሽን ሲፈቅድ በልዩ የኢኮኖሚ ዞን ሁሉም የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተፈጽሞበት የሚለቀቅ ዕቃ በጉምሩክ ጣቢያው ወይም በማንኛውም ሌላ ቦታ ተደራሽ በመሆን መፈጸም ይችላል፡፡

፭/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን የሚገኝ እቃ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ቢፈጸምበትም ሆነ ሳይፈጸምበት ላልተገደበ ጊዜ ሊቆይ ይችላል፡፡

**፸. <u>በጉዞ ላይ ላሉ ዕቃዎች የሚሰጥ ዋስትና</u>**

ከውጭ ሀገር ወደ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን፣ ወይም በሀገር ውስጥ ከሚገኝ ሌላ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ወይም ከጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ወደ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን በሚተላለፍ ዕቃ ላይ ተጠቃሚው በጉምሩክ ሕግ በሚወሰነው መሰረት ተመጣጣኝ የቀረጥና ታክስ ዋስትና ማስያዝ ይኖርበታል፡፡

**፸፩. <u>ስለምርት ሂደት እና ክንውን</u>**

፩/ የዚህ አዋጅ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዞኑ ውስጥ ዕቃዎች ሊከማቹ፣ ሊሸጡ፣ ለእይታ ሊቀርቡ፣ ሊበተኑ፣ እንደገና ሊታሸጉ፣ ሊገጣጠሙ፣ ሊከፋፈሉ፣ ሊለዩ፣ ደረጃ ሊወጣላቸው፣ ሊደባለቁ ወይም ሊመረቱ ይችላሉ።

another user within a special economic zone shall be treated as export and be subject to appropriate customs procedures.

3/ The transfer or sell of goods effected in accordance with Sub-Article (2) of this Article shall be exempt from any customs duty and tax.

4/ When the Customs Commission permits, all customs formalities and the release of goods in a special economic zone may be undertaken at a customs station or any other accessible location.

5/ Within a special economic zone, goods can be kept for an unlimited period of time with or without undergoing customs formalities.

**70. <u>Guarantee for goods in transit</u>**

In respect of goods moved from abroad to a special economic zone, or from another special economic zone or from a bonded warehouse to a special economic zone, a duty and tax guarantee must be secured by the end-user as established under the appropriate customs law.

**71. <u>Product processing</u>**

1/ Subject to the applicability of this Proclamation and other applicable laws, goods within a special economic zone may be stored, sold, displayed, dispersed, repackaged, assembled, distributed, adjusted, graded, mixed, or otherwise manufactured.

https://t.me/customsclearingagents

፪/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የሚገኙ ዕቃዎች ወደ ውጭ ለመላክ፣ ለጥገና፣ ለፕሮሰሲንግ፣ ወይም ወደ ሌላ እቃ ለመቀየር፣ ወይም ሥልጣን ባለው አካል በተለየ ሁኔታ በሚሰጠው ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ከልዩ ኢኮኖሚ ዞኑ ክልል ማውጣት አይቻልም፡፡

**፸፪. ተመልሰው ከሀገር ስለሚወጡ ወይም ወደ ሀገር ስለሚገቡ ዕቃዎች**

፩/ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ከመጠናቀቁ በፊት ወደ ውጪ ሀገር ተመልሶ እንዲወጣ ጥያቄ የቀረበበት እቃ ያልተከለከለ ወይም አግባብነት ያለው የጉምሩክ ሕግን የማይጻረር እስከሆነ ድረስ ከማናቸውም ክፍያ ነጻ ተደርጎ እንዲወጣ ይፈቀዳል፡፡

፪/ ማናቸውም ዕቃ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ተመርቶ ወደ ውጭ ከተላከ በኋላ በሽያጭ ውሉ ወይም በንግድ ግንኙነቱ ላይ የተመለከተውን የጥራት ደረጃ ባለማሟላቱ ምክንያት ተመልሶ ወደ ሀገር የሚገባ ከሆነ የጊዜ ገደብ ሳይደረግበት ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ይሆናል፡፡

**፸፫. ተረፈ-ምርትን ስለመሸጥ**

፩/ በሚመለከተው አካል ሲረጋገጥ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ በምርት ሂደት የሚፈጠር ተረፈ-ምርትን በዞኑ ውስጥ መሸጥ ይፈቀዳል፡፡ በዚህ አግባብ የሚሸጥ ተረፈ-ምርት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ አይከፈልበትም፡፡

፪/ በሚመለከተው አካል ሲረጋገጥ በምርት ሂደት የሚፈጠር ተረፈ-ምርት በጉምሩክ ክልል እንዲሸጥ የጉምሩክ ኮሚሽን ይፈቅዳል፡፡ በዚህ አግባብ የሚሸጥ ተረፈ-ምርት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ይከፈልበታል፡፡

2/ Goods within a special economic zone cannot be moved out of such area except for export, repair, maintenance, processing, or conversion, or unless such is specifically authorized by the competent authority.

**72. Re-export or import of goods**

1/ Goods in respect of which a request for re-export is made before the completion of customs formalities shall be exempted from any payment if the goods are not prohibited items or their entry had not contravened the pertinent customs law.

2/ Any good produced within a special economic zone which is exported but has to be re-imported because of failure to comply with quality standards specified in a sale agreement or business relationship shall be exempted from customs duties and taxes without any time limit.

**73. Sale of wastage**

1/ When verified by the competent authority, by-products of a manufacturing process produced within a special economic zone can be sold within the zone. Such by-products shall not be subject to customs duties and taxes.

2/ When verified by the competent authority, the sale of by-products within the customs territory shall be permitted by Customs Commission. Such by-products shall be subject to customs duties and taxes.

https://t.me/customsclearingagents
https://t.me/customsclearingagents

**፸፬. ስለሚወገዱ ዕቃዎች**

፩/ ጥቅም ላይ እንደማይውል በሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል ማረጋገጫ የተሰጠበት ማንኛውም በልዩ ኢኮኖሚ ዞን የሚገኝ ዕቃ የሚመለከተው አካል እና ጉምሩክ ኮሚሽን በተገኙበት እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚወገድ ዕቃ ቀረጥና ታክስ አይከፈልበትም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚወገድ ዕቃ አስቀድሞ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ያለው እንደሆነ ለከፋዩ ተመላሽ ይደረግለታል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚወገድ ዕቃ የማስወገጃ ወጪ በዕቃው ባለቤት የሚሸፈን ይሆናል፡፡ የሚወገደው ዕቃ ባለቤት የሌለው ወይም ባለቤቱን መለየት የማይቻል እንደሆነ ወጪው በአስተዳዳሪው የሚሸፈን ይሆናል፡፡

**፸፭. ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ለአገልግሎት ስለሚገቡ ዕቃዎች**

የተፈቀደለት አገልግሎት ሰጪ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ለተጠቃሚዎች ወይም ለነዋሪዎች አገልግሎት የሚያስገባቸው ዕቃዎችን በተመለከተ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈፀም ሆኖ ዝርዝሩ የጉምሩክ ኮሚሽን በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

**74. Destruction of goods**

1/ Any good within a special economic zone certified for removal by the competent authority shall be removed in the presence of the competent authority and Customs Commission.

2/ A good disposed in accordance with Sub Article (1) of this Article of shall not be subject to customs duty and tax.

3/ Where duty and tax has already been paid in respect of a good disposed in accordance with Sub-Article (1) of this Article, the duty and tax shall be refunded to the payer.

4/ The cost of removal of a good disposed in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be borne by the owner of the good. Where the good to be removed does not have an owner or the owner cannot be identified, the cost shall be borne by the zone operator.

**75. Goods moved to a special economic zone to provide service**

The customs formality of goods moved to a special economic zone by an authorized service provider for purposes of delivering amenities to end-users or residents shall be subject to customs clearance in accordance with the relevant law, and be specified through a Directive to be issued by Customs Commission.

https://t.me/customsclearingagents

https://t.me/customsclearingagents

**፸፮. የመሰረተ ልማት አቅርቦት**

፩/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ክልል በአግባቡ መለየት አለበት።

፪/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ክልልን የሚለይ አጥር ርዝመት እና አይነት የጉምሩክ ኮሚሽን በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፫/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳዳሪው የጉምሩክ ኮሚሽን በሚያቀርበው ዝርዝር መሰረት ለጉምሩክ አገልግሎት ሥራ አመቺ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች እና ተያያዥ መሰረተ-ልማቶችን የማሟላት ግዴታ አለበት፡፡

**፸፯. በቴክኖሎጂ የተደገፈ የቆጠራ ሥርዓት ስለማደራጀት**

፩/ ማንኛውም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት የዕቃዎችን መግባት፣ ፈቃድ፣ መከማቸት፣ በሂደት ማለፍ፣ ማስተላለፍ እና መውጣት እና በድርጅቱ እጅ ያሉ፣ የተላለፉ ወይም የተሸጡ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ክፍያ ሁኔታን ለመለየት የሚያስችል በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

፪/ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የሚከናወን ማንኛውም የዕቃ ሽያጭ፣ ወደ ውጭ መላክ፣ ወይም የማስወገድ ሥራ ከጉምሩክ ኮሚሽን እውቅና ውጭ የተፈፀመ እንደሆነ ለዕቃው ተገቢ ቀረጥና ታክስ መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ አስተዳደራዊ ቅጣት ያስከትላል።

፫/ ማናቸውም በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የተተወ ወይም ባለቤት የሌለው ዕቃ ለጉምሩክ ኮሚሽን እንዲተላለፍ ተደርጎ አግባብ ባለው አሰራር መሰረት እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

**76. Infrastructure provision**

1/ A special economic zone shall be properly segregated.

2/ The height and type of barrier that encloses a special economic zone shall be specified through a Directive issued by Customs Commission.

3/ To facilitate the provision of customs services, a special economic zone operator shall equip the economic zone with appropriate technologies and associated infrastructure as specified by Customs Commission.

**77. Duty to Maintain Automated Inventory System**

1/ Every special economic zone enterprise shall establish an automated information management system to identify the entry, permit, storage, processing, transfer and exit of goods, and the status of customs duty and tax payment of goods in its possession, transferred, or sold.

2/ Any sale, export, or disposal of goods effected within a special economic zone without the knowledge of Customs Commission shall entail payment of duty and tax on the goods and an administrative penalty.

3/ Any good abandoned or left within a special economic zone shall be handed over to Customs Commission and be disposed of in accordance with the relevant procedures.

https://t.me/customsclearingagents

## ክፍል አስራ አምስት

## ስለ አስተዳደራዊ እርምጃዎች

**፸፰. በቦርዱ ወይም ኮሚሽኑ የሚሰጥ ማስጠንቀቂያ**

፩/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ፣ ወይም በኢንቨስትመንት ፈቃድ፣ ወይም በአልሚ ወይም አስተዳዳሪ ሥምምነት ላይ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን የጣሰ እንደሆነ በኮሚሽኑ ምክረ-ሀሳብ መሰረት ቦርዱ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

፪/ በአስተዳዳሪ፣ በድርጅት ወይም ሌሎች ተጠቃሚዎች ጥሰት በተፈፀመ ጊዜ ማስጠንቀቂያ የሚሰጠው በኮሚሽኑ ይሆናል።

**፸፱. የማስተካከያ እርምጃ፣ ማገድ እና ስረዛ**

፩/ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው አልሚ፣ አስተዳዳሪ፣ ድርጅት ወይም ሌላ ተጠቃሚ ማስጠንቀቂያውን ከተቀበለበት እለት አንስቶ ባሉት ስልሳ ቀናት ውስጥ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ አለበት።

፪/ አልሚው፣ አስተዳዳሪው፣ ድርጅቱ ወይም ሌላ ተጠቃሚ በማስጠንቀቂያው ላይ በተገለፀው የጊዜ ገደብ ውስጥ አሳማኝ ምክንያት ሳይኖረው የማስተካከያ እርምጃ ካልወሰደ እንደአግባብነቱ ቦርዱ ወይም ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ወይም የንግድ ፈቃዱን ከሥልሳ ቀናት ላለበለጠ ጊዜ ሊያግድ ይችላል።

፫/ አልሚው፣ አስተዳዳሪው፣ ድርጅቱ ወይም ሌላ ተጠቃሚ የኢንቨስትመንት ወይም የንግድ ፈቃዱ ታግዶ በቆየበት ጊዜ የማስተካከያ እርምጃ ካልወሰደ እንደአግባብነቱ ቦርዱ ወይም ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ወይም የንግድ

## PART FIFTEEN

## ADMINISTRATIVE MEASURES

**78. Issuance of Reprimand by the Board or the Commission**

1/ Where a special economic zone developer violates provisions established under this Proclamation or Regulation and Directive enacted hereunder, or under the investment permit or a developer agreement, the Board shall issue a reprimand based on recommendation of the Commission.

2/ A reprimand shall be issued by the Commission where a violation is committed by an operator, enterprise or other end-user.

**79. Rectification Measure, Suspension and Revocation**

1/ A developer, operator, enterprise or other end-user issued with a warning notice shall adopt rectification measures within Sixty days of receiving such notice.

2/ Where a developer, operator, enterprise or other end-user fails to take measures within the time-frame indicated in the notice for no reasonable cause, as appropriate, the Board or the Commission may decide that the investment permit or business license be suspended for not more than Sixty days.

3/ Where a developer, operator, enterprise or other end-user fails to take rectification measures during the suspension period, as appropriate, the Board or the Commission may revoke the investment permit or business

https://t.me/customsclearingagents

ፈቃዱን ሊሰርዝ ይችላል።

፬/ የአልሚው፣ አስተዳዳሪው፣ ድርጅቱ ወይም ሌላ ተጠቃሚ የኢንቨስትመንት መክሰር ከታወጀ ወይም ሥራው የተቋረጠ ስለመሆኑ ለኮሚሽኑ ከተገለፀ እንደአግባብነቱ ቦርዱ ወይም ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ወይም የንግድ ፈቃዱን ሊሰርዝ ይችላል።

፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) እና (፬) መሰረት የኢንቨስትመንት ወይም የንግድ ፍቃድ ሲሰረዝ የአልሚው፣ የአስተዳዳሪው ወይም የድርጅቱ በልዩ ኢኮኖሚ ዞኑ ውስጥ ያለሙትን ንብረት መብት ተፈፃሚ የሚሆኑበትን መንገድ አስመልክቶ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## ፹. <u>አበዳሪዎችን እና ሌሎች አካላትን ስለማሳወቅ</u>

፩/ የኢንቨስትመንት ወይም የንግድ ፈቃዱ የሚታገድበት ወይም የሚሰረዝበት ባለሀብት የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ንብረትን በመያዣነት በማስያዝ ብድር የወሰደ ከሆነ እና ኮሚሽኑ ይህ መረጃ ካለው፣ ማንኛውም የፈቃድ ማገድ ወይም ስረዛ እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ለሚመለከተው አካል በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።

፪/ የሶስተኛ ወገኖችን መብት ለማስጠበቅ ኮሚሽኑ የጊዜያዊ ባለአደራ አስተዳደር መሰየምን ጨምሮ ሌሎች እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል።

፫/ ኮሚሽኑ የፈቃድ ስረዛን ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት ባለሀብቱ የሚፈለግበትን ክፍያ የከፈለ ወይም በውል የተመለከቱ ግዴታዎቹን ሁሉ የተወጣ ስለመሆኑ ከጉምሩክ ኮሚሽን እና ከአገልግሎት ሰጪ አካላት ማረጋገጫ እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል።

license.

4/ The Board or the Commission may, as appropriate, revoke a permit or license if a developer, operator, enterprise or other end-user is declared bankrupt or termination of the business activity is revealed to the Commission.

5/ When an investment permit or a business license is revoked pursuant to Sub-Article (3) and (4) of this Article, the consequences thereof in relation to maintaining the property rights of the developer, operator or enterprise shall be specified in a Regulation issued by Council of Ministries .

## 80. <u>Notification to Lenders and Other Entities</u>

1/ Prior to any suspension or revocation measure, the Commission shall notify the relevant entities in writing where the investor had received a loan by attaching an economic zone property, provided that the Commission has information concerning such security agreement.

2/ To preserve the rights of third parties, the Commission may adopt referral measures involving the appointment of an appropriate body, including a provisional trustee.

3/ Before effecting a revocation, the Commission may seek verification from Customs Commission or utility providers that the investor has cleared all required payments or obligations under a contract.

https://t.me/customsclearingagents

**፹፩. <u>የፈቃድ ማገድ ወይም መሰረዝ ውጤቶች</u>**

፩/ የኢንቨስትመንት ወይም የንግድ ፈቃድ መሰረዝ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ተጠቃሚነት ስምምነትን እንዲሁም በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተሰጡ ማበረታቻዎች ወይም ጥቅሞች እንዲቋረጡ ያደርጋል። ኮሚሽኑ ፈቃዱ ለታገደበት ወይም ለተሰረዘበት ኢንቨስትመንት የተሰጡ ማበረታቻዎች ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሱ ወይም እንዲመለሱ ለሚመለከተው አካል ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪/ የኢንቨስትመንት ወይም የንግድ ፈቃድ ከተሰረዘ ባለሀብቱ በሊዝ ወይም በንዑስ ሊዝ የተከራየውን የልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬት ለባለንብረቱ መመለስ አለበት። እርምጃው አልሚን የሚመለከት ከሆነ ስለሚከተለው የአልሚነት ደረጃ ማጣት ሂደት እና ውጤት ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**<u>ክፍል አስራ ስድስት</u>**

**<u>ስለ ቅሬታ፡ ክርክር አፈታት ሥርዓት እና ቅጣቶች</u>**

**፹፪. <u>ቅሬታ እና ክርክር ስለሚስተናገድበት ሥርዓት</u>**

በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የሚነሳ የአስተዳደር ቅሬታ፣ የፍትሐብሔር እና የንግድ ጉዳዮች አለመግባባት እና ክርክር ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ሚዛናዊ የሆነ ሥርዓት በመዘርጋት ይፈታል።

**81. <u>Consequences of Suspension or Revocation of permit</u>**

1/ The revocation of an investment permit or a business license shall entail termination of the special economic zone end-user agreement, as well as of any incentives or benefits accorded under this Proclamation or other applicable laws. The Commission may request the appropriate authority to withdraw or return, in whole or in part, the incentives granted to the investment whose permit or license has been suspended or revoked.

2/ When an investment or business permit is revoked, a special economic zone land leased or sub-leased by the investor shall be returned to the property owner. Where the measure applied pertains to a developer, the effects of losing a developer status and the consequences thereof shall be specified through a Directive issued by the Board.

**<u>PART SIXTEEN</u>**

**<u>GRIEVANCE, DISPUTE HANDLING PROCEDURE AND SANCTIONS</u>**

**82. <u>Grievance and Dispute Settlement procedures</u>**

Administrative complaints, civil and commercial issues and disputes that arise within special economic zones shall be resolved through the deployment of an efficient, effective, and equitable system.

https://t.me/customsclearingagents

https://t.me/customsclearingagents

**፹፫. ለኮሚሽኑ የሚቀርብ ቅሬታ**

፩/ ማንኛውም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ተጠቃሚ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ሥልጣኑን ተግባራዊ በሚያደርግ አካል የሚወሰድ የመጨረሻ እርምጃን በመቃወም ቅሬታውን ለኮሚሽኑ የማቅረብ መብት አለው።

፪/ ቅሬታው በፅሁፍ ሆኖ ቅሬታ ያስነሳው እርምጃ ከተወሰደበት እለት አንስቶ ባሉት ሰላሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ መቅረብ አለበት።

፫/ ኮሚሽኑ በአንድ ማዕከል አገልግሎት ሥርዓት ማእቀፍ ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር ቅሬታው በደረሰ በሰላሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ የመፍትሄ ሀሳብ ያቀርባል።

፬/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ማዕከል አገልግሎት ማእቀፍ ወይም በሌላ አሰራር መሰረት በማናቸውም መንግስታዊ ተቋም የሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት ላይ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት ተቋሙ ከኮሚሽኑ ጋር አማራጭ የመፍትሄ ሀሳብ ለማቅረብ የሚያስችል ምክክር የማድረግ ግዴታ አለበት።

**፹፬. ከኮሚሽኑ ውሳኔ ለቦርዱ የሚቀርብ ቅሬታ**

፩/ ቦርዱ የኮሚሽኑን ማናቸውንም አስተዳደራዊ ውሳኔ በመቃወም ውሳኔው በተሰጠ በሰላሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ የሚቀርብ ቅሬታን ይቀበላል፡፡

፪/ ቅሬታው በኮሚሽኑ ከተሰጠ ውሳኔ ወይም ከተወሰደ አስተዳደራዊ እርምጃ ግልባጭ ጋር ሆኖ በጽሑፍ መቅረብ አለበት፡፡

**83. Grievance Submitted to the Commission**

1/ Any special economic zone end user shall have the right to lodge a complaint to the Commission against a final measure taken by a competent authority exercising its powers within a special economic zone.

2/ A complaint shall be lodged with the Commission in writing within Thirty consecutive days of the taking of the measure in question.

3/ The Commission shall, within Thirty consecutive days of its submission, engage with the competent authority through the one stop service system and issue a written recommendation to solve the grievance.

4/ Without prejudice to the stipulation of Sub-Article (1) of this Article, before an administrative measure is adopted against a special economic zone enterprise by any government agency within the framework of one stop services or other procedures, such agency is obliged to consultatively engage with the Commission and search for alternative solutions.

**84. Grievance Submitted to the Board Against the Commission's Decision**

1/ The Board can receive a complaint submitted against any final administrative decision of the Commission lodged within Thirty days of its taking.

2/ The complaint shall be made in writing along with a copy of the decision or measure taken by the Commission.

https://t.me/customsclearingagents

፫/ ቦርዱ ቅሬታው በደረሰው በሰላሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

፬/ በቦርዱ የመጨረሻ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔውን በተቀበለ በሰላሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

፭/ የቦርዱ ወይም የኮሚሽኑ ውሳኔ ወይም አስተዳደራዊ እርምጃ ግልባጭ እንዲሰጠው ቅሬታ አቅራቢው ከጠየቀ በሰባት ተከታታይ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ይሰጠዋል፡፡

፮/ በዚህ ክፍል በተለይ ባልተመለከቱ ጉዳዮች ላይ የፌዴራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፫/፪ሺ፲፪ የአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ፣ ቅሬታ አቀራረብ እና የፍርድ ቤት ክለሳ ሥርዓት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

**፹፭. ስለ እርቅ**

፩/ ኮሚሽኑ የፍትሐብሔር እና የንግድ ጉዳዮችን እና ክርክሮችን ጨምሮ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ተጠቃሚዎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን በአንድ ማዕከል አገልግሎት ሥርዓት ማእቀፍ በእርቅ እንዲያልቁ ያደርጋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አገልግሎት የሚሰጠው ቅሬታ ውስጥ የገቡ ወገኖች ሥርዓቱን ለመጠቀም ተስማምተው ጥያቄያቸውን በጽሑፍ ሲያቀርቡ ብቻ ነው።

፫/ የእርቅ ጥያቄ በቀረበ ጊዜ ኮሚሽኑ በአንድ ማዕከል አገልግሎት ውስጥ የሚገኝ አስታራቂ ባለሙያ ይሰይማል፡ ባለሙያው ከባለጉዳዮች ጋር በመነጋገር ቅሬታው በቀረበ በሰላሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ የመጨረሻ የመፍትሔ

3/ The Board shall render its decision within Thirty consecutive days.

4/ Any party aggrieved by a final decision of the Board may, within Thirty consecutive days of receiving such decision, lodge its appeal with the Federal High Court.

5/ Where an aggrieved party requests, the decision or administrative measure taken by the Commission or the Board shall be issued in writing within seven consecutive days of the request.

6/ In respect of matters not specifically regulated under this section, the provisions of the Federal Administrative Procedure Proclamation No. 1163/2020 relating to administrative decision making, grievance submission and judicial review shall be applicable.

**85. Conciliation**

1/ The Commission shall cause the resolution of issues or disputes, including civil and commercial matters arising between special economic zone end-users, through conciliation service which shall be availed within the one stop service platform.

2/ The service specified under Sub-Article (1) of this Article shall be provided only if the parties agree to use the platform and submit their request in writing.

3/ Where a request for conciliation service is submitted to the Commission, the Commission shall engage a conciliator from the one stop service; the conciliator shall consult with the parties and adopt, within

https://t.me/customsclearingagents

ሐሳብ በጽሁፍ ያቀርባል።

፬/ ቅሬታ ውስጥ የገቡ ወገኖች የኮሚሽኑ አስታራቂ ባለሙያ አዘጋጅቶ ባቀረበው ምክረ ሀሳብ ይገደዳሉ፡ ቅሬታ ከገቡ ወገኖች አንዱ የመፍትሄ ሀሳቡን አለመቀበል የሚችለው የመፍትሄ ሀሳቡ ከቀረበበት እለት ጀምሮ ባሉት ሰባት ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ተቃውሞውን ከገለፀ ብቻ ነው።

፭/ ተገልጋዮች ከእርቅ ሂደቱ ጋር በተያያዘ የወጡ ወጪዎችን በየራሳቸው ይሸፍናሉ፡፡

## ፹፮. ስለ ግልግል

፩/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ተጠቃሚዎች አለመግባባቶችን በግልግል ዳኛ ለመጨረስ መስማማት ይችላሉ።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሰረት በግልግል የሚያዝ ጉዳይን አስመልክቶ የሚደረግ ስምምነት በጽሑፍ መደረግ አለበት።

፫/ ቅሬታ ውስጥ የገቡ ወገኖች አንድ ወይም ከአንድ በላይ የግልግል ዳኞችን ለመሰየም፣ ተፈፃሚ የሚሆኑ መሰረታዊ እና የሥነ-ሥርዓት ህጎችን ለመምረጥ፣ የግልግል ዳኞችን ወጪ ለመወሰን እና መሰል ጉዳዮችን ለመምራት ነፃ ናቸው፡፡

## ፹፯. የፌዴራል ዳኝነት ችሎች አደረጃጀት

፩/ በፌዴራል ሕገ መንግስት ላይ የተመለከተውን ስነ ስርአት በመከተል በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ በሚነሱ የስራ፣ የፍትሐብሄር እና የንግድ አለመግባባቶች እና የወንጀል ጉዳዮች ላይ የፌዴራል ዳኝነት ስልጣን የሚኖረው አንድ ወይም ከአንድ በላይ ቋሚ ወይም ተዘዋዋሪ



thirty consecutive days of submission of the complaint, a final recommendation in respect of the dispute.

4/ The parties shall be bound by any recommendation which the Commission's conciliator draws; however, a party may reject the recommendation if it does so in writing within Seven days from the date of the issuance of such recommendation.

5/ The parties shall settle own expenses incurred in connection with a conciliation procedure.

## 86. Arbitration

1/ Special economic zone end-users may agree to resolve their disputes through arbitration.

2/ Any arrangement referred to arbitration under Sub-Article (1) of this Article shall be concluded in writing.

3/ The disputing parties shall be free to determine procedures for the appointment of one or more arbitrators, the choice of applicable substantive and procedural laws, determination of arbitrator fees, and regulation of related matters.

## 87. Organization of a Federal Judicial Bench

1/ Following the procedures prescribed under the federal constitution, one or more dedicated or circuit-based bench shall be organized within special economic zones having federal jurisdiction on labor, civil and commercial disputes and criminal matters.

https://t.me/customsclearingagents

ችሎት እንዲቋቋም ይደረጋል።

፪/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎቱ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ እንዲደራጅ ያደርጋል፡፡

**፹፰. የሕግ ማስከበር ስራ እና የመረጃ ልውውጥ**

ኮሚሽኑ አግባብነት ባላቸው የፀጥታ እና የሕግ አስከባሪ አካላት፣ አልሚዎች፣ አስተዳዳሪዎች እና ድርጅቶች መካከል በልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ትብብር እና ቅንጅት እንዲኖር ያደርጋል።

**፹፱. አስተዳደራዊ ቅጣት፣ የገንዘብ ቅጣት እና እርምጃዎች**

፩/ በዚህ አዋጅ እና ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ ላይ የተመለከቱ ግዴታዎች ወይም ሁኔታዎች ጥሰት ሲያጋጥም፣ እንዲሁም በኢንቨስትመንት ፈቃድ፣ የንግድ ፈቃድ እና ሌሎች ስምምነቶች ላይ የተመለከቱ ሁኔታዎች ሳይከበሩ ሲቀሩ ኮሚሽኑ አስተዳደራዊ ቅጣት፣ የገንዘብ ቅጣት እና እርምጃዎችን እንዲወስድ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል።

፪/ የቅጣቱ መጠን ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

**ክፍል አስራ ሰባት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**፺. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡

2/ The Federal Supreme Court shall facilitate the establishment of such a bench within a special economic zone.

**88. Law Enforcement and Information Exchange**

The Commission shall ensure coordination between the pertinent security and law enforcement entities, developers, operators, and enterprises.

**89. Administrative Penalties, Fines and Sanctions**

1/ The Commission is hereby vested with authority to enforce administrative penalties, fines and sanctions in respect of violations or non-compliance with this Proclamation, or regulation and directives enacted hereunder, including for failures to comply with conditions stipulated under permits, licenses, or agreements.

2/ The amount of penalties shall be prescribed in a Directive to be issued by the Board.

**PART SEVENTEEN**

**MISCELLANEOUS PROVISIONS**

**90. Powers to issue regulation and Directive**

1/ The Council of Ministers may issue regulations required to implement this Proclamation.

https://t.me/customsclearingagents

፪/ ቦርዱ እና ኮሚሽኑ ለዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ተከትሎ ለሚወጣ ደንብ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ያወጣሉ።

2/ The Board and the Commission shall issue Directives necessary for the implementation of this Proclamation and Regulation issued hereunder.

**፺፩. <u>የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>**

**91. <u>Repealed and Inapplicable laws</u>**

፩/ የኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፮/፪ሺ፯ እና የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፲፯/፪ሺ፱ በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።

1/ The Industrial Park Proclamation No.886/2015 and Industry Park Regulation No.417/2017 are hereby repealed.

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

2/ In respect of maters covered by this Proclamation, any proclamation, regulation, directive or customary practice that is inconsistence with this Proclamation shall have no effect.

**፺፪. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>**

**92. <u>Transitory provisions</u>**

፩/ ይህ አዋጅ በስራ ላይ ከሚውልበት ጊዜ ጀምሮ የነባር ኢንዱስትሪ ፓርኮች አስተዳደር፣ ቁጥጥር እና ድጋፍ ስራ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እና ማስፈፀሚያ ህጎች ይመራል።

1/ On entry into force of this Proclamation, the administration, regulation and facilitation of all existing industrial parks shall be subject to the provisions of this Proclamation and its executive Regulations.

፪/ በኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፮/፪ሺ፯ እና በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፲፯/፪ሺ፱ መሰረት የወጡ መመሪያዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ እና በሌላ መመሪያ እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል።

2/ So far as they are not inconsistent with this Proclamation and pending their replacement, Directives issued under the Industry Parks Proclamation No. 886/2015 and Industry Parks Regulation No. 417/2017 shall remain in force.

፫/ ደረጃ በደረጃ ተፈጻሚ የሚሆኑ የዚህ አዋጅ ውስን ክፍሎችን የመለየት የቦርዱ ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ - ሁሉም ነባር የኢንዱስትሪ ፓርኮች ወይም በዚህ መልኩ የተሰየሙ ሌሎች ዞኖች ይህ አዋጅ በስራ ላይ ከዋለበት እለት

3/ Without prejudice to the Board’s power to identify the gradual application of specific sections of this Proclamation to industrial parks, all existing industrial parks or other zones designated as such shall be presumed

https://t.me/customsclearingagents

አንስቶ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን እንደሆኑ ተቆጥሮ በዚህ አዋጅ መሰረት ይተዳደራሉ።

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎች የተሻለ መብት የሚሰጡ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በተሰየሙ ሁሉም የኢንዱስትሪ ፓርኮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

፭/ በዚህ አዋጅ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር ከኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎች ጋር የተደረጉ ስምምነቶች እና የተረጋገጡ ወይም የተሰጡ የማበረታቻ ሥርዓቶች ፀንተው ይቀጥላሉ።

፮/ ይህ አዋጅ በሥራ ላይ በዋለበት ጊዜ በኮሚሽኑ እየታዩ ያሉ የኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ፈቃድ ማመልከቻዎች በዚህ አዋጅ መሰረት እንደቀረቡ ተቆጥረው ውሳኔ ያገኛሉ።

፺፫. <u>ስለነባር የክልል አግሮ-ፕሮሰሲንግ ፓርኮች</u>

ይህ አዋጅ ከወጣ በኋላ በክልሎች ባለቤትነት የተያዙ የአግሮ ፕሮሰሲንግ ፓርኮች አስተዳደር እና ቁጥጥር በዚህ አዋጅ ማእቀፍ ውስጥ ስለሚውልበት አሊያም በሌላ አሰራር ስለሚመራበት ሁኔታ የሚመለከታቸው ክልሎች እና ኮሚሽኑ በጋራ ይወስናሉ። ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

special economic zone entities and be governed by this Proclamation.

4/ Without prejudice to the stipulation of Sub-Article (3) of this Article, the provisions of this Proclamation that confer better rights in respect of industrial park end-users shall apply to all industrial parks designated before the coming into force of this Proclamation.

5/ Unless provided otherwise, all prior agreements entered into with industrial park end-users and the incentive regimes guaranteed or granted shall remain valid.

6/ Any application in respect of the development of industrial parks pending before the Commission at the time of entry into force this Proclamation shall be deemed to have been presented pursuant to this Proclamation.

**93. <u>Existing regional agro-processing parks</u>**

The concerned regions and the Commission shall jointly determine the condition under which the administration and regulation of existing agro-processing parks owned by regional states fall within the scope of this Proclamation or remain regulated through a different procedure. The details shall be specified in a Board Directive.

https://t.me/customsclearingagents

**፺፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፩፪ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**94. Effective date**

This Proclamation shall enter into force on the date of its Publication in Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, on this 20th day of May 2024.

**Sahilework Zewude**

**President of the Federal Democratic Republic of Ethiopia**

https://t.me/customsclearingagents

https://t.me/customsclearingagents